አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና

ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

የድኅረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

# ከ2001 — 2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ትንተና

በ

ሲሳይ ቴሌ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

መጋቢት 2007 ዓ.ም.

# ከ2001 — 2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት
የድኅረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

ለ "ተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር"
ለአርትስ ማስተርስ ዲግሪ በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሲሳይ ቴሌ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

መጋቢት 2007 ዓ.ም.

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

## የድኅረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

# ከ2001 — 2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ትንተና


በ

ሲሳይ ቴሌ


መጋቢት 2007 ዓ.ም.

## የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| ______________________ | ______________________ |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

ከሁሉም አስቀድሜ ሁሉ እንዲሆን ላደረገ ለዓለም መድኃኒት እና ለእናቱም ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

በማስከተል ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ እዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ሳይሰለቹ ክፍተቶቼን በማሳየት፣ ሙያዊ ድጋፋቸውን ለሰጡኝ ለመምህሬና ለአማካሪዬ ለዶ/ር ጌታሁን አማረ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍትንና መርሀ ትምህርቶችን በማዋስ የተባበሩኝ ወ/ሮ የኔነሽ እስመላለምን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ የሞራል ድጋፍ በመስጠት ላበረታቱኝ መምህሮቼ፣ ለክፍል ጓደኞቼና ለሥራ ባልደረቦቼ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........................................................................................................ I
ማውጫ ........................................................................................................ II
የሰንጠረዥ ማውጫ ........................................................................................ V
የግራፍ ማውጫ ............................................................................................ VI
አህጽሮተ ጥናት ............................................................................................ VII

## ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........................................................................................................ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ ................................................................................................ 1
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................................................ 3
1.3.የጥናቱ ዓላማ ............................................................................................. 4
1.4.ጥናቱ የሚመልሳቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ........................................................ 5
1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ .......................................................................................... 5
1.6.የጥናቱ ወሰን ............................................................................................. 6

## ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት .............................................................................................. 7
2.1.የቋንቋ ፈተና ............................................................................................. 7
2.1.1. የቋንቋ ፈተና ምንነት................................................................................ 7
2.1.2. የቋንቋ ፈተና ዓላማ .................................................................................. 8
2.1.3. የቋንቋ ትምህርትና ፈተና ተዛምዶ ................................................................ 8
2.1.4. የቋንቋ ፈተና መመዘኛ መስፈርት ................................................................. 9
2.1.5. የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች ............................................................................. 12
2.1.5.1. ከፈተና ዓላማ አኳያ ........................................................................... 12
2.1.5.2. ከሚተገበርበት ወቅት አኳያ.................................................................... 16
2.1.5.3. ከአቀራረብ ስልት አኳያ ......................................................................... 16
2.1.6. የቋንቋ ፈተና ጥያቄ ትንተና ...................................................................... 19

2.2. የሰዋስው ትምህርት እና ፈተና ይዘት ........................................ 22
2.2.1. የሰዋስው ምንነት ................................................ 22
2.2.2. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ........................................ 23
2.2.3. የሰዋስው ፈተና ይዘት ............................................ 25
2.3. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት .............................................. 26

## ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴ ............................................................ 29
3.1. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ............................................ 29
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ........................................ 30
3.3. የናሙና አመራረጥ .................................................. 31
3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ............................................. 31

## ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተና ........................................................ 33
4.1. የፈተናዎች ቅኝት .................................................. 33
4.2. የተተኳሪ ፈተናዎች የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ......................... 39
4.3. የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከመርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ
መጻሕፍት አንጻር ..................................................... 42
4.3.1. በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ
የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ............................................ 42
4.3.2. የተተኳሪ ፈተናዎች የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች
ከመርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት አንጻር ........................ 45
4.4. በየፈተናዎቹ ውስጥ በሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ ላይ
ከፈተና መርሆዎች አኳያ የሚታይባቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ..... 49
4.4.1. በጥያቄዎቹ አቀራረብ ላይ የታዩ ጠንካራ ጎኖች ...................... 50
4.4.2. በተተኳሪ ጥያቄዎች ላይ የታዩ ደካማ ጎኖች ........................ 53

## ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ እና አስተያየት .......................................................................... 60
5.1. ማጠቃለያ ……………...................……....……...............……........... 60
5.2. አስተያየት ...........…………..................……....…….................... 63

ዋቢ ጽሑፎች …………………………..……………………………........…. 65

አባሪዎች

አባሪ ሀ …………………………..……………………………..….......... 71

አባሪ ለ ……………………………………………………………........... 77

አባሪ ሐ ...…………………………..……………………………............ 82

አባሪ መ ……………………………………………………………..…....... 88

አባሪ ሠ …………………………..…………………………….............. 95

አባሪ ረ …………………………..…………………………….......... 100

አባሪ ሰ …………………………..……………………………..….…..... 106

ማረጋገጫ …………………………..…..……………………………........…. 107

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡- የተተኳሪ ፈተናዎች አጠቃላይ የጥያቄ ብዛት

በቁጥርና በመቶኛ ........................................................ 37

ሠንጠረዥ 2፡- የተተኳሪ ፈተናዎች የሰዋስው ጥያቄዎች

ይዘት እና መጠን ........................................................ 39

ሠንጠረዥ 3፡- ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተዘጋጁ

የአማርኛ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት

ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች .................................. 43

# የግራፍ ማውጫ

ግራፍ 1፡- የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ብዛት

በቁጥርና በመቶኛ ……………………………………………..…… 38

ግራፍ 2፡- የተተኳሪ ፈተናዎች የሰዋስው

ጥያቄዎች ይዘትና ብዛት …………………………..…..…………... 41

# አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ መተንተን ነው። በጥናቱም ዓይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ስልትን በመጠቀም ለጥናቱ ዋና ዋና ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷቸዋል። በሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በተዛማጅ ጽሑፍ ክፍል ውስጥ ከተነሱት ንድፈ-ሀሳባዊ ጉዳዮች አኳያ ተተንትነዋል። በዚህም መሰረት ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2006 ዓ.ም. በተሰጡት የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የቋንቋን አጀማመርና ባህርያት፣ ስነ-ድምጽን፣ ስነ-ምዕላድን፣ ስነ-አገባብን እና ስነ-ፍችን የሚመለከቱ ዋና ዋና ይዘቶች ተካተው እንደሚገኙ ማረጋገጥ ተችሏል። በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ይዘት ጥያቄዎች አብዛኞቹ በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱን ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አብዛኛውን የሰዋስው ይዘት እንዳካተቱ ማረጋገጥ ተችሏል። በ2002 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ የምዕላድንና የቃልን አንድነት እና የስም መሙያን፣ በ2003 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ የአረፍተ ነገርን ስልት የሚወክል ጥያቄ እና በ2006 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ደግሞ የስምና የግስ ገላጭን የሚወክሉ ጥያቄዎች በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያልተካተቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ተካተው እንደሚገኙ ማረጋገጥ ተችሏል። በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በመርሀ ትምህርቶቹ እና በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተሰጣቸው የትኩረት ደረጃ አኳያ ለየይዘቶቹ ተገቢ ውክልና እንዳልተሰጣቸው በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል። ተተኳሪ ፈተናዎችም ከፈተና መርሆዎች አኳያ ሲፈተሹ ጠንካራ ጎናቸው የሚያመዝን ቢሆንም እንኳ ደካማ ጎንም ታይቶባቸዋል። በመጨረሻም በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ፈተናዎች የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ላይ የታዩት ደካማ ጎኖች ወደፊት በሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ እንዳይደገሙና ጥንቃቄ ለማድረግ ያመች ዘንድ አስተያየት ተሰንዝሯል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ የተማሪዎችን አራቱን የቋንቋ ክሂል ማጎልበት፣ የሥነ-ጽሑፍና የሥነ-ልሳን ዕውቀትን ማዳበር ነው፡፡ ይህን አጠቃላይ ዓላማ ለማሳካት በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ከተማሯቸው በኋላ የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች መረዳት አለመረዳታቸውን፣ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን፣ የቋንቋው ትምህርት ዓላማ የታለመለትን ግብ መምታት አለመምታቱን፣ ተማሪዎች በየደረጃው የተፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለመድረሳቸውን ለማረጋገጥ ምዘናዎች ይካሄዳሉ፡፡

ምዘና የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ለማሳካት እና ለውሳኔ የሚረዳ መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችል ስልት ነው፡፡ ይህንንም የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት አስመልክቶ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት (1985፡31) ባዘጋጀው አጠቃላይ የትምህርት ሥልጠና ረቂቅ ፖሊሲ ማብራሪያ ላይ "ምዘና በማስተማር መማር ሂደት አካልነቱ የተማሪውን እውቀት፣ ክህሎትና ዝንባሌ አስመልክቶ በተከታታይ ወይም በማጠቃለያ (Formative or Summative) የሚካሄድ ምርምር አዘል ተግባር ነው፡፡" በማለት ገልጿል፡፡ ይህም ምዘና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከሚከወኑ ዐበይት ተግባራት ውስጥ አንዱ በመሆኑ የተነሳ በትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅትም (ሀ.አ.ፈ.ድ.) (1994፡3) ምዘና የትምህርት ግብዓትና ሂደት መስተጋብራዊ ውጤትን አስመልክቶ ለውሳኔ የሚረዳ አጠቃላይ መረጃ የመሰብሰቢያ ሂደት መሆኑን

ገልጿል። በዚህም የተነሳ የቋንቋ ፈተና የታለመውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተግባራዊነት ለማረጋገጥ፣ የተፈለገውን መረጃ በሚፈለገው መጠን ለማግኘት ሲባል ምዘናዎች ይካሄዳሉ።

እንደማንኛውም የትምህርት ዓይነት በማስተማር ሂደት ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ፈተና ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። Bachman (1990፡54) የቋንቋ ፈተና መሰረታዊ ጠቀሜታ ለውሳኔ የሚያበቃ መረጃ ማስገኘት መሆኑን ገልጸዋል።

በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርት በተገቢ መልኩ መሰጠቱን ለማረጋገጥ እና የተፈለገውን መረጃ ለመሰብሰብ ምዘና በተለያዩ የመመዘኛ መሳሪያዎች አማካይነት ይካሄዳል። የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት (1985፡31) "የትምህርት ውጤትን ደረጃ ለመመዘን ከሚያስችሉ የመመዘኛ መሣሪያዎች መካከል ፈተና፣ መጠይቅ፣ ቃለመጠይቅ እና ምልከታ ዋነኞቹ ናቸው። ከነዚህ መካከል ፈተና የጎላ ድርሻ አለው።" በማለት ገልጿል። ሀ.አ.ፈ.ድ. (1994፡9) "መረጃ ለመሰብሰብ ከሚረዱ መሣሪያዎች መካከል የጽሑፍ እና የቃል ፈተናዎች፣ መጠይቆች፣ የክፍል ውስጥ ውይይቶች፣ የክፍል እና የቤት ሥራዎች፣ ቀጥታና ቀጥተኛ ያልሆኑ ምልከታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።" በማለት በመመዘኛነት የሚያገለግሉትን መሳሪያዎች አስፍሯል። ከተለያዩ የመመዘኛ መሳሪያዎች ውስጥ ተዘውትሮ የሚሰራበት እና ጉልህ ሚና ያለው ፈተና ነው። በማስተማር ሂደት ውስጥ ፈተና በተከታታይ ምዘናነት ወይም በማጠቃለያ ፈተናነት ሊሰጥ ይችላል። ሀ.አ.ፈ.ድ. (1994፡2) በአንድ የትምህርት እርከን ማጠናቀቂያ ማለትም በአንደኛ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ የሚሰጡ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች የትምህርት ምዘና አካሎች መሆናቸውን ይገልጻል።

ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት በየዓመቱ 10ኛ ክፍልን ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተናን፣ 12ኛ ክፍልን ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናን አንድ ወጥ በሆነ መልኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይሰጣል (ትምህርት ሚኒስቴር 1994፡40)።

በኢትዮጵያ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተና ከ1993 ዓ.ም. ጀምሮ በመሰጠት ላይ ይገኛል (ትምህርት ሚኒስቴር 1993፡32)፡፡ ለተፈታኞች በተማሯቸው የትምህርት ዓይነቶች መነሻነት ተዘጋጅተው ከሚሰጡት የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ አንዱ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነው፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተዘጋጅተው በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡ ይህ ጥናትም ከ2001—2006 ዓ.ም. ለስድስት ተከታታይ ዓመታት በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያነት በብሔራዊ ደረጃ በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት እና አቀራረብ ላይ አተኩሯል፡፡

በቋንቋ ፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች የተማሪዎችን የሰዋስው ችሎታ፣ ዕውቀት ለመለካትና ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ ያገለግላሉ፡፡ Heaton (1988፡9) የሰዋስው ፈተና የተማሪዎችን የሰዋስው ችሎታ ለመለካት እንደሚያገለግል ገልጸዋል፡፡ በቋንቋ ፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች በተፈለገው መጠን የተማሪዎችን የሰዋስው ችሎታ መለካት አለመለካታቸውን፣ ተገቢ የመመዘኛ መሳሪያ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ በፈተናዎች ላይ ጥናት ሊካሄድባቸው ይገባል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት ከ2001—2006 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ላይ ጥናት እንዲካሄድ አነሳሽ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል ቀዳሚው አጥኚው በስራ ሂደት በፈተናው ውስጥ አንዳንድ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተካተው አለመገኘታቸውን መመልከቱ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱትንና ያልተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች

ለይቶ ለማወቅ ያለው ፍላጎት ነው፡፡ ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ላይ የተሰራ ጥናት አለመኖሩም ጥናቱን ለማካሄድ አነሳስቶታል፡፡

ሌላው በክልል ደረጃ ለስምንተኛ ክፍል ማጠናቀቂያነት በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች መነሻነት በተሰሩ ጥናቶች ላይ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከፈተና መርሆዎች አንጻር የሚታይባቸው ድክመቶች እንዳሉ ተገልጿል (አበበች 2004 ፣መሠረት 2005)፡፡ በክልል ደረጃ በተዘጋጁት የአማርኛ ፈተናዎች በሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት አቀራረብ ላይ ድክመቶች ከታዩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከፈተና መመዘኛ መስፈርት እና ከፈተና መርሆዎች አኳያ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማወቅ፣ የሚታይባቸውንም ድክመት ለመፈተሽ ያለው የአጥኚው ፍላጎት በተጠቀሰው ርዕስ ላይ ጥናቱን እንዲያካሂድ አነሳስተውታል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛው ዓላማ ከ2001—2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት አማካይነት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያነት ተዘጋጅተው በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የሰዋስው ጥያቄዎችን ይዘትና አቀራረብ መተንተን ሲሆን፣ ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

- ከ2001—2006 ዓ.ም. ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ምን ምን የሰዋስው ይዘቶች እንደተካተቱ መለየት፣
- በጥያቄዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በመርሀ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው

ትምህርት ይዘቶች አንጻር የተካተቱትን እና ያልተካተቱትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች መለየት፣

- በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከፈተና መርሆዎች አኳያ የሚታይባቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን መለየት፣

የሚሉት ናቸው።

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች

በጥናቱ ውስጥ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል።

- ከ2001—2006 ዓ.ም. ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ምን ምን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካተዋል?
- በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በመርሀ ትምህርቶቹ እና በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አንጻር ሲታዩ በየፈተናዎቹ ውስጥ የትኞቹ የሰዋስው ይዘቶች ተካተዋል?
- በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት የፈተና መመዘኛ መስፈርትን ያሟሉ ናቸውን?
- ተተኳሪ ፈተናዎች ከፈተና መርሆዎች አኳያ ምን ጠንካራና ደካማ ጎን ይታይባቸዋል?

የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል።

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል።

- ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦችን በመጠቆም አስተዋጽኦ ሊያበረክት መቻሉ፣

- በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት የይዘትን ተገቢነት (Content validity) ማሟላት አለማሟላታቸውን በመለየት በቀጣይ በሚዘጋጁ ፈተናዎች ውስጥ የይዘትን ተገቢነት በተሟላ መልክ ለማቅረብ ማስቻል፣
- ፈተና በትምህርት ሥራ ውስጥ ጉልህ ሚና ያለው በመሆኑ በየፈተናዎቹ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከፈተና መመዘኛ ባህርያት አኳያ የሚታይባቸውን ግድፈቶች አሻሽሎ ለማቅረብ ማገልገል፣

የሚሉት ጥናቱ ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ከ2001—2006 ዓ.ም. ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት (ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች) በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህም የተነሳ ጥናቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት በተሰጡት የስድስት ተከታታይ ዓመታት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ ይወሰናል፡፡ በእነዚህ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው ከሚገኙት የቋንቋ ትምህርት ይዘት ጥያቄዎች ውስጥ በጥናቱ ላይ ትኩረት የተሰጣቸው የሰዋስው ጥያቄዎች ብቻ ናቸው፡፡

ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ አስተማማኝነት ፈተናው ለግለሰብ ወይም ለተመሳሳይ ተማሪዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ተሰጥቶ ሊገኝ በሚችለው የውጤት ተመሳሳይነት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፣ ተተግባሪነት ደግሞ ከፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የዚህ ጥናት ትኩረት አይደሉም፡፡ ጥናቱ ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ በይዘት ተገቢነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ይህ ጥናት በየፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የሰዋስው ጥያቄዎች ከፈተና መርሆዎች አኳያም በሚታይባቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎን ላይ እና በይዘት ተገቢነት ላይ በማተኮር ትንታኔውን አቅርቧል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ተካተዋል፡፡ በመጀመሪያ የቋንቋ ፈተና እና ተያያዥ ጉዳዮች ዳሰሳ ቀርቧል፡፡ ሁለተኛው ክፍል የሰዋስው ምንነትን እና ተዛማጅ ጉዳዮችን ያካተተ ነው፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናታዊ ጽሁፎች የሚዳስሰው ክፍል ነው፡፡

## 2.1. የቋንቋ ፈተና

### 2.1.1. የቋንቋ ፈተና ምንነት

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከሚከናወኑት ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ አንዱ ምዘና ነው፡፡ ምዘና በማስተማር ሂደት ክንውን የማያቋርጥ ተግባር ነው፡፡ ምዘና ለውሳኔ የሚረዳ ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግል መሳሪያ መሆኑን በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል (Thorndike and Hagen 1977፡4፣ Braun and Kanjee 2006፡9)፡፡

በትምህርት ሂደት ውስጥ በመመዘኛነት ከሚያገለግሉ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ፈተና ነው (ሀ.አ.ፈ.ድ. 1994፡9፣ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት 1985፡31፣ Brown 2004፡4፣ Hughes 2003፡5)፡፡ ፈተና የሚዘጋጅበት ቀዳሚው ጉዳይ ተማሪዎች ምን እንዳወቁ መመዘን መሆኑን Heaton (1988፡14) ገልጸዋል፡፡

Brown (2004፡3) ፈተና የክህሎትን፣ የእውቀትን ወይም የተግባርን ባህርያት ለመለካት የሚያስችል ዘዴ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሀ.አ.ፈ.ድ. (1994፡3) ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህሉን በሚገባ እንደተገነዘቡ ለማረጋገጥ የሚረዱ የልዩ ልዩ ጥያቄዎች ስብስብ መሆኑን አመልክቷል፡፡ በዚህም የተነሳ

እንደማንኛው የትምህርት ዓይነት የቋንቋ ፈተናም ተማሪዎች እንዲማሯቸው የተነደፉትን አጠቃላይ እና ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች መሰረት የቋንቋ ትምህርት ክሂሎቻቸውን፣ የሰዋስውና የሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ዕውቀታቸውን ምን ያህል እንዳዳበሩ እና እንደተገነዘቡ ለመፈተሽ የሚያስችል፣ ልዩ ልዩ የጥያቄ ስብስብን የያዘ የመመዘኛ መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.1.2. የቋንቋ ፈተና ዓላማ

የቋንቋ ፈተና ዋነኛው ዓላማ የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት ክሂልም ሆነ የእውቀት ዘርፍ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ መመዘን፣ መፈተሽ ነው፡፡ በቋንቋ ፈተና የተማሪዎች የመናገር፣ የማድመጥ፣ የመጻፍ እና የማንበብ ክሂሎች እንዲሁም የሰዋስው እና የስነ-ጽሑፍ እውቀት ብቃት ይለካል፤ ይፈተሻል፡፡ ከቋንቋ ብቃት ውስጥ አንዱ የሰዋስው እውቀት ብቃት ነው፡፡ የሰዋስው ብቃት የስነ-ምዕላድን (morphology)፣ የአረፍተ ነገርን ስርዓት (sentence-grammar)፣ የስነ-ፍችን (semantics) እና የስነ-ድምፅን (phonology) ብቃት እንደሚያካትት Bachman (1990፡85) Canale and Swain (1980)ን በመጥቀስ ገልጸዋል፡፡

በሰዋስው ትምህርት ይዘት ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የብቃት ደረጃዎች ለመለካት ሲባል የሰዋስው ፈተናዎች ይዘጋጃሉ፤ ይሰጣሉ፡፡ ተማሪዎች የሰዋስው ብቃታቸውን ምን ያህል እንዳዳበሩ መለካት የፈተና ዋና ዓላማ ነው፡፡ በዚህም አማካይነት የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት እውቀት አስመልክቶ ለውሳኔ የሚያበቃ መረጃ ይሰበሰባል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ፈተናዎች የታለመላቸውን ዓላማ ከግብ ማድረስ ይችሉ ዘንድ በጥንቃቄ ሊዘጋጁ እና ብቃታቸውም በየጊዜው ሊፈተሽ ይገባል፡፡

### 2.1.3. የቋንቋ ትምህርትና ፈተና ተዛምዶ

በማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ከቋንቋ ትምህርት በፊት፣ በትምህርቱ ወቅት እና ትምህርቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የቃልም ሆነ የጽሑፍ ጥያቄዎችን

በማቅረብ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ይመዘናሉ፡፡ ከቋንቋ ትምህርቱ በፊት ስለሚማሩት ርዕሰ ጉዳይ አስቀድሞ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው፣ በቋንቋ ትምህርት ወቅት የቋንቋውን ትምህርት ይዘት ምን ያህል እየተከታተሉ እንደሆነ እና የቋንቋው ትምህርት ሲጠናቀቅ ደግሞ የተማሯቸውን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተገነዘቡና እንዳወቁ ለመረዳት በቃል ወይም በጽሁፍ ጥያቄዎች አማካኝነት ይመዘናሉ፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግቡን ምን ያህል እንደመታ ለማወቅ ፈተናን በመጠቀም ምዘና ይካሄዳል፡፡ በቋንቋ ትምህርት የታለመውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ የትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች እንዲማሯቸው ይቀርባሉ፡፡ የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተገነዘቧቸው ለማወቅ ክትትል ይደረጋል፡ ይህም የቋንቋ ትምህርት እና ፈተና ያላቸውን ተዛምዶ ያመለክታል፡፡ የቋንቋ ትምህርት እና ፈተና የማይለያዩ እና የማይነጣጠሉ ተግባራት ናቸው፡፡ የሁለቱንም ግንኙነት አስመልክቶ Heaton (1988፡5) ቋንቋን ማስተማርና መፈተን በጥብቅ የተሳሰሩ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

### 2.1.4. የቋንቋ ፈተና መመዘኛ መስፈርት

ጥሩ ፈተና ለማዘጋጀትም ሆነ ተዘጋጅቶ የቀረበው ፈተና ጥሩ የመመዘኛ መሳሪያ መሆኑን ለመገምገም የሚያስችሉ የተለያዩ የፈተና መመዘኛ መስፈርቶች አሉ፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ፈተናው የተፈለገውን ዓላማ ለማሳካት በተገቢው መንገድ መዘጋጀቱን፣ ከመስፈርቱ አኳያ ተገቢ የመመዘኛ መሳሪያ መሆኑን፣ የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ መዘጋጀቱን ወዘተ. ለማረጋገጥ ያገለግላሉ፡፡

Harmer (2001፡322) ተገቢነት (validity) እና አስተማማኝነት (Reliability) የፈተና መመዘኛ መስፈርቶች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ Bachman and Palmer (1996፡19) እውነተኛነት (Authenticity)፣ ተተግባሪነት (Practicality)፣ አስተማማኝነት (Reliability) እና ተገቢነት (Validity) በማለት የፈተና መመዘኛ

መስፈርቶችን በአራት ከፍለውታል፡፡ Brown (2004፡19) የፈተና መመዘኛ መስፈርቶችን ተተግባሪነት (Practicality)፣ አስተማማኝነት (Reliability)፣ ተገቢነት (Validity)፣ እውነተኛነት (Authenticity) እና ዋሽ ባክ (Washback) በማለት በአምስት ከፍለውታል፡፡ Thorndike and Hagen (1977፡56) በርካታ ዝርዝር የፈተና መመዘኛዎች እንዳሉ በመጥቀስ መስፈርቶቹ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም በተገቢነት፣ በአስተማማኝነት እና በተተግባሪነት ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

በምሁራን አተያይ መስፈርቶቹ አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ተመድበው ባይቀርቡም እንኳ የተለያዩ የፈተና መመዘኛ መስፈርቶች እንዳሉ ተገልጸዋል፡፡ አብዛኞቹ ምሁራን አስተማማኝነት፣ ተተግባሪነት እና ተገቢነት የጥሩ ፈተና መመዘኛ መስፈርቶች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ እነዚህም መስፈርቶች፡-

- አስተማማኝነት (Reliability) — አስተማማኝነት እንደ Bachman and Palmer (1996፡20) አገላለጽ የተዘጋጀው ፈተና በተለያየ ጊዜ በተደጋጋሚ ለግለሰብ ወይም ለቡድን በሚሰጥበት ጊዜ ተመሳሳይ ውጤት ማስገኘት መቻሉን የሚመለከት ነው፡፡
- ተተግባሪነት (Practicality) — ይህ የፈተና መመዘኛ መስፈርት የፈተናውን ዝግጅት እና አስተዳደር ይመለከታል፡፡ ትኩረቱም ከፈተናው ዝግጅት እስከ አሰጣጡ ድረስ ያለውን የጊዜ፣ የአቅም፣ የክንውን፣ የውጤት አሰጣጥ ላይ ነው፡፡
- ተገቢነት (Validity) — ተገቢነት እንደ Alderson et al. (1995፡171)፣ Heaton (1988፡159)፣ Hughes (1989፡22)፣ Fulcher and Davidson (2007፡4)፣ Henning (1987፡89) አገላለጽ ፈተና ተገቢነት አለው የሚባለው መመዘን የሚገባውን ነገር በትክክል መመዘን ሲችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከነዚህ የፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ አስተማማኝነት ፈተናው ለግለሰብ ወይም ለተመሳሳይ ተማሪዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ተሰጥቶ ሊገኝ በሚችለው

የውጤት ተመሳሳይነት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፣ ተተግባሪነት ደግሞ ከፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የዚህ ጥናት ትኩረት አይደሉም፡፡ ይህ ጥናት ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ በተገቢነት ላይ ያተኩራል፡፡

ምሁራን ተገቢነትን በተለያዩ ክፍሎች ከፍለውታል፡፡ የተገቢነትን ዓይነቶች አስመልክቶ በAlderson et al. (1995፡171) አገላለጽ የይዘት ተገቢነት (Rational/content validity)፣ ንድፈ-ሐሳባዊ ተገቢነት (Construct validity) እና ቀመራዊ/መስፈርታዊ ተገቢነት (Emprical/statistical validity) በሚባሉ ሶስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል በማለት ገልጸዋል፡፡ Heaton (1988፡159-162) ተገቢነትን ገጻዊ ተገቢነት (Face Validity)፣ የይዘት ተገቢነት (Content validity)፣ ንድፈ-ሐሳባዊ ተገቢነት (Construct validity) እና ቀመራዊ/መስፈርታዊ ተገቢነት (Emprical/Statistical validity) በማለት በአራት ከፍለውታል፡፡ Hughes (1989፡22-27) ተገቢነትን የይዘት ተገቢነት (Content validity)፣ መስፈርት ተኮር ተገቢነት (Criterion-related validity)፣ ንድፈ-ሐሳባዊ ተገቢነት (Construct validity) እና ገጻዊ ተገቢነት (Face Validity) በማለት በአራት ከፍለውታል፡፡ Fulcher and Davidson (2007፡4) መስፈርት ተኮር ተገቢነት (Criterion-oriented validity)፣ የይዘት ተገቢነት (Content validity) እና ንድፈ-ሐሳባዊ ተገቢነት (Construct validity) በመባል በሶስት እንደሚከፈል ገልጸዋል፡፡

የፈተና ተገቢነት በምሁራን አተያይ መሰረት አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ተከፍሎ አይገኝም፡፡ ይህ ጥናት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት እና አቀራረብ የሚመለከት በመሆኑ የተነሳ ከተገቢነት ዓይነቶች የይዘት ተገቢነትን የሚመለከት ነው፡፡ አንድ ፈተና ሊይዝ የሚገባውን የቋንቋ ትምህርት ይዘት ከየዓይነቱ በተመጣጠነ መልኩ በናሙናነት ካካተተ የይዘት ተገቢነት አለው ማለት ነው፡፡

### 2.1.5. የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች

ፈተና በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚዘጋጅበትን ዓላማ መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የፈተናው ዓይነት፣ የፈተናው ይዘት እና የፈተናው አቀራረብ እንደሚዘጋጀው ፈተና ዓላማ ይወሰናል፡፡ የቋንቋን ፈተና በተመለከተ Bachman and Palmer (1996፡17) በቋንቋ ፈተና ዝግጅት ወቅት ፈተና ለምን ዓላማ እንደሚውል መረዳት አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ Henning (1987፡4) የቋንቋ ፈተና የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳሉት እና የተለያዩ የፈተና ዓይነቶች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ የፈተና ዓይነቶች በተለያየ ክፍል ይመደባሉ፡፡ አመዳደባቸውን እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

#### 2.1.5.1. ከፈተና ዓላማ አኳያ

ፈተና የሚፈለገውን መረጃ እንዲያስገኝ እንደየፈተናው ዓይነት የተፈለገውን የፈተና ዓላማ ለማሳካት ታስቦ ሊዘጋጅ ይገባዋል፡፡ የፈተና ዓይነቶችን አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ ክፍል ከፋፍለዋቸዋል፡፡ ፈተናዎችን በተለያየ ክፍል ከከፋፈሏቸው ምሁራን ውስጥ የሚከተሉትን እናገኛለን፡፡

Henning (1987፡6) የብቃት መለኪያ ፈተና (Proficiency test) ፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Apptitude test) እና የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test) በማለት በሶስት ከፍለዋል፡፡ እንደ Alderson et al. (1995፡11) የምደባ ፈተና (Placement tests)፣ የእድገት መለኪያ ፈተና (Progress tests)፣ የብቃት መለኪያ ፈተና (Proficiency tests)፣ የጥንካሬ እና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic tests) እና የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement tests) በማለት በአምስት ሰፋፊ ክፍሎች እንደሚከፈሉ ገልጸዋል፡፡ Brown (2004፡43) የቋንቋ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Language aptitude tests)፣ የቋንቋ ብቃት መለኪያ ፈተና (Language proficiency tests)፣ የምደባ ፈተና (Placement tests)፣ የጥንካሬ እና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic tests) እና የችሎታ መለኪያ ፈተና

(Achievement tests) በማለት በአምስት ሲከፍሉት፣ Harmer(2001፡321)፣ Heaton (1988፡171) ደግሞ የፈተና ዓይነቶችን የብቃት መለኪያ ፈተና (Proficiency test)፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Apptitude test)፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic test) እና የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement/Attainment test) ተብለው በአራት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ Hughes (1989፡9) የብቃት መለኪያ ፈተና (Proficiency test)፣ የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test)፣ የምደባ ፈተና (Placement tests)፣ የጥንካሬ እና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic tests) በማለት በአራት ከፍለውታል፡፡

የቋንቋ ፈተናዎች በምሁራን አከፋፈል መሰረት አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ተከፍለው ባይገኙም እንኳ በተለያዩ ክፍሎች ተመድበው ይገኛሉ፡፡ የፈተና ዓይቶችን አስመልክቶ በአብዛኞቹ ምሁራን የተጠቀሱትን እንደሚከተለው በተወሰነ መልኩ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

- **የብቃት መለኪያ ፈተና (Proficiency test)** — ይህ የፈተና ዓይነት ግለሰቡ ወይም ተማሪው አስቀድሞ ምንም ዓይነት ስልጠና ወይም ትምህርት ከመውሰዱ በፊት በቋንቋው ላይ ያለውን አጠቃላይ ብቃት ለመመዘን የሚያገለግል የፈተና ዓይነት ነው፡፡ እንደ Henning (1987፡6) አገላለጽ ይህ የፈተና ዓይነት በታቀደው የትምህርት ዓላማ ወይም ይዘት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ሳይሆን ግለሰቡ (ተፈታኙ) አስቀድሞ ባለው የቋንቋ ችሎታ ላይ የሚመሰረት ፈተና ነው፡፡
- **የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Apptitude test)** — ይህ የፈተና ዓይነት ተማሪው ለሚቀጥለው ተግባር ወይም ትምህርት ያለው ችሎታ ምን ያህል እንደሆነ በቅድሚያ ለመተንበይ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎችን ለተለያዩ የሙያ ስልጠናዎች ለመምረጥ፣ በተለያዩ ሙያዎች ያላቸውን ችሎታና ፍላጎት ለማረጋገጥ የሚሰጥ የፈተና ዓይነት ነው (Henning 1987፡6)፡፡

- **የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና** (Diagnostic test) — ይህ የፈተና ዓይነት መምህራን የተማሪዎችን ችግር ለመረዳት የሚያገለግል ነው (Brown 2004፡47)። መምህራን ለተማሪዎቻቸው በተለያየ ጊዜ የሚሰጧቸውን ፈተናዎች የሚያካትት ሲሆን ተማሪዎቹ የተማሩትን ትምህርት መረዳት አለመረዳታቸውን፣ የትኛውን በአግባቡ እንደተገነዘቡ እና የቱጋ ደግሞ ችግር እንዳለባቸው የሚጠቁም የፈተና ዓይነት ነው (Alderson et al. 1995፡12፣ አለም 1992፡72)።

- **የችሎታ መለኪያ ፈተና** (Achievement/Attainment test) — ይህ የፈተና ዓይነት በተነደፈው (በተቀረጸው) የቋንቋ ትምህርት ዓላማ መሰረት ተማሪዎች አስቀድመው የተማሩትን ትምህርት መነሻ በማድረግ የሚዘጋጅ ነው። Alderson et al. (1995፡12) በመርሀ ትምህርቱ፣ በመማሪያ መጽሐፉ መነሻነት ተማሪዎች አስቀድመው የተማሩትን ትምህርት መነሻ በማድረግ የሚዘጋጅ ፈተና መሆኑን ይገልጻሉ።

የችሎታ መለኪያ ፈተና መርሀ ትምህርቱን፣ የመማሪያ መጽሐፉን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህሉን እንደጨበጡ ወይም የትምህርቱ ዓላማ ምን ያህል ግቡን እንደመታ ለመረዳት የሚያስችለውን መረጃ ለማግኘት ጥቅም ላይ የሚውል የፈተና ዓይነት ነው።

Heaton (1988፡172) የችሎታ መለኪያ ፈተና የተቀረጸውን መርሀ ትምህርትና ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት የተማሩትን መሰረት በማድረግ ለሁለተኛ ደረጃ መግቢያ፣ ለሁለተኛ ደረጃ ማጠቃለያ የሚዘጋጀውን ፈተና እንደሚያካትት ገልጸዋል። ከመማር በኋላ ማለትም በየክፍል ደረጃው የሚገኙ መምህራን የሚሰጧቸው የክፍል ፈተናዎች፣ የ10ኛ እና የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎች ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከተማሩና ካጠናቀቁ በኋላ የሚሰጡ የመማር ውጤት መለኪያ ፈተናዎች በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

እንደ Brown (2004፡48) አገላለጽ በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ የሚካተቱት ጥያቄዎች የትምህርቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች ሊመዝኑ የሚችሉ ጥያቄዎች በጥንቃቄ ተመርጠው መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመርሀ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከተካተቱት የትምህርት ይዘቶች ውስጥ በርካታ ክፍለ ጊዜ የተሰጣቸውን እና ጥቂት ክፍለ ጊዜ ተሰጥቷቸው እንዲማሯቸው የተደረጉትን ይዘቶች በመለየት፣ የጥያቄዎችን መጠን (ብዛት) በመወሰን ይዘቶችን ሊወክሉ የሚችሉ የጥያቄ ናሙናዎችን ማካተት ተገቢ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ለየይዘቶቹ የተሰጠውን የትኩረት ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት በፈተና ውስጥ ተገቢውን የጥያቄ መጠን ማካተት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግ ያስችል ዘንድ የፈተና እቅድ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

የፈተና እቅድ ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት በፈተናው ውስጥ መካተት ያለባቸውን ይዘቶች ምን ምን እንደሆኑና ምን ያህል ጥያቄዎች ከየይዘቱ ውስጥ ተመርጠው መካተት እንዳለባቸው ለመወሰን ያገለግላል፡፡ Heaton (1988፡13) ማንኛውም ፈተና ከመዘጋጀቱ በፊት የፈተና አውጪው አካል የፈተና ዕቅድ ማዘጋጀት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

በፈተና ዕቅድ አወጣጥ ላይ ትኩረት ከሚሰጣቸው ዋና ዋና ነገሮች መካከል የትምህርቱ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የትምህርቱ ዋና እና ንዑሳን ይዘቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በፈተና እቅዱ ውስጥ ለማካተት ህጋዊነት ያላቸውን የትምህርት ሰነዶች ማለትም ሥርዓተ ትምህርት፣ መርሀ ትምህርት፣ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያ፣ የመምህሩ ዓመታዊ እና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ለፈተና ዕቅድ አስፈላጊውን መረጃ ለማሰባሰብና ለማደራጀት የሚያገለግሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው (ሀ.አ.ፈ.ድ. 1994፡51—52) ፡፡

### 2.1.5.2. ከሚተገበርበት ወቅት አኳያ

ይህ የፈተና ዓይነት አከፋፈል መሰረት የሚያደርገው በማስተማር ሂደት ክንውን ጊዜ ፈተናው የሚሰጥበትን ጊዜ (ወቅት) ነው፡፡ Brown (2004፡6) አብዛኛውን ጊዜ በማስተማር ሂደት በተከታታይ የሚሰጠው የምዘና ዓይነት ሂደታዊ ምዘና (Formative Assessment) እንደሚባልና በኮርሱ ወይም በትምህርቱ ማጠናቀቂያ ላይ የሚሰጠው የምዘና ዓይነት ደግሞ የማጠቃለያ ምዘና (Summative Assessment) ተብሎ እንደሚጠራ ገልጸዋል፡፡ በማስተማር ሂደት ክንውን እነዚህን ሁለት የፈተና ዓይነቶች ማለትም ሂደታዊ ፈተና ትምህርቱ እየተከናወነ እያለ በቃል፣ በክፍል እና በቤት ስራ መልመጃ፣ በክፍል የሙከራ ፈተናዎች እና በመሳሰሉት የመለኪያ ዘዴዎች አማካኝነት በሂደት የሚከናወን በመሆኑ እና የማጠቃለያ ፈተና ደግሞ በመንፈቀ-ዓመቱ መጨረሻ፣ በዓመቱ መጨረሻ ወይም የአንድ ትምህርት ኮርስ ሲጠቃለል የሚሰጡ ናቸው፡፡ ሁለቱም የፈተና ዓይነቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለመለካት እና ለውጤታቸው ዋጋ ለመስጠት የሚያገለግሉ የምዘና ዓይነቶች ናቸው፡፡

### 2.1.5.3. ከአቀራረብ ስልት አኳያ

የፈተና ዓይነቶች ከማቅረቢያ ስልት አኳያ በሁለት ይከፈላሉ ፡፡ እነሱም ገለጻ ተኮር (Subjective Test) እና ምርጫ ተኮር (Objective Test) ፈተና ተብለው በሁለት ዐቢይ ክፍሎች ይመደባሉ (Bachman 1990፡79)፡፡

የቋንቋ ፈተናዎች በገለጻ ተኮር እና/ወይም በምርጫ ተኮር የጥያቄ አቀራረብ ስልቶች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ገለጻ ተኮር የጥያቄ አቀራረብ ስልት እንደየፈተናው ዓይነት ለጥያቄዎቹ አጭር መልስ በመስጠት፣ ማጠቃለያ በመስጠት፣ ትንታኔ በማቅረብ ወዘተ. ምላሽ የሚሰጥበት የፈተና ዓይነት ነው፡፡

ምርጫ ተኮር የጥያቄ አቀራረብ ስልት ደግሞ በመምረጥ ምላሽ የሚሰጥበት የፈተና ዓይነት ነው (Henning 1987፡4)፡፡ በምርጫ ተኮር የጥያቄ አቀራረብ

ስልት ውስጥ እውነት ሐሰት፣ ማዛመድ፣ ቅደም ተከተልን ማስተካከል፣ የምርጫ ጥያቄዎች ወዘተ. ይገኙበታል።

በገለጻ ተኮርም ሆነ በምርጫ ተኮር የሚቀርቡት ፈተናዎች የራሳቸው የሆነ ጠንካራ እና ደካማ ጎን አላቸው። የፈተና አዘጋጁ ፈተና የታቀደለትን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ እንዲያሳካ፣ በፈተና የሚገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት የየፈተና ዓይነቶችን ጠንካራ እና ደካማ ጎን፣ የፈተና ጥያቄዎችን ያቀራረብ ስልትና ባህርያት በመረዳት ተገቢ የመመዘኛ መሳሪያ ማዘጋጀት ይኖርበታል።

የምርጫ ተኮር የጥያቄ አቀራረብ ስልት የቋንቋን ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች በስፋት ከመወከላቸውም ባሻገር ፈተናውን በቀላሉ ለማረም አመቺ ነው። በዚህ የፈተና ዓይነት የፈተናው ውጤት የማይለዋወጥ እና አስተማማኝ በመሆኑ የተነሳ በምዘና መሳሪያነት ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ጥናት የምርጫ ተኮር የጥያቄ አቀራረብ ስልት በሆነው በምርጫ ጥያቄ (Multiple-Choice Item) ላይ የሚያተኩር ነው።

የምርጫ ጥያቄ ከተሰጡት አራት ወይም አምስት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ የሚመለስ ነው (Weir 2005:62)። የምርጫ ጥያቄ ከሌሎች የጥያቄ ዓይነቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውና በስፋት የተማሪዎችን ችሎታ ለመገምገም የሚያገለግል መሳሪያ ነው (Heaton 1988:27)። Mulu and Daniel (2005:65—66) ይህ የጥያቄ አቀራረብ ስልት ጠለቅ ያለ ወይም ከፍተኛ የማሰብ ክህሎትን የሚጠይቁ ባህርያትን የመመዘን ብቃቱ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

የምርጫ ጥያቄ ግንድ (Stem)፣ ትክክለኛ መልስ (Correct answer) እና አሳሳቾች (Distractors) የሚባሉ ሶስት ክፍሎች አሉት (Brown 1996:54፣ Chesla 2002:19)። ግንድ የጥያቄው ዋና ክፍል ሲሆን ቀጥተኛ በሆነ አጠያየቅ ወይም ባልተሟላ ዐረፍተ-ነገር ሊቀርብ ይችላል። አማራጭ መልስ ለጥያቄው

ወይም ለችግሩ የመፍትሄ ሀሳቦችን (ምላሾችን) የያዘው ክፍል ነው፡፡ የአማራጮች ቁጥር አብዛኛውን ጊዜ አራት ወይም አምስት ሊሆን ይችላል፡፡ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አንዱ ትክክለኛ መልስ ወይም ቁልፍ መልስ ሲሆን ለጥያቄ ትክክለኛ መልስ ያልሆኑት ደግሞ አሳሳች መልስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ አሳሳች መልስ የተፈታኞቹን ሀሳብ፣ ትኩረት በመሳብ እንዲያመዛዝኑ፣ እንዲመራመሩ የሚያደርግ ክፍል ነው (Brown 1996፡54)፡፡

Mulu and Daniel (2005፡71) አንድ የምርጫ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ሊኖረው በሚችል መልኩ መቀረጽ እንዳለበት እና አሳሳች መልሶችም ልክ እንደትክክለኛው መልስ ሆነው መቅረብ እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

የምርጫ ጥያቄ አቀራረብ ስልት የራሱ የሆነ ጠንካራ እና ደካማ ጎን አለው፡፡ Hughes (1989፡59-62)፣ Mulu and Daniel (2005፡67—68)፣ ሀ.አ.ፈ.ድ. (1994፡ 79-80) በምርጫ ጥያቄዎች ላይ የሚታዩትን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አስመልክቶ ያሰፈሯቸውን ነጥቦች መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### ሀ. የምርጫ ጥያቄ ጠንካራ ጎን

- ቀላልና ከፍተኛ የማሰብ ክህሎትንና ችሎታን የመመዘን ብቃት አለው፡፡
- የመለየት፣ የመተርጎም፣ የማጠቃለልና ችግሮችን የመፍታት ችሎታን ለመገምገም ያስችላል፡፡
- ከተሰጡት አራት ወይም አምስት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ ለመምረጥ ስለርዕሰ-ጉዳዩ ወይም ጽንሰ-ሀሳቡ በቂ እውቀትና ግንዛቤን ስለሚጠይቅ በግምት (በጭፍን) የመመለስ እድልን ይቀንሳል፡፡
- የምርጫ ጥያቄ ሰነፍና ጎበዝ ተማሪን የመለየት ብቃቱ ከፍተኛ ነው፡፡ አንድ ተማሪ በቂ ዝግጅትና ግንዛቤ ከሌለው ከአራት ወይም አምስት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ የመምረጥ ችሎታው

ዝቅተኛ ይሆናል፤ ኀበዙ ተማሪ ግን ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል በማስተዋል፣ በማመዛዘን ምላሽ ይሰጣል።

- እርማቱ ሙሉ በሙሉ ተጨባጭ፣ ውጤቱም አስተማማኝ ነው።
- በርካታ ይዘቶችን ለመዳሰስ እና ለመገምገም ያስችላል።
- ፈተናውን ባጭር ጊዜ ውስጥ አርሞ ውጤቱን መግለጽ ያስችላል።

### ለ. የምርጫ ጥያቄ ደካማ ጎን

- የተማሪዎችን የማደራጀት፣ አቀነባብሮ የመጻፍ ወይም የማቅረብ ችሎታን ለመገምገም አያስችልም።
- በግምት ሊመለስ ስለሚችል የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ለመገምገም አስቸጋሪ ነው።
- የምርጫ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት አስቸጋሪ እና ብዙ ጊዜን ይፈጃል። አራት ወይም አምስት የተቀራረቡ አማራጭ መልሶችን ለአንድ ጥያቄ መፍጠር አስቸጋሪ ነው።
- ጥያቄውን ለማዘጋጀት ከሌሎቹ በምርጫ ከሚመለሱ የፈተና ዓይነቶች ይልቅ የተሻለ ችሎታን ስለሚጠይቅ በመምህሩ/ርቷ የምርጫ ጥያቄ የማውጣት ክህሎት ደረጃ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።
- ተፈታኞች ተኮራርጀው እንዲሰሩ በር ይከፍታል።

ባጠቃላይ እንደማንኛውም የጥያቄ ዓይነት በምርጫ ጥያቄ ላይ ከሚታዩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ውስጥ ከላይ የቀረቡት ተጠቃሽ ናቸው። በመሆኑም የምርጫ ጥያቄ ሲዘጋጅ የተፈለገውን መረጃ እንዲያስገኝ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## 2.1.6. የቋንቋ ፈተና ጥያቄ ትንተና (Item analysis)

የቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የቋንቋ እውቀት ደረጃ ለመለካት የሚያስችል የልዩ ልዩ ጥያቄዎች ስብስብ ነው። በቋንቋ ፈተና ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች ተካተው

ይገኛሉ። በቋንቋ ፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙት ጥያቄዎች የፈተናው መሰረታዊ ክፍሎች ናቸው። Brown (1996፡49) የፈተና ጥያቄዎች (Test Item) አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ የፈተና አነስተኛ ክፍሎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

የፈተናን መሰረታዊ ክፍሎች (ጥያቄዎች) ለማዘጋጀትም ሆነ ለማሻሻል ወይም ለመከለስ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ አንዱ የፈተና ጥያቄ ትንተና ነው። የጥያቄ ትንተና በፈተናው ውስጥ የሚገኙትን ጥያቄዎች ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚካሄድ ስርዓታዊ ግምገማ እንደሆነ Brown (1996፡50) ገልጸዋል። የጥያቄ ትንተና የተሻሉ ወይም ጥሩ የፈተና ጥያቄዎችን ለመምረጥና ተገቢውን ፈተና ለማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

የፈተና ጥያቄዎች ከክብደት እና ቅለት፣ ከፈተናው ውጤት፣ ከአሳሳቾች ወዘተ. አኳያ ሊተነተኑ ይችላሉ። ይህ ጥናት የምርጫ ጥያቄዎችን የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን ጥያቄዎቹን ከፈተና መርሆዎች አንጻር ምን እንደሚመስሉ ይመለከታል።

በምርጫ ጥያቄ ዝግጅት ወቅት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ አጠቃላይ መመሪያዎች ወይም መሰረታዊ መርሆዎች አሉ። የፈተና መርሆዎችን አስመልክቶ Brown (1996፡54)፣ ሀ.አ.ፈ.ድ. (1994፡61—62) ባሰፈሯቸው ነጥቦች መሰረት እንደሚከተለው ቀርበዋል። እነሱም፡-

- በፈተናው ውስጥ ተካተው የሚገኙት ጥያቄዎች ሊመዘን የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ ወይም የባህሪ ለውጥ መሠረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- ተማሪዎች በግምት ምላሽ እንዳይሰጡ የማመዛዘን፣ የመመራመር ችሎታቸውን እንዳይቀንስ አላስፈላጊ ፍንጭ ሰጭ (ስነ-ድምጻዊ፣ ስነ-ምዕላዳዊ የመሳሰሉት) ነገሮች መወገድ ይኖርባቸዋል (Brown 1996፡55)።

- አሳሳቾቹ እንደትክክለኛው መልስ የተፈታኙን ትኩረት በሚስብ መልኩ ሊቀረጹ ይገባቸዋል፡፡ ምክንያቱም የጥያቄውን ዋና ክፍልና ትክክለኛውን መልስ እና ሁለቱን አሳሳቾች በቀላሉ መጻፍ ሲቻል አራተኛውን አሳሳች ምላሽ መጻፍ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል Brown (1996፡55) ይገልጻሉ፡፡
- በምርጫ ፈተና ጥያቄ ውስጥ አላስፈላጊ ድግግሞሽ ሊኖር አይገባም፡፡ በምርጫ ጥያቄ አማራጭ መልሶች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉትን ድግግሞሾች በቀላሉ በዋናው የጥያቄ ክፍል ማካተት ይቻላል (Brown 1996፡56)፡፡
- ትክክለኛው መልስ ተዘበራርቆ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ትክክለኛው መልስ ተመሳሳይ አካሄድን ከተከተለ ተፈታኙ ቀሪዎችን ጥያቄዎች በዚያ ቅደም ተከተል በቀላሉ በመገመት እንዲመልስ እድል ስለሚሰጥ የማመዛዘን፣ የመመራመር ችሎታውን ይቀንሳል፡፡
- "ሁሉም መልስ ናቸው"፣ "ሁሉም መልስ አይደሉም"፣ "ሀ እና ለ ብቻ ትክክለኛ መልስ ናቸው" የሚሉ አማራጮችን ማስወገድ፡፡ መካተትም ካለባቸው በቀረቡት አማራጮች ላይ የበለጠ እንዲያመዛዝኑ፣ ለተወሰነ ዓላማ ሲባል ካልሆነ በስተቀር መጠቀም አይመከርም (Brown 1996፡57)፡፡
- ጥያቄው አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ ሊኖረው ይገባል፡፡
- አሻሚ ሀሳቦችን፣ አገላለጾችን፣ አረፍተ ነገሮችን ማስወገድ፡፡
- አፍራሽ እና ሁለት አፍራሽ አገላለጾችን ማስወገድ፡፡ አፍራሽ አገላለጾች በጥያቄው ውስጥ መካተት ካለባቸው ከሌሎች ቃላት እና ሐረጋት ጎላ ተደርገው ሊጻፉ ወይም ሊሰመርባቸው ይገባዋል፡፡
- በአንድ ጥያቄ ላይ የቀረበው ይዘት ለሌላው ጥያቄ ምላሽ ፍንጭ ሰጭ መሆን የለበትም፡፡
- ሁሉም የጥያቄ ክፍሎች (ዋናው ጥያቄ እና አማራጭ መልሶች) በአንድ ገጽ ላይ መጠቃለል ይኖርባቸዋል፡፡

- የፈተና ጥያቄዎቹ የትምህርት ይዘቶችን ሊወክሉ የሚችሉትን ጥያቄዎች ማካተት ይገባቸል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት መሰረታዊ ነጥቦች ተገቢውን የፈተና ጥያቄ ለማዘጋጀት፣ ፈተናው መመዘን የሚገባውን የክሂልም ሆነ የእውቀት ዘርፍ በትክክል እንዲመዝን፣ በፈተናው የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችለውን ጥሩ ፈተና ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ በፈተና ዝግጅት ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች ውስጥ ተጠቃሽ በመሆናቸው ለፈተና ጥያቄዎች ትንተናም ሆነ ለጥሩ ፈተና ዝግጅት አስፈላጊ መርሆዎች ናቸው፡፡

## 2.2. የሰዋስው ትምህርት እና ፈተና ይዘት

### 2.2.1. የሰዋስው ምንነት

የቋንቋ ዋነኛው አገልግሎት ማግባባት ነው፡፡ የመግባባት ሂደት ይከናወን ዘንድም ቢያንስ ሁለት ሰዎች ሊኖሩ ይገባል — የመልእክት አቀባይና ተቀባይ፡፡ ሁለቱም ሰዎች በቋንቋ አማካይነት ለመግባባት የሚጠቀሙበትን ቋንቋ ስርዓት ማወቅ፣ ለቋንቋው ስርዓትም መገዛት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም የሚተላለፈውን መልእክት ግልጽ እና ቀላል በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ ያስችላል፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በቋንቋ ትምህርት የሚማሩትንና የሚጠቀሙትን ቋንቋ ባህሪ ጠንቅቀው እንዲያውቁ፣ በቋንቋው አማካይነት መልእክታቸውን በአግባቡ ለማስተላለፍ ያስችላቸው ዘንድ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡ ለመሆኑ ሰዋስው ስንል ምን ማለታችን ነው?

የሰዋስው ምንነትን አስመልክቶ Murthy (2006፡3) ሰዋስው ቋንቋን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና የቋንቋ ጥናት ክፍል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህ ብያኔ ሥነ-ልሳን ከሚለው ቃል ጽንሰ-ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ያመለክታል (Todd 1987:6)፡፡ ሰዋስው ቋንቋን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ

የሚያጠና ሲል ሰዋስው እንደማንኛውም የጥናት መስክ ሳይንሳዊ የሆነ የአጠናን ሂደትን የሚከተል የቋንቋ ጥናት ክፍል መሆኑን ያመለክታል።

ጌታሁን (1990፡iv) ሰዋስው የሚለውን ቃል በተመለከተ ሁለት አሻሚ የሆኑ ፍቺዎችን ይዞ የሚገኝ መሆኑን ይገልጻል። አንደኛው የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ዕውቀት የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋን ስርዓትና መዋቅር የሚመለከት ነው።

የተለያዩ ምሁራን ሰዋስው የቋንቋን ስርዓት የሚመለከት ክፍል መሆኑን ይገልጻሉ (Brinton 2000፡8፣ ባየ 1987፡8)። በያንዳንዱ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙት ድምጾች፣ ቃላት፣ ሐረጋት እና አረፍተ ነገሮች አመሰራረት የየራሳቸው ስርዓት አላቸው። ሰዋስው የቋንቋን ስርዓት የቋንቋ መሰረት ከሆነው ድምጽ ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ደረጃ ያለውን የቋንቋ የስርዓት ጥናት የሚመለከተው ክፍል ነው።

### 2.2.2. የሰዋስው ትምህርት ይዘት

"የቋንቋ ጥናት በአጠቃቀም፣ በለውጥ፣ በስርኣት ወዘተ. ላይ ሊያተኩር ይችላል። ሰዋስው ከቋንቋ ጥናቶች ውስጥ ስርኣትን የሚመለከት ክፍል ነው።" (ጌታሁን 1990፡iv)። ሰዋስው በጥናቱ የቋንቋን የድምጽ አፈጣጠርና አቀነጃጀት፣ የቃላትና የሐረጋት አመሰራረት፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር ወዘተ. የስርዓት ይዘት ላይ ያተኩራል።

የቋንቋን ስርዓት ለማመልከት ባየ (1987፡322) የቋንቋ መሰረት ከሆነው ድምጽ አንስቶ እስከ አረፍተ ነገር ድረስ ያለው ክፍል አንዱ ካንዱ ጋር ተያይዞና በስርዓት ተዋቅሮ መገኘቱን ለማመልከት በቤት አሰራር መስለውታል። ይኸውም አንድ ቤት ሲሰራ መሰረት፣ ግድግዳና ጣሪያ ሦስቱም ተደጋግፈው የተሟላ ቤትን እንደሚያስገኙ ሁሉ በቤት የተመሰለው አረፍተ ነገርም መሰረቱ ድምጽ እንደሆነ፣ ድምጾች ተቀናጅተው ምዕላድንና ቃላትን፣ ቃላትም ተቀናጅተው ሐረጋትን፣ ሐረጋትም ተዋቅረው የተለያዩ አረፍተ ነገሮች ሊመሰረቱ

እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ሰዋስው በቋንቋ ውስጥ በሚገኙት ድምጾች፣ ቃላት፣ ሐረጋት፣ አረፍተ ነገሮች ላይ ያተኩራል (Murthy 2006፡3)፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዋነኛው ዓላማ እንደ ማረው (2003፣39) አገላለጽ የተማሪዎችን የመግባባት ችሎታ ማሳደግ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የሰዋስው ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎቹ የሚማሩትን ቋንቋ አጠቃቀም (ክህሎት) እና ስርዓት ጠንቅቀው ሊያውቁ በሚያስችላቸው መልክ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ባየ (1987፣10) እና ጌታሁን (1990፣V) የቋንቋ ትምህርት በክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን በስርዓት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ተማሪው የተሟላ የቋንቋ እውቀት ይኖረው ዘንድ ሁለቱንም (ክህሎትን እና ስርዓትን) አጣምሮ ማስተማር እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡ የተማሪዎችን የቋንቋ እውቀት በተሟላ መልኩ ማሳደግ ይቻል ዘንድ የሰዋስው ትምህርቱ የክህሎትና የስርዓት እውቀት ደረጃቸውን ሊያጎለብትና ችሎታቸውን ሊያዳብር በሚችል መልኩ ሊቀርብ እና በየመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የመግባባት ችሎታ ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ ሊቀረጹ ይገባል፡፡ ይህም በተገቢው መንገድ ተዘጋጅቶ በቀረበው የሰዋስው ትምህርት ዓላማ እና ይዘት መነሻነት ተማሪዎቹ የሰዋስው እውቀታቸውን ምን ያህል እንዳዳበሩ ለመመዘን የሚያስችሉትን ጥያቄዎች ለማዘጋጀት እና በፈተናውም ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ያግዛል፡፡

የሰዋስው ትምህርት ዓላማ የሰዋስው እውቀትን በማዳበር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ሰዋስው የቋንቋ ስርዓትን የሚመለከት በመሆኑ ከትምህርቱ ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ለተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ስርዓት ማሳወቅ ነው፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ባየ (1987፣9) አንዱ የሰዋስው ትምህርት ዓላማ የአንድን ቋንቋ ስርዓት ማሳየት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሰዋስው ትምህርት የተቀረጸለትን ዓላማ ለማሳካት ያስችል ዘንድ የቋንቋውን የድምጽ፣ የምዕላድ፣ የቃል፣ የሐረግ፣ የአረፍተ ነገርና የመሳሰሉትን የሚያመለክቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቋንቋ መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡

### 2.2.3. የሰዋስው ፈተና ይዘት

በማስተማር ሂደት ውስጥ አራቱን የቋንቋ ትምህርት ክሂሎች፣ የሥነ-ጽሑፍ እና የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር ሲባል በየክፍል ደረጃው መርሀ ትምህርቶች፣ የመማሪያ መጻሕፍት ተዘጋጅተውና በተግባር ላይ ውለው ይገኛሉ፡፡ የሰዋስውን ትምህርት ዓላማ ለማሳካት በየመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተለያዩ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡

ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ይዘትነት እንዲማሩ በተነደፈው መርሀ ትምህርት እና መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ይዘቶች መፈተን የችሎታ መለኪያ ፈተና ተግባር ነው፡፡ የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች አስቀድመው በየክፍል ደረጃቸው በተቀረጹት መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት መነሻነት የተማሯቸውን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ነው፡፡

ሰዋስው የቋንቋን ስርዓት የሚመለከት ክፍል ነው፡፡ ይህ የቋንቋን ስርዓት የሚመለከተው ክፍል በውስጡ ምን ምን ይዘቶችን ያካትታል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ በየመርሀ ትምህርቱ እና በየመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሚካተቱትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ለመወሰንና ለማካተት ይረዳል፡፡ ለተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በትምህርትነት ከቀረቡ በኋላ የፈተና ጥያቄዎችን በመርሀ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጻሕፍቱ በመታገዝ ተገቢውን ጥያቄ ለማዘጋጀት ይረዳል፡፡

ባየ (1987፣8) ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ስርዓት ከድምጽ አሰካኩ አንስቶ እስከ ሀረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው ከሚማሩት ቋንቋ ድምጽ አንስቶ እስከ አረፍተ-ነገር አመሰራረት ስርዓት ድረስ ያለውን የቋንቋ ስርዓት እንዲማሩ በየመርሀ ትምህርቱም ሆነ በየመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡ በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ የሚካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በመርሀ

ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ሊወክሉ የሚችሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

Heaton (1988፥9) የሰዋስው ፈተና ተገቢውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ እና የመዋቅር አጠቃቀም ችሎታን መለካት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የሰዋስው ፈተና ዓላማ የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት መመዘን ነው፡፡ የሰዋስው ፈተና ትኩረትም በተነደፈው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ መሰረት የሰዋስው ይዘት ያላቸውን ጥያቄዎች በመጠቀም ተማሪዎች የተማሩትን የቋንቋ ስርዓት ምን ያህል እንደተገነዘቡ፣ የሰዋስው እውቀት ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ መለካት ነው፡፡

ባጠቃላይ በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ የሚካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ተማሪዎች በየክፍል ደረጃቸው በተቀረጸላቸው መርሀ ትምህርት እና መማሪያ መጽሐፍ መሰረት አስቀድመው የተማሯቸውን ይዘቶች መነሻ በማድረግ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ የፈተና ጥያቄዎቹም ሲዘጋጁ በ 2.1.4. ስር የተገለጹት የቋንቋ ፈተና መመዘኛ መስፈርቶች እና በ 2.1.6. ስር የሰፈሩት የፈተና መርሆዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

ከጥናቱ ርዕስ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ይገኛሉ፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት ከተሰሩት ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ በለጠ ያዕቆብ (1995) በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ፈተና ላይ፣ ፀጋዬ ግርማ (1997) እና ተስፋ አከለ (2000) በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ በተሰጡ ተከታታይ እና የማጠቃለያ ፈተናዎች ላይ የሰሯቸው ጥናቶች ይገኛሉ፡፡

በክልል ደረጃ ለ8ኛ ክፍል በተሰጡት ክልላዊ ፈተናዎች ላይ ከተሰሩት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ የመሠረት አለማየሁ (2005)፣

የሙሉፀሐይ ገነት (2005)፣ የታለጌታ ይመር (2005) እና የአበበች ገብሩ (2004) ጥናቶች ይገኙበታል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ እና ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ በተሰጡት ፈተናዎች መነሻነት ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት ከተሰሩት ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ የትንሳኤ ብርሐኔ (1988)፣ የወንድማገኝ አደም (2005) እና የጠጅቱ በሬቻ (1999) ጥናታዊ ጽሁፎች ይገኙበታል፡፡

ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጁት ፈተናዎች ላይ ከተሰሩት ስራዎች ውስጥ ትንሳኤ (1988) "የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት፡፡" በሚል ርዕስ በቀድሞው የትምህርት ፖሊሲ ለ12ኛ ክፍል ተፈታኞች የተሰጡትን ብሔራዊ ፈተናዎች መነሻ በማድረግ የሰሩት ጥናት ሲሆን የአጥኚው ጥናት ከትንሳኤ (1988) ጥናት የሚለየው ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ (ለ10ኛ ክፍል) ማጠቃለያነት በተሰጡ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ ማተኮሩ፣ በፈተናዎቹ ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ላይ መመስረቱ እና የጊዜ ልዩነቶች ናቸው፡፡

ወንድማገኝ (2005) "ከ2001—2004 ዓ.ም. የተሰጡ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገር አቀፍ እና ሞዴል ፈተናዎች ይዘትና አቀራረብ ንጽጽር በጋምቤላ ክልል በሁለት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መነሻነት፡፡" በሚል ርዕስ ያካሄዱት ጥናት ሲሆን አጥኚው ከ2001—2004 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰጡትን የአማርኛ ፈተናዎችንና በጋምቤላ ክልል በተመረጡ ሁለት ትምህርት ቤቶች የተሰጡትን ሞዴል ፈተናዎችን በመጠቀም ባካሄዱት ንጽጽራዊ ጥናት መሠረት በ2004 ዓ.ም. በጄይን ትምህርት ቤት የተሰጠው ሞዴል ፈተና እና በ2001 እና በ2003 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት የተሰጡት ፈተናዎች የአቀራረብ ችግር ያልታየባቸው መሆኑን፣ በቀሪዎቹ ዓመታት የተሰጡት የሁለቱ ፈተናዎች እና በትንሿ ሜጢ ትምህርት ቤት ተዘጋጅተው የተሰጡት ሞዴል ፈተናዎች ሁሉም የአቀራረብ ችግር የታየባቸው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ጠጅቱ (1999) “በአዲስ አበባ ከተማ በግል እና በመንግስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገር አቀፍ ፈተና ውጤቶች ንጽጽር፡፡” በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት የ1997 ዓ.ም. እና የ1998 ዓ.ም. የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን፣ የጽሑፍ መጠይቅን እና የፈተና ዉጤቶችን በመጠቀም ባደረጉት ጥናት የግል ትምህርት ቤቶች ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ጋር ሲነጻጸሩ የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን አመልክተዋል፡፡

ይህ ጥናት በፈተና ላይ ማተኮሩ ከላይ ከተጠቀሱት ከሁሉም ጥናቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ ጥናቱ ከወንድማገኝ እና ከጠጅቱ ጥናቶች ጋር የሚያመሳስለው ደግሞ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት (ለ10ኛ ክፍል) በተሰጡት ፈተናዎች ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከወንድማገኝና ከጠጅቱ ጥናቶች የሚለየው ከ2001 እስከ 2006 ዓ.ም. ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያነት በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ላይ በመመስረት ትንታኔ ማቅረቡ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሏል፡፡ በአቀራረቡም ገላጭ የምርምር ስልትን በመጠቀም የሰዋስው ጥያቄዎችን ይዘትና አቀራረብ ከፈተና መርሆዎች፣ ከመርሀ ትምህርቱ እና ከመማሪያ መጻሕፍቱ አኳያ በመመርመር ተንትኗል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች በአሃዝ የቀረቡ በመሆናቸው የተነሳ መጠናዊ የምርምር ዘዴም ተግባራዊ ሆኗል፡፡

## 3.1. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት ውስጥ ዋና የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉት ከ2001—2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያነት ተዘጋጅተው የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ናቸው፡፡

በተጨማሪም የችሎታ መለኪያ ፈተና መሰረት የሚያደርገው አስቀድመው ተማሪዎች እንዲማሩ የቀረቡ ይዘቶችን በመሆኑ የተነሳ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲባል ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በ1996 ዓ.ም. እና በ2004 ዓ.ም. የተዘጋጁት መርሀ ትምህርቶች፣ በ1997 ዓ.ም. እና በ2004 ዓ.ም. የተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት በአጋዥነት ያገለገሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡

ከ2001—2004 ዓ.ም ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በ1996 ዓ.ም ከተዘጋጁት መርሀ ትምህርቶች እና በ1997 ዓ.ም. ከተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡

የ2005 ዓ.ም. ፈተና በ1996 ዓ.ም. ለ9ኛ ክፍል ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት፣ በ1997 ዓ.ም. ከተዘጋጀው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣ እንዲሁም በ2004 ዓ.ም. ለ10ኛ ክፍል ከተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እና መማሪያ መጽሐፍ ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በ2005 ዓ.ም. የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች በ2004 ዓ.ም. በዘጠኛ የክፍል ደረጃ ሲማሩ የቆዩት በ1996 ዓ.ም. በተዘጋጀው መርሀ ትምህርት እና በ1997 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በነበረው መማሪያ መጽሐፍ ሲሆን፣ በ2005 ዓ.ም. በ10ኛ የክፍል ደረጃ የተማሩት ደግሞ በ2004 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በ2005 ዓ.ም. ተግባራዊ በሆነው አዲስ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እና መማሪያ መጽሐፍ በመሆኑ ነው፡፡

የ2006 ዓ.ም. ፈተና ደግሞ በ2004 ዓ.ም. ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ ምክንያት አጋዥ የመረጃ ምንጭ ሆነዋል፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

በማንኛውም ጥናታዊ ክንውን አጥኚው እንደ ጥናቱ ዓይነትና ባህሪ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚጠቀምባቸው የተለያዩ መሳሪያዎች ይኖሩታል፡፡ ያለው (2004፡147-148) የጽሑፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ፣ መዛግብት፣ ፈተናዎች፣ ውይይት ዋና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚህ ጥናት የሰነድ ፍተሻ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋነኛው ዓላማ በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት አማካይነት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ከ2001—2006 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ መተንተን በመሆኑ የሰነድ ፍተሻ ቀዳሚው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከ2001—2006 ዓ.ም. የተሰጡት ፈተናዎች በዐቢይ ሰነድነት፣

ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ደግሞ በአጋዥ ሰነድነት ተፈትሸዋል፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ ወሳኝ የንሞና (Nonprobability Sampling) ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ወሳኝ ንሞና በውስጡ የተለያዩ የንሞና አመራረጥ ዘዴዎችን ያካተተ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በጥናቱ ዓላማ ላይ በመመስረት የዓላማ ተኮር ንሞናን (Purposeful, purposive, judgement or judgemental sampling) ተግባራዊ ያደረገ ነው (ያለው 2004፡132)፡፡

በአዲሱ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጠው ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት (10ኛ ክፍልን ለሚያጠናቅቁ) ብቻ በመሆኑ የተነሳ ብቸኛው ተመራጭ ሆኗል፡፡

በሀገራችን በአዲሱ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ መሰረት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና በሀገር አቀፍ ደረጃ መሰጠት የተጀመረው በ1993 ዓ.ም. ነው (ትምህርት ሚኒስቴር 1993፡32)፡፡ በ2006 ዓ.ም. ለ14ኛ ጊዜ የተሰጠ ሲሆን ከ2001 — 2006 ዓ.ም. በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ፈተናዎች በጥናቱ ዓላማ ላይ ተመስርተው የተመረጡ ናቸው፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በየፈተናዎቹ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ተለይተዋል እንዲወጡ ተደርገዋል፡፡ በተሰበሰቡት መረጃዎች መሰረት በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች በየፈርጃቸው ተለይተው ከቀረቡ በኋላ ሠንጠረዥንና ግራፍን በመጠቀም ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች፣ ከፈተና መርሆዎች፣ ከተተኳሪ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አኳያ ተተንትነዋል፡፡

ስለዚህ በጥናቱ ውስጥ ከ2001—2006 ዓ.ም. የተሰጡት የስድስቱ ዓመታት ፈተናዎች በሰነድነት (Document) ተፈትሸዋል፡፡ በየፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ከተነሱት የፈተና መመዘኛ መስፈርቶችና የፈተና መርሆዎች ተቃኝተዋል፡፡ በትንታኔው የሰዋስው ጥያቄዎች ከፈተና መርሆዎች አኳያ የሚታዩባቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ትኩረት ከ2001—2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ መተንተን እንደመሆኑ መጠን በጥናቱ ዓላማ ላይ በመመስረት የተገኙት ውጤቶች በምዕራፍ ሁለት ከተነሱት ንድፈ ሀሳባዊ ጉዳዮች አንጻር ተተንትነዋል፡፡ በንዑስ ክፍል 4.1 የፈተናዎች ቅኝት፣ በ4.2 የተተኳሪ ፈተናዎች የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት፣ በ4.3 በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ከተዘጋጁት መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አንጻር ምን እንደሚመስል እና በ4.4 ደግሞ በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከፈተና መርሆዎች አኳያ የሚታይባቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተካተው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. የፈተናዎች ቅኝት

በሀገራችን በሀገር አቀፍ ደረጃ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን (10ኛ ክፍልን) ለሚጨርሱ ተማሪዎች የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ፣ የመሰናዶ ትምህርታቸውን (12ኛ ክፍልን) ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናዎች ይሰጣሉ፡፡ ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት ከተሰጡት ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ይገኝበታል፡፡

ከ2001 እስከ 2006 ዓ.ም. ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያነት ተዘጋጅተው በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የሽፋን ገጽ ላይ ፈተናውን ያዘጋጀው ድርጅት ስም፣ ፈተናው ለየትኛው የክፍል ደረጃ እንደተዘጋጀ፣ የፈተናውን ዓይነት (Subject)፣ ፈተናው የተሰጠበትን ወር እና ዓ.ም.፣

የትምህርት ዓይነት መለያን፣ የጥራዝ መለያን፣ ለፈተናው የተፈቀደው የጊዜ መጠን፣ የጥያቄውን ብዛት እና አጠቃላይ መመሪያዎችን ይዟል፡፡

ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት የተሰጡት ፈተናዎች እያንዳንዳቸው በየትምህርት ዓይነታቸው መለያ (CODE) ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ፈተናዎች የተሰጣቸው የትምህርት ዓይነት መለያ (SUBJECT CODE) 01 ነው፡፡ በየዓመቱ የተሰጡት ፈተናዎች በተለያዩ አራት ጥራዞች የተዘጋጁ ሲሆኑ ለየጥራዞቹ መለያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከ2001 እስከ 2005 ዓ.ም. የተሰጡት ፈተናዎች የጥራዝ መለያ (BOOKLET CODE) በተከታታይ “81”፣ “82”፣ “83” እና “84” ሲሆኑ፣ በ2006 ዓ.ም. የተሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የጥራዝ መለያ ደግሞ “010”፣ “011”፣ “012” እና “013” ናቸው፡፡

ፈተናዎቹ እያንዳንዳቸው ዘጠና ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች የ2001 ዓ.ም. እና የ2003 ዓ.ም. በስምንት መመሪያዎች የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ የ2002፣ የ2006 እና የ2004 ዓ.ም. በዘጠኝ፣ የ2005 ዓ.ም. ደግሞ በአስር መመሪያዎች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡ በያመቱ ተዘጋጅተው በተሰጡት አራት አራት ጥራዞች ውስጥ የሚገኙት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ ልዩነታቸው በየጥራዞቹ ውስጥ ጥያቄዎቹ የሚገኙበት መመሪያ ቅደም ተከተል፣ የጥያቄዎቹ ተራ ቁጥር እና አማራጭ መልሶች ተዘበራርቀው መቀመጣቸው ነው፡፡ ለዚህም በ2004 ዓ.ም በተሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በአራቱም ጥራዞች ውስጥ ከሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ አንዱን በአስረጅነት እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

በጥራዝ መለያ “81” **“መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 23 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡”** በሚለው የመጀመሪያ መመሪያ ተራ ቁጥር 11 ላይ የሚከተለው የሰዋስው ጥያቄ ሰፍሯል፡፡

*11. ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?*

*A. ወንዝ ተሻግሮ የመጣ ጠላት ሳይገድል አይመለስም፡፡*

*B. አርቆ አሳቢ የሆኑ ሰዎች የማመዛዘን ችሎታ አላቸው፡፡*

*C. በሀገሬ ማር የተጣለው ጠጅ ተጠጥቶ አይጠገብም፡፡*

*D. ታናሽ እህቴ በትላንቱ መርከብ ወደ ውጪ ሀገር ሄደች፡፡*

በጥራዝ *መለያ* "82" **"መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 38 እስከ 60 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡"** በሚለው አምስተኛ *መመሪያ* ስር ከተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ በተ.ቁ. 60 ላይ የሚከተለው ጥያቄ ሰፍሯል፡፡

*60. ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?*

*A. በሀገሬ ማር የተጣለው ጠጅ ተጠጥቶ አይጠገብም፡፡*

*B. ታናሽ እህቴ በትላንቱ መርከብ ወደ ውጪ ሀገር ሄደች፡፡*

*C. ወንዝ ተሻግሮ የመጣ ጠላት ሳይገድል አይመለስም፡፡*

*D. አርቆ አሳቢ የሆኑ ሰዎች የማመዛዘን ችሎታ አላቸው፡፡*

በጥራዝ *መለያ* "83" **"መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 12 እስከ 34 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡"** በሚለው ሦስተኛ *መመሪያ* ስር ከተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ በተ.ቁ. 15 ላይ የሚከተለው ጥያቄ ይገኛል፡፡

*15. ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?*

*A. አርቆ አሳቢ የሆኑ ሰዎች የማመዛዘን ችሎታ አላቸው፡፡*

*B. ወንዝ ተሻግሮ የመጣ ጠላት ሳይገድል አይመለስም፡፡*

*C. ታናሽ እህቴ በትላንቱ መርከብ ወደ ውጪ ሀገር ሄደች፡፡*

*D. በሀገሬ ማር የተጣለው ጠጅ ተጠጥቶ አይጠገብም፡፡*

በጥራዝ *መለያ* "84" ላይ **"መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 50 እስከ 72 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡"** በሚለው ሰባተኛ *መመሪያ* ስር በተ.ቁ. 65 ላይ የሚከተለው ጥያቄ ሰፍሯል፡፡

*65. ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?*

*A. ታናሽ እህቴ በትላንቱ መርከብ ወደ ውጪ ሀገር ሄደች፡፡*

*B. በሀገሬ ማር የተጣለው ጠጅ ተጠጥቶ አይጠገብም፡፡*

*C. አርቆ አሳቢ የሆኑ ሰዎች የማመዛዘን ችሎታ አላቸው፡፡*

*D. ወንዝ ተሻግሮ የመጣ ጠላት ሳይገድል አይመለስም፡፡*

በሚል መልክ ቀርበዋል፡፡ በአስረጅነት ከቀረበው ጥያቄ *መመልከት* እንደሚቻለው ጥያቄው በጥራዝ *መለያ* "81" በመጀመሪያው፣ በጥራዝ *መለያ* "82"

በአምስተኛው፣ በጥራዝ መለያ “83” በሦስተኛው፣ በጥራዝ መለያ “84” ደግሞ በሰባተኛው መመሪያ ስር የተካተተ ነው፡፡ በአስረጅነት የቀረበው የሰዋስው ጥያቄ ይዘት የሚገኝበት መመሪያ በአራቱም ጥራዞች አንድ ዓይነት ነው፡፡

በአስረጅነት የቀረበው የሰዋስው ጥያቄ ይዘት የተካተተበት መመሪያ ሲታይ በአራቱም ጥራዞች ውስጥ የተጠቀሰው መመሪያ በስሩ ሃያ ሦስት ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ በመመሪያው ውስጥ ከተካተቱት ጥያቄዎች ብዛት አኳያ በምሳሌነት የቀረበው ጥያቄ በጥራዝ መለያ “81” “82”፣ “83” እና “84” ከቀረቡት ሃያ ሦስት ጥያቄዎች በቅደም ተከተል 11ኛውን፣ 23ኛውን፣ 4ኛውን እና 16ኛውን ተራ ቁጥር ይዞ ይገኛል፡፡ ይህም በየጥራዞቹ ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ ጥያቄዎቹ የሚገኙበት መመሪያ ቅደም ተከተል እና የጥያቄዎቹ ተራ ቁጥር ግን የተለያየ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በጥያቄው ላይ መመልከት እንደሚቻለው በአማራጭነት የቀረቡት መልሶች በየጥራዞቹ ውስጥ ተዘበራርቀው የተቀመጡ ናቸው፡፡ “ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?” ለሚለው ዋና የጥያቄ ክፍል በየጥራዞቹ ውስጥ የቀረቡት አማራጮች ተዘበራርቀው ቀርበዋል፡፡ ከላይ በአስረጅነት ለቀረበው ጥያቄ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ውስጥ በጥራዝ መለያ “81” በምርጫ “D” ላይ “ታናሽ እህቴ በትላንቱ መርከብ ወደ ውጪ ሀገር ሄደች፡፡” በሚል የቀረበው ትክክለኛ መልስ በጥራዝ መለያ “82” አማራጭ “B”፣ በጥራዝ መለያ “83” አማራጭ “C”፣ በጥራዝ መለያ “84” ደግሞ አማራጭ “A” ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ሌሎቹም ትክክለኛ እና አሳሳች መልሶች በየጥራዞቹ ውስጥ በዚህ መልክ ተዘበራርቀው ተቀምጠዋል፡፡

ባጠቃላይ በአስረጅነት የቀረበው “ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?” የሚለው የጥያቄው ዋና ክፍል በየጥራዞቹ ውስጥ አንድ ዓይነት ሲሆን፣ መመሪያው የሚገኝበት ቅደም ተከተል፣ የጥያቄው ተራ ቁጥር እና በአማራጭነት የቀረቡት መልሶች ግን በየጥራዞቹ ውስጥ ተዘበራርቀው ቀርበዋል፡፡ ይህም በተፈታኞች መካከል ሊከሰት የሚችለውን የኩረጃ መጠን ለመቀነስም ሆነ ለመከላከል ይረዳል፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ፈተናዎች ውስጥ የአንብቦ መረዳትን፣ የመጻፍን፣ የመናገርን፣ የማድመጥን ክሂል፣ እንዲሁም የሥነ-ጽሑፍ እና የሰዋስው እውቀትን ለመመዘን የሚያስችሉ ጥያቄዎች ተካተውባቸዋል፡፡ በፈተናዎቹ ውስጥ የሚገኙትን ጥያቄዎች ብዛት በቁጥር እና በመቶኛ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡

| የጥያቄዎቹ ይዘት | ጥያቄዎቹ የቀረቡበት ዓመተ ምህረት | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2001 | | 2002 | | 2003 | | 2004 | | 2005 | | 2006 | |
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| የንባብ ክሂል | 11 | 12.2 | 9 | 10 | 10 | 11.1 | 10 | 11.1 | 10 | 11.1 | 13 | 14.4 |
| የጽህፈት ክሂል | 17 | 18.9 | 21 | 23.3 | 19 | 21.1 | 19 | 21.1 | 24 | 26.7 | 18 | 20 |
| የመናገር ክሂል | 8 | 8.9 | 10 | 11.1 | 8 | 8.9 | 5 | 5.6 | 10 | 11.1 | 4 | 4.5 |
| የማድመጥ ክሂል | 3 | 3.3 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 | 3.3 | 2 | 2.2 |
| ሥነ-ጽሑፍ | 25 | 27.8 | 26 | 28.9 | 27 | 30 | 27 | 30 | 19 | 21.1 | 28 | 31.1 |
| ሰዋስው | 26 | 28.9 | 24 | 26.7 | 26 | 28.9 | 29 | 32.2 | 24 | 26.7 | 25 | 27.8 |
| ድምር | 90 | 100 | 90 | 100 | 90 | 100 | 90 | 100 | 90 | 100 | 90 | 100 |

ሠንጠረዥ-1፡- የተተኳሪ ፈተናዎች አጠቃላይ የጥያቄ ብዛት በቁጥርና በመቶኛ


ከላይ በሠንጠረዥ-1 ላይ እንደተመለከተው ከ2001—2006 ዓ.ም. ድረስ ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ተዘጋጅተው የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ባጠቃላይ 540 ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 154ቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት ካጠቃላዩ የፈተና ጥያቄ አንጻር ሲታይ 28.52 በመቶ የሚሆነውን ይዟል፡፡

በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙ የፈሊጣዊ ንግግርን ፍች የሚወክሉ ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቶችና በመማሪያ መጽሐፎች በሥነ-ጽሑፍ ይዘትነት

ተካተው በመገኘታቸው ምክንያት በዚህም ጥናት በሰዋስው ጥያቄ ይዘት ውስጥ አልተካተቱም፡፡

ይህ ጥናት በየፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው በሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የተነሳ በየዓመቱ በተሰጡት ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት በቁጥር እና በመቶኛ በግራፍ-1 ላይ እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

**ግራፍ-1 የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ብዛት በቁጥርና በመቶኛ**




በግራፍ-1 ላይ እንደሚታየው በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው ከሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ የሚገኘው በ2004 ዓ.ም. የተሰጠው ፈተና ነው፡፡ በየፈተናዎቹ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች በሙሉ በምርጫ ጥያቄ አቀራረብ ስልት የቀረቡት ናቸው፡፡ እንደ Weir (2005፡62) አገላለጽ የምርጫ ጥያቄ ከተሰጡት አራት ወይም አምስት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ የሚመለስ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው አራት አራት አማራጮችን ይዘዋል፡፡

በእያንዳንዱ ፈተና ውስጥ የተለያዩ የሰዋስው ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ተካተው ይገኛሉ፡፡ ይህንን እንደሚከተለው ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 4.2. የተተኳሪ ፈተናዎች የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት

በየፈተናዎቹ ውስጥ የቋንቋ አጀማመርንና ባህርያትን፣ ስነ-ድምጽን፣ ስነ-ምዕላድን፣ ስነ-ፍችን እና ስነ-አገባብን የሚመለከቱ ጥያቄዎች መካተታቸውን በሰነድ ፍተሻ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ሰዋስዋዊ ይዘቶች በስራቸው ንዑሳን ይዘቶችን አካተው ይዘዋል፡፡ በእያንዳንዱ ፈተና ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት እና መጠን በሠንጠረዥ-2 እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙ ሰዋስዋዊ ይዘቶች | የሰዋስው ጥያቄዎች ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 |
| 1. የቋንቋ አጀማመርና ባህርያት | | | | | | |
| 1.1. የቋንቋ አጀማመር | 1 | 1 | 1 | - | - | - |
| 1.2. የቋንቋ ባህርያት | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 |
| 2. ስነ-ድምጽ | | | | | | |
| 2.1. የድምጽ መጥበቅና መላላት | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 3. ስነ-ምእላድ | | | | | | |
| 3.1. ነጻና ጥገኛ ምእላድ | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 2 |
| 3.2. የእርባታ ምእላድ ተግባር | 4 | 1 | 3 | 1 | 3 | 5 |
| 3.3. የምእላድና የቃል አንድነት | - | 1 | - | - | - | - |
| 3.4. የቃል ክፍል | 2 | 2 | 2 | 1 | - | 1 |
| 3.5. የቃል ምስረታ | 1 | 1 | - | 1 | 4 | 2 |
| 4. ስነ-አገባብ | | | | | | |
| 4.1. ስነ-ሐረግ | | | | | | |
| 4.1.1. የሀረግ ዓይነትን መለየት | 2 | 4 | 4 | 7 | 4 | 3 |
| 4.1.2. የስም መሙያ | - | 1 | - | - | - | - |
| 4.1.3. የስምና የግስ ገላጭ | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 |
| 4.2. አረፍተ ነገር | | | | | | |
| 4.2.1. የአረፍተ ነገር ባለቤት እና ተሳቢ | 2 | - | - | - | - | - |
| 4.2.2. ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገር | 2 | - | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 4.2.3. የአረፍተ ነገር ስልት | - | - | 1 | - | 2 | 2 |
| 4.2.4. ሰዋስዋዊ ስህተት | - | - | 1 | - | - | - |
| 4.2.5. ተገቢውን ቃል በዐ.ነ. ውስጥ መጠቀም | - | 1 | - | 2 | - | - |
| 4.2.6. ቃላትን በአገባብ ቅደም ተከተል በማደራጀት አረፍተ ነገር መመስረት | 1 | - | - | 1 | - | - |
| 4.3. አያያዥ ቃል/ ሐረግ | 1 | - | 2 | - | - | - |
| 5. ስነ-ፍች | | | | | | |
| 5.1. የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 1 |
| 5.2. የቃላት ተቃራኒ ፍቺ | - | - | - | - | 1 | - |
| 5.3. የቃላት ቀጥተኛ እና አገባባዊ ፍቺ | 1 | 3 | - | 3 | 1 | 3 |
| ድምር | 26 | 24 | 26 | 29 | 24 | 25 |

ሠንጠረዥ-2 የተተኳሪ ፈተናዎች የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት እና መጠን

ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ከ2001—2006 ዓ.ም. በተሰጡት ሀገር አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ከተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ ከፍተኛውን እና ዝቅተኛውን ድርሻ የያዙት ይዘቶች ከላይ በሠንጠረዥ-2 በቀረበው መረጃ መነሻነት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በ2001 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ካጠቃላይ የሰዋስው ጥያቄዎች (ከ26ቱ) ይዘት ውስጥ እያንዳንዳቸው አስር (38.46%) ጥያቄዎችን በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው የሚገኙት የስነ-ምእላድ እና የስነ-አገባብ ይዘቶች ናቸው፡፡ አንድ (3.85%) ጥያቄ በመያዝ ዝቅተኛውን ደረጃ የያዘው ደግሞ የስነ-ድምጽ ይዘት መሆኑን ከተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማግኘት ተችሏል፡፡

በ2002 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ካጠቃላይ የሰዋስው ጥያቄዎች (ከ24ቱ) ውስጥ የስነ-አገባብ ይዘት ስምንት (33.3%) ጥያቄዎችን በማካተቱ ከፍተኛውን ቁጥር ሲይዝ፣ የስነ-ድምጽ ይዘት ደግሞ አንድ (4.17%) ጥያቄ በማካተቱ ዝቅተኛውን ደረጃ ይዟል፡፡

በ2003 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከ26ቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ የስነ-አገባብ ይዘት አስራ አንድ (42.31%) ጥያቄዎችን በማካተቱ ቀዳሚውን ደረጃ ሲይዝ፣ አንድ (3.85%) ጥያቄን በመያዝ የመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ የስነ-ድምጽ ይዘት ነው፡፡


በ2004 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከ29 የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ የስነ-አገባብ ይዘት አስራ አራት (48.28%) ጥያቄዎችን በማካተት ቀዳሚውን ስፍራ ሲይዝ፣ አንድ (3.45%) ጥያቄ በማካተት ዝቅተኛውን ስፍራ የያዘው ደግሞ የስነ-ድምጽ ይዘት ነው፡፡

በ2005 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ካጠቃላይ (ከ24ቱ) የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ እያንዳንዳቸው ዘጠኝ (37.5%) ጥያቄዎችን በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው የሚገኙት የስነ-ምእላድ እና የስነ-አገባብ ይዘቶች ናቸው፡፡ አንድ

(4.17%) ጥያቄ በመያዝ ዝቅተኛውን ደረጃ የያዘው ደግሞ የስነ-ድምጽ ጥያቄ ይዘት ነው፡፡

በ2006 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከ25ቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ የስነ-ምእላድ ይዘት አስር (40%) ጥያቄዎችን በማካተት የመጀመሪያውን ደረጃ ሲይዝ፣ አንድ (4%) ጥያቄን በመያዝ የመጨረሻው ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ የስነ-ድምጽ ጥያቄ ይዘት ነው፡፡

በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካትተው የሚገኙትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና መጠን ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው በግራፍ-2 እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡




ግራፍ-2 የተተኳሪ ፈተናዎች የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት እና መጠን

ከዚህ በላይ በግራፍ-2 ላይ እንደተመለከተው በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች እና ከየይዘቶቹ ምን ያህል ጥያቄዎች እንደተካተቱባቸው በሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ መመልከት ተችሏል፡፡

በቀጣይ ደግሞ ለሁለተኛ ደረጃ ማጠቃለያ በሆኑት የክፍል ደረጃዎች ለትምህርትነት ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የትኞቹ ይዘቶች እንደተካተቱ እና መካተት ከሚገባቸው ይዘቶች ውስጥ ያልተካተቱትን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4.3. የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከመርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አንጻር

በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት በያመቱ ተዘጋጅተው የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂልም ሆነ የእውቀት ዘርፍ ችሎታ መለካት ነው፡፡ በችሎታ መለኪያ የቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ተፈታኞቹ አስቀድመው የተማሯቸውን ሰዋስዋዊ ይዘቶች መነሻ በማድረግ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች በፈተናዎቹ ውስጥ የትኞቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካተው እንደሚገኙ ለማየት ያስችል ዘንድ ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ይዘቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.3.1. በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች

ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት ተዘጋጅተው በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከመርሀ ትምህርቱና ከመማሪያ መጽሐፉ አኳያ በመመልከት በየፈተናዎቹ ውስጥ የትኞቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንደተካተቱ እና መካተት ሲገባቸው ያልተካተቱትን ይዘቶች መለየት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በሠንጠረዥ-3 ከ2001—2006 ዓ.ም. ተዘጋጅተው

ከተሰጡት የሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ጋር ተያያዥ በሆኑት መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ቀርበዋል።

| በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች | 9ኛ ክፍል | | 10ኛ ክፍል | |
|---|---|---|---|---|
| | 1996[1]/1997[2] ዓ.ም. | 2004 ዓ.ም. | 1996/1997ዓ.ም | 2004ዓ.ም. |
| **1. የቋንቋ መሠረታዊ ጉዳዮች** | | | | |
| 1.1. የቋንቋ ምንነትና አጀማመር | X | X | - | X |
| 1.2. የቋንቋ መሰረታዊ ባህርያት | - | - | X | X |
| **2. ስነ-ድምጽ** | | | | |
| 2.1. የድምጽ መጥበቅና መላላት | X | X | X | X |
| **3. ስነ-ምእላድ** | | | | |
| 3.1. የምእላድ ምንነት | X | X | X | - |
| 3.2. ነጻና ጥገኛ ምእላድ | X | X | X | X |
| 3.3. የጥገኛ ምእላድ ተግባር | X | - | - | X |
| 3.4. የእርባታ ምእላድ ተግባር | X | X | - | X |
| 3.5. መነሻና መድረሻ ቅጥያ | X | X | X | |
| 3.6. የቃል ክፍል | X | X | - | X |
| 3.7. ነጠላ ቁጥርን ወደ ብዙ ቁጥር መቀየር | X | - | - | - |
| 3.8. የቃል ክፍል ሙያ | X | X | - | - |
| 3.9. በቃል ውስጥ የሆሄያት መገኛ ቦታ | X | - | - | - |
| 3.10. የቃል ቅርጽ ለውጥ | X | - | - | - |
| 3.11. ከግስ ግስን መመስረት | - | X | - | - |
| 3.12. ከግስ ስምና ቅጽልን መመስረት | X | | X | X |
| 3.13. ከግስ ስም መሰል ቃልንና ቅጽልን መመስረት | - | - | - | X |
| 3.14. ጥምር ቃልን መመስረት | X | - | X | - |
| 3.15. ከስም በቅጠላ ቅጽል መመስረት | X | - | X | - |
| **4. ስነ-አገባብ** | | | | |

[1] .1996 የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መርሀ ትምህርቶች የተዘጋጁበትን ዓ.ም. ያመለክታል።
[2] 1997 የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት የተዘጋጁበትን ዓ.ም. ያመለክታል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4.1. ስነ-ሐረግ | | | | |
| 4.1.1. የሐረግ ምንነት | - | X | - | - |
| 4.1.2. ሐረግ መመስረት | - | X | X | X |
| 4.1.3. የሐረጋትን ዓይነት መለየት | X | X | X | X |
| 4.1.4. የስምና የግስ ገላጭ | X | - | - | - |
| 4.2. አረፍተ ነገር | | | | |
| 4.2.1. ሰዋስዋዊ ስህተት | X | X | X | - |
| 4.2.2. በአ.ነ. ውስጥ የቃላት ቅደም ተከተል | X | - | - | - |
| 4.2.3. ተራ እና ውስብስብ አ.ነ. | X | X | X | X |
| 4.2.4. የአ.ነ. ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ | X | X | X | |
| 4.2.5. ጅምር አ.ነ. ማሟላት፣ | - | X | X | X |
| 4.2.6. የአረፍተ ነገር ስልት | - | - | - | X |
| 4.3. መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት | X | X | X | X |
| 5. ስነ-ፍቺ | | | | |
| 5.1. የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ | X | X | X | X |
| 5.2. የቃላት እና የሀረጋት ቀጥተኛ ፍቺ | - | X | - | X |
| 5.3. የቃላት እና የሐረጋት አገባባዊ ፍቺ | X | X | X | X |
| 5.4. በቃላት መካከል ያለ የፍች ልዩነት | X | - | X | X |
| 5.5. እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | X | X | - | X |
| 5.6. አገላለጾችን በአንድ ቃል መተካት | - | - | X | - |

ሠንጠረዥ-3፡- ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተዘጋጁ የአማርኛ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች

በሠንጠረዥ-3 ላይ በቀረበው መረጃ ላይ እንደሚታየው ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቋንቋን መሠረታዊ ጉዳዮች፣ ስነ-ድምጽን፣ ስነ-ምእላድን፣ ስነ-አገባብን እና ስነ-ፍችን የሚመለከቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካተዋል፡፡ በነዚህ ይዘቶች ውስጥ ንዑሳን ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ፡፡

## 4.3.2. በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍት አንጻር

ለሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያነት የተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከተዘጋጁት መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አንጻር በመፈተሽ በየፈተናዎቹ ውስጥ የትኞቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንደተካተቱ፣ መካተት ከሚገባቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ የትኞቹ እንዳልተካተቱ፣ በመርሀ ትምህርቶች እና በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያልተካተቱ ነገር ግን በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች የትኞቹ እንደሆኑ እንደሚከተለው ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል፡፡

በስድስቱም ዓመታት በተሰጡት ተተኳሪ የአማርኛ ፈተናዎች ውስጥ መካተት የሚገባቸውን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት አስመልክቶ ከላይ በሰንጠረዥ-2 እና በሠንጠረዥ-3 ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ተተኳሪ ፈተናዎች የቋንቋን መሠረታዊ ባህርያትን፣ ስነ-ድምጽን፣ ስነ-ምዕላድን፣ ስነ-አገባብን እና ስነ-ፍችን የሚመለከቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አካተዋል፡፡ በነዚህ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ውስጥ በንዑስ ይዘትነት የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከተተኳሪ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አንጻር በመመልከት በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በ2001 ዓ.ም. በተሰጠው ሀገር አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከተተኳሪ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አኳያ መካተት ከሚገባቸው የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ ጥምር ቃልን፣ ሰዋስዋዊ ስህተትን፣ በቃላት መካከል ያለን የፍች ልዩነትን፣ የቃላትን ተቃራኒ ፍች ሊወክሉ የሚችሉ ጥያቄዎች አልተካተቱም፡፡

በ2002 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከመርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አኳያ መካተት ከሚገባቸው የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ ጥምር ቃልን፣ የስም ሙያን፣ ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገርን፣ ሰዋስዋዊ

ስህተትን፣ የቃላትን ተቃራኒ ፍቺ፣ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ በአገባብ ቅደም ተከተል ማደራጀትን የሚመለከቱ ይዘቶችን አስመልክቶ አንድም ጥያቄ አልተካተተበትም። በፈተናው ውስጥ በመርሀ ትምህርቶች እና በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ግን ያልተካተቱ የምዕላድን እና የቃልን አንድነት፣ የስም መሙያን የሚያመለክቱ ይዘቶች ተካተዋል።

በ2003 ዓ.ም. በተሰጠው ሀገር አቀፍ የአማርኛ ፈተና ከመርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አኳያ መካተት ከሚገባቸው የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ ጥምር ቃልን፣ የአረፍተ ነገር ባለቤትንና ተሳቢን፣ የቃላትን የፍች ልዩነት፣ የቃላትን ተቃራኒ ፍች፣ የቃላትን አገባባዊ ፍች፣ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ በአገባብ ቅደም ተከተል ማደራጀትን የሚወክሉ ጥያቄዎች አልተካተቱበትም። በፈተናው ውስጥ በመርሀ ትምህርቶች እና በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያልተካተተ የአረፍተ ነገርን ስልት የሚወክል ጥያቄ ተካትቷል።

በ2004 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከመርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አኳያ መካተት ከሚገባቸው የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ የቋንቋን አጀማመር፣ የዕርባታ ምዕላድን ተግባር፣ የአረፍተ ነገር ባለቤትንና ተሳቢን፣ ሰዋስዋዊ ስህተትን፣ የቃላትን የፍች ልዩነት፣ የቃላትን ተቃራኒ ፍች፣ የሚወክሉ ይዘቶች አልተካተቱበትም።

በ2005 ዓ.ም. በተሰጠው ሀገር አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አኳያ የቋንቋን አጀማመር፣ የቃል ክፍልን፣ ጥምር ቃልን፣ የአረፍተ ነገር ባለቤትንና ተሳቢን፣ ሰዋስዋዊ ስህተትን፣ የቃላትን የፍች ልዩነት፣ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ በአገባብ ቅደም ተከተል ማደራጀትን የሚወክሉ ጥያቄዎች አልተካተቱበትም።

በ2006 ዓ.ም. በተሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመርሀ ትምህርቶች እና ከመማሪያ መጻሕፍት አንጻር መካተት ከሚገባቸው የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት

ውስጥ የቋንቋን አጀማመር፣ ጥምር ቃልን፣ የአረፍተ ነገር ባለቤትንና ተሳቢን፣ ሰዋስዋዊ ስህተትን፣ የቃላትን የፍች ልዩነት፣ የቃላትን ተቃራኒ፣ አያያዥ ቃልን የሚወክሉ ጥያቄዎች አልተካተቱበትም፡፡ የስምና የግስ ገላጭን የሚመለከት ይዘት በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያልተካተተ በፈተናው ውስጥ ተካቷል፡፡

በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ለመመዘን የተፈለገውን የዕውቀት ደረጃ መለካት ይችሉ ዘንድ የፈተና መመዘኛ መስፈርትን በተገቢው መንገድ አሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት በ2.1.4. ስር ፈተናዎች ማሟላት የሚገባቸው የፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ምን ምን እንደሆኑ ተገልጸዋል፡፡ ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ተገቢነት ነው፡፡ ከተገቢነት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ የይዘት ተገቢነት ነው፡፡ ከይዘት ተገቢነት አኳያ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ በተዘጋጁት መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተመጣጠነ መልኩ ይዘቶቹን የሚወክሉ ጥያቄዎች መካተታቸውን ይመለከታል፡፡ በዚህም መነሻነት በተካሄደው ፍተሻ በስድስቱ ዓመታት በተሰጡት ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ለየይዘቱ በመርሀ ትምህርቶቹ እና በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተሰጣቸው የትኩረት ደረጃ አንጻር ተመጣጣኝ የሆነ ወካይ ጥያቄ እንዳልተካተተባቸው በተካሄደው የሰነድ ፍተሽ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በ2001 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ የቃል ምስረታን የሚወክል አንድ፣ የጥገኛ ምእላድን ተግባር የሚወክል አራት ጥያቄዎች ተካተው ይገኛሉ፡፡ ለነዚህ ይዘቶች የተሰጠው የትኩረት ደረጃ ሲታይ የቃል ምስረታን በሚመለከት በ9ኛ ክፍል ስምንት ጊዜ፣ በ10ኛ ክፍል አራት ጊዜ፣ በድምሩ አስራ ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ሲሆን፣ የጥገኛ ምእላድን ተግባር በሚመለከት በ9ኛ

ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሶስት ጊዜ ብቻ ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ነው (አባሪ ሰ)፡፡

በሠንጠረዥ-2 እና በግራፍ-2 ላይ እንደሚታየው በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በተመጣጠነ መልኩ በየፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው ባይገኙም እንኳ የትኞቹን ሰዋስዋዊ ይዘቶች እንዳካተቱ መመልከት ተችሏል፡፡

ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው በመርሀ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ተገቢውን ውክልና ማግኘታቸው ነው፡፡ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ለየይዘቱ ከተሰጠው የትኩረት ደረጃ አንጻር ሲታይ ጥያቄዎቹ ተገቢውን ውክልና እንዳላገኙ መረዳት ተችሏል (አባሪ ሰ)፡፡ ለይዘቱ የተሰጠውን የትኩረት ደረጃ የሚያመለክተው ይዘቱ በመርሀ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተደጋግሞ መቅረቡ ነው፡፡

በ1997 ዓ.ም. በተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገርን የሚመለከት ይዘት በዘጠነኛ ክፍል አንድ ጊዜ፣ በአስረኛ ክፍል ሶስት ጊዜ፣ በድምሩ አራት ጊዜ ተደጋግሞ ሲቀርብ፣ ሰዋስዋዊ ስህተትን የሚመለከት ይዘት ደግሞ በዘጠነኛ ክፍል ሶስት ጊዜ፣ በአስረኛ ክፍል ሶስት ጊዜ፣ በድምሩ ስድስት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ነው፡፡ በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገርን የሚመለከት ይዘት በዘጠነኛ ክፍል አንድ ጊዜ፣ በአስረኛ ክፍል ሰባት ጊዜ፣ በድምሩ አስር ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን፣ ሰዋስዋዊ ስህተትን የሚመለከት ይዘት ደግሞ በዘጠነኛ ክፍል ሶስት ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ነው (አባሪ ሰ)፡፡ እነዚህን ይዘቶች አስመልክቶ ከ2001—2006 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገር የሚወክሉ በ2001፣ በ2004፣ በ2005 እና በ2006 በተሰጡት ፈተናዎች ሁለት ጥያቄዎች፣ በ2003 በተሰጠው ፈተና ደግሞ አንድ ጥያቄ ብቻ ተካቶ ይገኛል፡፡ በ2002 ዓ.ም. በተዘጋጀው ፈተና ግን

አንድም ወካይ ጥያቄ አልተካተተበትም፡፡ በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚከሰትን የሰዋስዋዊ ስህተት ይዘትን የሚወክል ጥያቄ በ2003 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከተካተተው አንድ ጥያቄ በስተቀር በሌሎቹ ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስዋዊ ስህተትን ይዘት የሚወክል አንድም ጥያቄ አልተካተተባቸውም፡፡ ለየይዘቱ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተሰጠው የትኩረት ደረጃ አኳያ ሲታይ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተገቢው ውክልና እንዳልተሰጣቸው መረዳት ተችሏል፡፡

ባጠቃላይ በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በተሰጡት ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከአንዳንድ ይዘቶች በስተቀር ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ላይ ተመስርተው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በየፈተናዎቹ ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት መረዳት እንደሚቻለው ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተዘጋጁት የአማርኛ መርሀ ትምህርቶችም ሆነ መማሪያ መጻህፍት መሰረት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ተገቢውን ውክልና ያለማግኘት ችግር እንደሚታይባቸው መረዳት ተችሏል፡፡

## 4.4. በየፈተናዎቹ ውስጥ በሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ ላይ ከፈተና መርሆዎች አኳያ የሚታይባቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች

በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው ከሚገኙት 154 የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ የጥያቄው ዋና ክፍል 108 (70.13%) በጥያቄ ስልት፣ 26 (16.88%) ባልተሟላ አረፍተ ነገር አቀራረብ ስልት፣ 20 (12.99%) ጥያቄዎች ደግሞ በተሟላ አረፍተ ነገር የቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡

የምርጫ ጥያቄዎች Brown (1996፡54)፣ Chesla (2002፡19) እንደገለጹት ግንድ (stem)፣ ትክክለኛ መልስ (correct answer) እና አሳሳቾች (Distractors) የሚባሉትን ሶስት ክፍሎች ይይዛሉ፡፡ በምርጫ ጥያቄዎች ውስጥ ተካተው

የሚገኙት አሳሳች መልሶች ልክ እንደትክክለኛው መልስ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል (Mulu and Daniel 2005፡71)፡፡ በጥናቱ ተካላይ ሆነው በቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ዋና ክፍል (ግንድ)፣ አንድ ትክክለኛ መልስ እና ልክ እንደትክክለኛው መልስ አሳሳች መልስ እንዲሆኑ የተቀረጹ ክፍሎችን ይዘው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በ2004 ዓ.ም. በተራ ቁጥር 17 ላይ የሰፈረውን እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

17. *"ኑሮህ ለአደጋ እንዳይጋለጥ ምን አይነት ጥንቃቄዎችን ታደርጋለህ?" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የትኛውን ይገልጻል?*
    A. *ሁለተኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ*
    B. *አንደኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ*
    C. *ሁለተኛ መደብ፣ብዙ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ*
    D. *ሶስተኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣አንስታይ ጾታ*

በዚህ ጥያቄ ላይ "'ኑሮህ ለአደጋ እንዳይጋለጥ ምን አይነት ጥንቃቄዎችን ታደርጋለህ?' በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የትኛውን ይገልጻል?" የሚለው በጥያቄ ስልት የቀረበ የጥያቄው ዋና ክፍል ሲሆን ምርጫ "A" ላይ የሰፈረው ትክክለኛው መልስ ነው፡፡ አሳሳች መልሶች ከትክክለኛው መልስ ጋር በያዙት የቃላት ብዛት (መጠን) ተመሳሳይ በመሆን ቀርበዋል፡፡

በየፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በምዕራፍ ሁለት በ2.1.6. ስር ከተገለጸው የፈተና መርሆዎች አንጻር የሚታይባቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 4.4.1. በጥያቄዎቹ አቀራረብ ላይ የታዩ ጠንካራ ጎኖች

ከ2001—2006 ዓ.ም. ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ተዘጋጅተው በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከፈተና መርሆዎች አኳያ የሚታይባቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሏቸው፡፡ ጠንካራ ጎናቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ተማሪዎች በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ በተቀረጹ ይዘቶች መነሻነት ሊመዘን የተፈለገውን የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ለማሳካት የቀረቡ ናቸው፡፡ ለአስረጅነት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመልከት ይቻላል፡፡

*39. ከሚከተሉት ውስጥ ለነፃ ምእላድ ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?*

| | |
|---|---|
| *A. ቤት* | *C. ቤታችን* |
| *B. ቤቱ* | *D. ቤቶች* |

*73. ከሃረጎቹ መካከል ቅጽላዊ ሃረግ የሆነው የትኛው ነው?*

| | |
|---|---|
| *A. ቀዩ ልጅ* | *C. ብሔራዊ ፈተና* |
| *B. በጣም ዘገምተኛ* | *D. ጠመዝማዛው መንገድ* |

ከላይ በምሳሌው ላይ እንደተመለከተው በ2001 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ተ.ቁ. 39 (አባሪ ለ) ላይ የቀረበው "ነጻ እና ጥገኛ ምዕላድን መለየት" የሚለውን የትምህርት ዓላማ፣ በ2003 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና በተ.ቁ. 73 (አባሪ ሐ) ላይ የቀረበው "የሀረግ ዓይነቶችን ለይቶ ማመልከት" የሚሉት በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካተው የሚገኙ የሰዋስው ትምህርት ዓላማዎችን መነሻ በማድረግ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በየፈተናዎቹ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካተው በሚገኙት የትምህርት ዓላማዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

በ2002 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከቀረበው አንድ የሰዋስው ጥያቄ ይዘት ማለትም በተ.ቁ. "40" ላይ "ሁሉም መልስ ይሆናሉ" (አባሪ ለ) ከሚለው አማራጭ መልስ በስተቀር በሁሉም ተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ "ሁሉም መልስ ናቸው" ፣ "ሁሉም መልስ አይደሉም" ፣ "ሀ እና ለ ብቻ ትክክለኛ መልስ ናቸው" የሚሉ አማራጭ መልሶች አልተካተቱም፡፡

በጥያቄዎቹ ውስጥ ሁለት አፍራሽ አገላለጾችን የያዙ ጥያቄዎች አልተካተቱም። ከ154ቱ ጥያቄዎች በአፍራሽ አገላለጽ የቀረቡት አምስት ጥያቄዎች ከስራቸው በማስመር ወይም ጎላ ብለው እንዲታዩ በማድረግ የቀረቡ ናቸው። እነዚህም ጥያቄዎች በ2001 በተሰጠው በተ.ቁ. 9 እና 11፣ በ2003 ዓ.ም በተሰጠው በተ.ቁ. 72፣ በ2006 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ደግሞ በጥያቄ ተ.ቁ. 36 እና 65 ላይ ይገኛሉ።

በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት አንድ ጥያቄ ላይ የቀረበው ይዘት ለሌላው ጥያቄ ምላሽ ፍንጭ ሰጭ በሆነ መንገድ አልቀረቡም።

በሰዋስው ይዘትነት በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የምርጫ ጥያቄዎች ዋና ክፍል፣ ትክክለኛ መልስ እና አሳሳቾች ሁሉ በአንድ ገጽ ላይ ያለቁ ናቸው።

በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች በተመጣጠነ መልክ ውክልና ተሰጥቷቸው ባይቀርቡም እንኳ ተፈታኞቹ በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ የተቀረጹትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን መነሻ አድርገው የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው።

ከ154 ጥያቄዎች ውስጥ በ2001 አንድ (በተ.ቁ. 4)፣ በ2003 አንድ (በተ.ቁ. 75)፣ በ2004 ሁለት (በተ.ቁ. 12፣19)፣ በ2005 አምስት (በተ.ቁ. 5፣6፣7፣19 እና 20)፣ በ2006 አራት (በተ.ቁ. 64፣68፣75፣77) ባጠቃላይ ከ13 የሰዋስው ጥያቄዎች በስተቀር 141 ጥያቄዎች ውስጥ በጥያቄው ዋና ክፍል ተካትቶ መገኘት የሚገባው አላስፈላጊ ድግግሞሽ በአማራጭ መልሶች ላይ አይታይባቸውም።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የተገለጹት በየፈተናዎቹ ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ከፈተና መርሆዎች አንጻር የታዩባቸው ጠንካራ ጎኖች በቀጣይ በሚዘጋጁ ፈተናዎች ተጠናክረው መቀጠል ያለባቸው ናቸው።

## 4.4.2. በተተኳሪ ጥያቄዎች ላይ የታዩ ደካማ ጎኖች

ከ2001—2006 ዓ.ም. ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ተዘጋጅተው በተሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ከፈተና መርሆዎች አኳያ ከሚታይባቸው ደካማ ጎኖች ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ተፈታኞች ለቀረቡት ጥያቄዎች በግምት እንዳይመልሱ፣ አስበው ተመራምረው ተገቢውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ይመልሱ ዘንድ አሳሳች መልሶች ከትክክለኛው መልስ መርዘም ወይም ማጠር አይኖርባቸውም፡፡ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት የተወሰኑ የሰዋስው ጥያቄዎች አማራጭ መልሶች ላይ ይህ ችግር ይስተዋልባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በ2001 ዓ.ም. (አባሪ ሀ) በተ.ቁ. 22 ላይ የሰፈረውን ጥያቄ እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

22. *ከሚከተሉት መካከል አንዱ ለውስብስብ አረፍተ ነገር ምሳሌ ነው፡፡*
    - A. *በፈተና አዳራሹ ውስጥ ያሉት ተፈታኞች በመብዛታቸው ክፍሉ ተጨናንቋል፡፡*
    - B. *በፈተና አዳራሹ ውስጥ በርካታ ተፈታኞች አሉ፡፡*
    - C. *የፈተና አዳራሹ በተፈታኞች ተጨናንቋል፡፡*
    - D. *በፈተና አዳራሹ ውስጥ ተፈታኞች በረድፍ በረድፍ ተቀምጠዋል፡፡*

በዚህ ምሳሌ ላይ መመልከት እንደሚቻለው በምርጫ "A" ላይ የቀረበው ትክክለኛ መልስ ከሌሎች አሳሳች መልሶች ጋር ሲነጻጸር ረዥም (በውስጡ በርካታ ቃላትን የያዘ) ነው፡፡ ይህም የተፈታኞች ትኩረት በመሳብ በግምት ምላሽ እንዲሰጡ ይጋብዛል፡፡

በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው በሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ በደካማ ጎንነት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የትክክለኛው መልስ ከአሳሳች መልሶች ረዝሞ ወይም አጥሮ የመገኘት ችግር ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ችግር ማለትም ትክክለኛው መልስ ከአሳሳች መልሶች ጋር በቃላት ብዛት፣ በቅርጽ ያለመመጣጠን

ችግር ከሚታይባቸው የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ውስጥ በ2001 ዓ.ም. (አባሪ ሀ) አስራ አምስት /57.69%/ ጥያቄዎች፣ በ2002 ዓ.ም. (አባሪ ለ) አስራ አምስት /62.5%/ ጥያቄዎች፣ በ2003 ዓ.ም. (አባሪ ሐ) አስራ ሁለት /50%/ ጥያቄዎች፣ በ2004 ዓ.ም. (አባሪ መ) አስራ ሁለት /41.4%/ ጥያቄዎች፣ በ2005 ዓ.ም. (አባሪ ሠ) አስራ አንድ /45.8%/ ጥያቄዎች፣ በ2006 ዓ.ም. (አባሪ ረ) በተሰጠው ፈተና ደግሞ አምስት /20%/ ጥያቄዎች ይገኙበታል፡፡ የዚህ ዓይነት ችግር ተፈታኞች ሳያመዛዝኑ ትክክለኛውን መልስ በቀላሉ እንዲያገኙ ፍንጭ ስለሚሰጥ፣ በግምት መልስ እንዲሰጡ ስለሚያደርግ አማራጭ መልሶች በሚዘጋጁበት ጊዜ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ በጥያቄው ዋና ክፍል ላይ መካተት የሚገባው አላስፈላጊ ድግግሞሽ ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በ2006 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና በተ.ቁ. 68 (አባሪ ረ) ላይ ከቀረበው ውስጥ የሚከተለውን መመልከት ይቻላል፡፡

68. *"በአካባቢያችሁ ስለሚገኝ ሐይቅ ወይም ግድብ ወይም ወንዝ ማህበራዊ አገልግሎት በጽሁፍ አስረዱ፡፡" የሚለው ለ________ የአረፍተነገር ስልት በምሳሌነት ይጠቀሳል፡፡*
   A. *ለመጠይቃዊ የአረፍተነገር ስልት*
   B. *ለትዕዛዛዊ የአረፍተነገር ስልት*
   C. *ለሀተታዊ የአረፍተነገር ስልት*
   D. *ለአሉታዊ የአረፍተነገር ስልት*

በምሳሌው ላይ እንደሚታየው "ለ" የሚለው መስተዋድድ እና "የአረፍተ ነገር ስልት" የሚለው ሐረግ በጥያቄው ዋና ክፍል ላይ ብቻ ተካቶ መገኘት ሲገባው በጥያቄው ዋና ክፍል እና በአማራጭነት በቀረቡት መልሶች ላይ በተደጋጋሚ ቀርበዋል፡፡

በተጨማሪም በጥያቄው ዋና ክፍል ላይ መካተት ሲገባቸው በአማራጭ መልሶች ላይ ተደጋግመው ከቀረቡት ውስጥ በ2001 በጥያቄ ተ.ቁ. 4፣ በ2003 በጥያቄ ተ.ቁ. 75፣ በ2004 በጥያቄ ተ.ቁ. 12 እና 19፣ በ2005 በጥያቄ ተ.ቁ. 5፣6፣7፣19 እና 20፣ በ2006 በጥያቄ ተ.ቁ. 64፣68፣75 እና 77 በቀረቡት

ጥያቄዎች ላይ ድግግሞሽ ይታይባቸዋል (ከ154 የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ አስራ ሦስት /8.4%/ ድግግሞሽ የሚታይባቸው ናቸው)፡፡

የምርጫ ጥያቄዎች አንድ ትክክለኛ መልስ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ጥቂቶቹ ትክክለኛ መልስ የሌላቸው እና ከአንድ በላይ መልስን ይዘው ይገኛሉ፡፡ ለአስረጅነት በ2001 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ውስጥ ከተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ መልስ የሌለው ጥያቄ በተ.ቁ. 9 (አባሪ ሀ) ላይ የቀረበውን እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

9. *ከሚከተሉት መካከል አንዱ ለምስርት ቃል ምሳሌ **<u>አይደለም</u>** ፡፡*
   *A. ብልግና*     *C. ጉልበተኛ*
   *B. ሰውነት*     *D. ወታደሩን*

በጥያቄው ላይ እንደሚታየው ከተሰጡት አራት አማራጭ መልሶች ውስጥ ለምስርት ቃል ምሳሌ ሊሆን የማይችለውን መልስ ተፈታኞች እንዲመርጡ የሚጠይቅ ነው፡፡ ከተሰጡት አራት አማራጭ መልሶች ውስጥ በምርጫ “A” “B” እና “C” ላይ የቀረቡት በቅጠላ የተመሰረቱ ውልድ ስሞች ሲሆኑ በምርጫ “D” ላይ የሚገኘው “ወታደሩን” የሚለው ቃል “ወቶ” እና “አደር” ከሚሉት ሁለት ቃላት ጥምረት የተመሰረተ ውልድ ስም ነው፡፡ የተሰጡት አማራጮች በሙሉ ምስርት ቃል በመሆናቸው የተነሳ ለጥያቄው ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚችል አማራጭ የለውም፡፡ በ2005 ዓ.ም. በተዘጋጀው ፈተና ተ.ቁ. 16 ላይ የቀረበውንም ጥያቄ እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

16. *ባለ አንድ ምእላድ የሆነው ቃል ___________ ነው፡፡*
   *A. ሆዳም*     *C. ደብተሬ*
   *B. ድርሰት*     *D. ድመቷ*

በሚለው ጥያቄ ላይ እንደሚታየው ባለአንድ ምዕላድ የሆነውን ቃል እንዲለዩ የቀረበ ነው፡፡ በአማራጭነት የቀረቡት መልሶች በሙሉ ከአንድ በላይ ምዕላድን የያዙ ቃላት ናቸው፡፡ ምርጫ “A” /ሆድ/ እና /-ኣም/፣ ምርጫ “B” /ድርስ-/ እና /-ኧት/፣ ምርጫ “C” /ደብተር/ እና /-ኤ/፣ ምርጫ “D” ላይ የቀረበው ቃል ደግሞ

/ድመት/ እና /-ዋ/ የሚሉትን ምዕላዶች የያዙ ናቸው። በዚህም መሰረት ለጥያቄው ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ባለአንድ ምዕላድ የሆነ ቃል ባለመኖሩ ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚችል አማራጭ የለውም። በተጨማሪም በ2003 ዓ.ም. በተዘጋጀው ፈተና ተ.ቁ. 67፣ በ2005 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ተ.ቁ. 2 ላይ የሰፈሩት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚችል አማራጭ የላቸውም።

የምርጫ ጥያቄዎች አንድ ትክክለኛ መልስ ሊኖራቸው ይገባል። በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት የሰዋስው ጥያቄዎች ውስጥ ከአንድ በላይ መልስን የያዙ ጥያቄዎች ይገኛሉ። ለአስረጅነት በ2002 ዓ.ም. በተሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተራ ቁጥር 42 (አባሪ ለ) ላይ የሰፈረው ጥያቄ እንደሚከተለው ቀርቧል።

> *42. "አዲስ የተወለዱ ሕፃናት አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠር አይችሉም።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሃረጉ የትኛው ነው?*
> *A. አዲስ የተወለዱ*
> *B. አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን*
> *C. አዲስ የተወለዱ ሕፃናት*
> *D. አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠር*

በዚህ ጥያቄ ተፈታኞች በጥያቄው ላይ በተሰጠው አረፍተ ነገር መነሻነት ስማዊ ሀረጉ የትኛው እንደሆነ ለይተው እንዲያመለክቱ የቀረበ ነው። ስማዊ ሀረግ ስምን መሪ አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው። በጥያቄው ዋና ክፍል ላይ በቀረበው አረፍተ ነገር ውስጥ "ሕፃናት" እና "መቆጣጠር" የሚሉትን ስሞች መሪ አድርገው "አዲስ የተወለዱ ሕፃናት" እና "አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠር" የተሰኙት ስማዊ ሀረጋት ተመስርተዋል። በዚህም መሰረት ለጥያቄው ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በምርጫ "B"፣ "C" እና "D" ላይ የቀረቡት መልስ መሆን ይችላሉ። በ2003 ዓ.ም. በተዘጋጀው ፈተና በተ.ቁ. 69፣ በ2004 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና በጥያቄ ተ.ቁ. 23 እና 24፣ በ2005 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና በተ.ቁ. 9 እና 10 ላይ የሚገኙት ጥያቄዎች ከአንድ በላይ ትክክለኛ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን ይዘዋል።

የጥያቄው ዋና ክፍል ሊጠየቅ የተፈለገውን ተገቢውን መረጃ በትክክል አሟልቶ መያዝ ይገባዋል፡፡ በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት ጥቂት የሰዋስው ጥያቄዎች በጥያቄው ዋና ክፍል ላይ ተገቢውን መረጃ በተገቢው መልኩ ያለመያዝ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ለአስረጅነት በ2002 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና ተ.ቁ. 41 ላይ (አባሪ ለ) የቀረበውን ጥያቄ እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

*41. "ወፍራም አካላዊ አገነባብ ያላቸው ልጆች ከጡንቻ ይልቅ ከፍተኛ የሆነ የስብ ቲሹ ይኖራቸዋል፡፡" በሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ከመጠን አንጻር ለመግለፅ የገባው ምን የሚለው ነው?*

| | | | |
|---|---|---|---|
| *A.* | *አካላዊ አገነባብ ያላቸው* | *C.* | *ወፍራም* |
| *B.* | *ከፍተኛ የሆነ የስብ ቲሹ* | D. | ከፍተኛ |

በዚህ ጥያቄ ላይ መመልከት እንደሚቻለው በጥቅስ ምልክት ውስጥ ለሰፈረው አረፍተ ነገር ባለቤት ሆኖ የገባውን መሪ ስም ከመጠን አኳያ የሚገልጸውን ገላጭ ተፈታኞቹ ለይተው እንዲመልሱ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ ተፈታኞች ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት ሁለት መሰረታዊ ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡

የመጀመሪያው ለጥያቄው ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት "የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሆኖ የገባው ስማዊ ሀረግ የትኛው ነው?" የሚለውን የመለየቱ ተግባር ነው፡፡ ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በተዘጋጁት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ "ማንኛውም ዜጋ የሀገሩ ክብርና ልዕልና ሲደፈር ይቆጨዋል፡፡" (ትምህርት ሚኒስቴር 1997ለ፡92) በሚል ዓይነት መንገድ ከቀረቡላቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ ስማዊ ሀረግ ሆኖ የገባውን በመለየት እንዲለማመዱ የቀረቡ አረፍተ ነገሮች ይገኙበታል፡፡ በመልመጃነት ከቀረቡላቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥም ባለቤት ሆኖ የገባው ስማዊ ሀረግ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ስለሚገኝ በቀላሉ መለየት ይችላሉ፡፡ በፈተና ጥያቄው ላይ የቀረበው አረፍተ ነገር ተማሪዎች እንዲማሩ በቀረበው የአገባብ ቅደም ተከተል መሰረት ያልተዋቀረ በመሆኑ የተነሳ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ከተካተቱት ስማዊ ሀረጋት ውስጥ የአረፍተ ነገሩን ባለቤት ነጥሎ ማውጣቱ ከተፈታኞች ደረጃ አኳያ ሲታይ አዳጋች ነው፡፡

ሁለተኛው ችግር በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ያሉትን "ወፍራም" እና "ከፍተኛ" የሚሉትን መጠን አመልካች ቃላት በመለየት ምላሽ ለመስጠት ቢሞክሩ እንኳ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ ያለመኖሩ ጉዳይ ነው፡፡ "ወፍራም አካላዊ አገነባብ ያላቸው ልጆች" በሚለው ሀረግ ውስጥ መሪውን ስም ለመግለጽ የገባው "ወፍራም አካላዊ አገነባብ ያላቸው" የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ በዚህ አዛማጅ አረፍተ ነገር ውስጥ መጠንን ሊገልጽ የገባው ቃል "ወፍራም" የሚለው ሲሆን ገላጭነቱ "አካል" ለሚለው ቃል እንጂ "ልጆች" ለሚለው አይደለም፡፡ "ከፍተኛ" የሚለውም ቃል ስምን ሲገልጽ አይታይም፡፡ በጥያቄው ላይ የሚታየው ችግር ተገቢውን መረጃ ያለመያዝ ብቻ ሳይሆን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚችል አለመገኘቱ ነው፡፡

ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ተፈታኞች ለተጠየቁት ጥያቄ ተገቢውን መልስ በማመዛዘን ይመልሱ ዘንድ በጥያቄው ዋና ክፍል ተገቢው መረጃ በተገቢው መንገድ ተካቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በ2003 በተሰጠው ፈተና (አባሪ ሐ) ጥያቄ ተ.ቁ. 67፣ በ2005 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በተሰጠው ፈተና (አባሪ ሠ) ተ.ቁ. 4፣ 5 እና 21፣ በ2006 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና (አባሪ ረ) ተ.ቁ. 71 ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች የተገቢነት ችግር ለሚታይባቸው ጥያቄዎች አስረጅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙትን ጥያቄዎች ተፈታኞች ምን እንደተጠየቁ ተገንዝበው ተገቢውን መልስ ይሰጡ ዘንድ ጥያቄዎቹ ታትመው ከመሰራጨታቸው በፊት የአርትኦት ስራ በጥንቃቄ እና በተገቢው መልኩ መሰራት ይኖርበታል፡፡ የአርትኦት ችግር በጥያቄው ላይ የግልጽነት ችግር እንዲኖር፣ ጥያቄው አንድ ትክክለኛ መልስ እንዳይኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡ ለዚህም በ2001 ዓ.ም. (አባሪ ሀ) ተ.ቁ. 13 ላይ የቀረበውን ጥያቄ በአስረጅነት መመልከት ይቻላል፡፡

13. *"አስረገፋት" በሚለው ቃል ውስጥ መድረሻ ላይ ያለችው ቅጣይ ምእላድ /-ት/ ________ ትገልጻለች፡፡*

A. *ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ጾታን*

B. *ሰስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ጾታን*

C. *ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ጾታን*

D. *ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ጾታን*

በዚህ ጥያቄ ላይ እንደሚታየው "አስረገፋት" በሚለው ቃል መድረሻ ላይ /-ኧ/ እና /-ኣት/ /አስረገፍ-ኧ-ኣት/ የሚሉት ቅጥያዎች ይገኙበታል፡፡ በጥያቄው ላይ ተፈታኞች እንዲመልሱ የተፈለገው በቃሉ መድረሻ ላይ የሚገኘው ቅጥያ /-ት/ ምንን እንደሚገልጽ ተጠይቀዋል፡፡ በተሰጠው ቃል ላይ ግን መድረሻ ቅጥያ /-ት/ ሳይሆን /-ኣት/ ነው፡፡ በቃሉ መድረሻ ላይ ቅጣይ ምዕላድ /-ት/ ሊገኝ የሚችለው ቃሉ "አስገረፉት" /አስገረፍ-ኡ-ት/ ሲሆን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ችግሮች ከአርትኦት ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ ስለሚችሉ በፈተና ህትመት ወቅት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ በዚሁ ጥያቄ አማራጭ "B" ላይ "ሰስተኛ" የሚለው ከህትመት ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችል ችግር ነው፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ፈተና (አባሪ ሀ) በጥያቄ ተ.ቁ. 12 በዋናው የጥያቄ ክፍል ላይ "የሚኖሮው" ፣ በ2006 ዓ.ም. በተሰጠው ፈተና (አባሪ ረ) ምርጫ "D" ላይ "የመጀመሪዋ" በሚል ሰፍረው የሚገኙት ቃላት ከአርትኦት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ችግሮች ናቸው፡፡

ባጠቃላይ በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ በፈተናዎቹ ውስጥ ተካተው የሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች አስቀድመው በትምህርትነት የቀረበውን የትምህርት ዓላማ መሰረት በማድረግ በፈተናው ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ማካተት ብቻ ሳይሆን ለየይዘቱ የተሰጠውን ትኩረት መሰረት በማድረግ ጥያቄዎቹ ተገቢውን ውክልና በማግኘት መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ተተኳሪ ፈተናዎች በ2.1.6. ስር ከተገለጹት የፈተና መርሆዎች አኳያ ጠንካራ እና ደካማ ጎን ይታይባቸዋል፡፡ በቀጣይ በሚዘጋጁት ፈተናዎች ውስጥ ከላይ የተገለጹት ደካማ ጎኖች እንዳይከሰቱ የምርጫ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የፈተና መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ሊቀረጹ ይገባል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ተዘጋጅተው በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ መተንተን ነበር፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ፈተናዎች ውስጥ ምን ምን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተካተዋል? በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶችና መማሪያ መጽሐፎች ውስጥ ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አንጻር ሲታዩ በየፈተናዎቹ ውስጥ የትኞቹ የሰዋስው ይዘቶች ተካተዋል? በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት የፈተና መመዘኛ መስፈርትን ያሟሉ ናቸውን? ተተኳሪ ፈተናዎች ከፈተና መርሆዎች አኳያ ምን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ይታይባቸዋል? የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል፡፡

በስድስቱ ዓመታት በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በተዛማጅ ጽሁፍ ክፍል ውስጥ የተነሱትን ንድፈ ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ዓይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡

በጥናቱም በተገኘው ፍተሻ መሰረት በስድስቱ ዓመታት የተሰጡት ፈተናዎች እያንዳንዳቸው ዘጠና ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ ተተኳሪ ፈተናዎች ባጠቃላይ አምስት መቶ አርባ (540) ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆኑ፣ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ብዛት አንድ መቶ ሃምሳ አራት (28.52%) ነው፡፡

በስድስቱም ዓመታት በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የቋንቋን አጀማመርና ባህርያት፣ ስነ-ድምጽን፣ ስነ-ምዕላድን፣ ስነ-አገባብን እና ስነ-ፍችን የሚመለከቱ ዋና ዋና ይዘቶች ተካተዋል፡፡ በነዚህ ዋና ዋና ይዘቶች ውስጥ ከሚገኙት ንዑሳን ይዘቶች ውስጥ በስድስቱም ዓመታት በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የቋንቋ ባህርያትን፣ የድምጽ መጥበቅና መላላትን፣ ነጻ እና ጥገኛ ምእላድን፣ የእርባታ ምዕላድን ተግባር፣ የሀረግ ዓይነትን፣ የስምና የግስ ገላጭን፣ የቃላትን እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍችን የሚወክሉ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ተካተውባው ይገኛሉ፡፡

የቋንቋ አጀማመርን የሚወክል ሰዋስዋዊ ይዘት በ2001 ዓ.ም.፣ በ2002 ዓ.ም. እና በ2003 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ፣ የአረፍተ ነገር ስልትን የሚወክል ጥያቄ ደግሞ በ2003፣ በ2005 እና በ2006 ዓ.ም በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ ሲገኝ በሌሎቹ ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ግን ወካይ ጥያቄ አልተካተተባቸውም፡፡ የ2001 ዓ.ም. ፈተና የአረፍተ ነገር ባለቤትንና ተሳቢን፣ የ2002 ዓ.ም. ፈተና የምዕላድንና የቃልን እንድነት፣ የ2003 ዓ.ም. ፈተና ሰዋስዋዊ ስህተትን፣ የ2004 ዓ.ም. ፈተና ጥምር ቃልን፣ የ2005 ዓ.ም. ፈተና የቃላትን ተቃራኒ ፍች የሚወክሉ ጥያቄዎች የተካተቱ ሲሆኑ በሌሎቹ ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ግን ይዘቶቹን የሚወክሉ ጥያቄዎች አልተካተቱባቸውም፡፡ ተገቢውን ቃል በአረፍተ ነገር ውስጥ የመጠቀምን ይዘት የሚወክሉ ጥያቄዎች በ2002 ዓ.ም. እና በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጁት ፈተናዎች፣ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ በአገባብ ቅደም ተከተላቸው ማደራጀትን የሚወክሉ ጥያቄዎች በ2001 ዓ.ም. እና በ2004 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች፣ አያያዥ ቃልን የሚወክል በ2001 ዓ.ም. እና በ2003 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ ሲሆኑ በሌሎቹ ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ግን ይዘቶቹን የሚወክሉ ጥያቄዎች አልተካተቱም፡፡

የቃል ክፍልን የሚወክል ጥያቄ በ2005፣ የቃል ምስረታን የሚወክል በ2003 ዓ.ም.፣ ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገርን የሚመለከት በ2002 ዓ.ም.፣ የቃላት

አገባባዊ ፍችን የሚመለከት በ2003 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ ያልተካተቱ ሲሆኑ፣ በሌሎቹ ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ግን ይዘቶቹን የሚወክሉ ጥያቄዎች ይገኙባቸዋል፡፡

በየፈተናዎቹ ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ከተተኳሪ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት አንጻር ሲታዩ በፈተናዎቹ ውስጥ የቋንቋ ባህርያትን፣ የድምጽ መጥበቅና መላላትን፣ ነጻ እና ጥገኛ ምዕላድን፣ የዕርባታ ምዕላድን ተግባር፣ የሀረግ ዓይነትን፣ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች የሚወክሉ ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡

በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት ሰዋስዋዊ ይዘቶች አንጻር በ2003 ዓ.ም.፣ በ2004 ዓ.ም. እና በ2006 ዓ.ም. የቋንቋን አጀማመርን የሚወክሉ ጥያቄዎች አልተካተቱም፡፡ በ2001 ዓ.ም.፣ በ2002 ዓ.ም.፣ በ2003 ዓ.ም.፣ በ2004 ዓ.ም. እና 2006 ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ የቃላትን ተቃራኒ፣ በ2002 ዓ.ም. ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገርን፣ በ2005 ዓ.ም. የቃል ክፍልን፣ በ2003 ዓ.ም. የቃል ምስረታን፣ በ2003 ዓ.ም. የቃላት አገባባዊ ፍቺን የሚወክሉ ጥያቄዎች ያልተካተቱ ሲሆኑ በሌሎቹ ተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ፡፡ በ2001 ዓ.ም.፣ በ2002 ዓ.ም.፣ በ2003 ዓ.ም. እና በ2005 ዓ.ም. ፈተናዎች ውስጥ ጥምር ቃልን የሚወክል ይዘት ያልተካተተ ሲሆን፣ በ2001 ዓ.ም.፣ በ2002 ዓ.ም.፣ በ2004 ዓ.ም.፣ በ2005 ዓ.ም. እና 2006 ዓ.ም. ፈተናዎች ሰዋስዋዊ ስህተት የሚወክል ጥያቄ አልተካተተባቸውም፡፡

በ2002 ዓ.ም. ፈተና የምዕላድንና የቃልን አንድነት እና የስም መሙያን፣ በ2003 ዓ.ም. ፈተና የአረፍተ ነገር ስልትን፣ በ2006 ዓ.ም. ፈተና ደግሞ የስምና የግስ ገላጭን የሚወክሉ ይዘቶች በተተኳሪ መርሀ ትምህርቶች እና መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያልተካተቱ ይዘቶች በተጠቀሰው ዓ.ም. በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ ግን ተካተው ይገኛሉ፡፡

ፈተናዎች ሲዘጋጁ የፈተና መስፈርትን መሰረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ከፈተና መስፈርቶች ውስጥ አንዱ የይዘት ተገቢነት ሲሆን በተተኳሪ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተሰጣቸው የትኩረት ደረጃ አኳያ ሲታዩ ሰዋስዋዊ ጥያቄዎቹ ተገቢውን ውክልና ያለማግኘት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ተተኳሪ ፈተናዎች ከፈተና መርሆዎች አኳያ ሲቃኙ ጠንካራ ጎናቸው አይሎ ቢገኝም እንኳ ደካማ ጎን ተስተውሎባቸዋል፡፡

## 5.2. አስተያየት

የቋንቋ ፈተናዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ፈተናዎቹ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ማድረስ ይችሉ ዘንድ፣ በፈተና የተፈለገውን መረጃ ማግኘት ያስችል ዘንድ የሚዘጋጁት ፈተናዎች የፈተና መመዘኛ መስፈርቶችንና መርሆዎችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ በጥናቱ ላይ ተተኳሪ በሆኑ ፈተናዎች ውስጥ በተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት ላይ ድክመቶች ይታያሉ፡፡ በፈተናዎቹ ላይ የታዩትን ጠንካራ ጎኖች አጠናክሮ በመቀጠል ድክመቶቹ ግን በቀጣይ በሚዘጋጁ ፈተናዎች እንዳይደገሙ ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡ እነሱም፡-

- በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ ተካተው የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች አስቀድመው ተማሪዎች የተማሯቸውን የሰዋስው ይዘቶች መነሻ በማድረግ የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ ለየይዘቶቹ የተሰጠውን የትኩረት ደረጃ መሰረት በማድረግ ወካይ ጥያቄዎች በፈተና ውስጥ ቢካተቱ፣
- የምርጫ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ተፈታኞች ለተጠየቁት ጥያቄ ተገቢውን መልስ መመለስ ይችሉ ዘንድ ተገቢ የሆኑ ጥያቄዎችን በተገቢው መንገድ በማዋቀር ቢዘጋጁ፣

- ተፈታኞች ለጥያቄዎቹ በግምት ምላሽ እንዳይሰጡ፣ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተገቢውን መልስ በማመዛዘን፣ በመመራመር ይመልሱ ዘንድ በአማራጭነት የሚቀርቡት ትክክለኛና አሳሳች መልሶች በሰዋስዋዊ ቅርጻቸው፣ በቃላት መጠናቸው ተመጣጣኝ በሆነ መልክ ቢዘጋጁ፣
- ለጥያቄው በአማራጭነት የሚዘጋጁት ምላሾች አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ እንዲይዙ ቢደረግ፣
- አላስፈላጊ ድግግሞሾች ቢወገዱ፣

የሚሉት አስተያየቶች ጥናቱ ሲጠናቀቅ በተተኳሪ ፈተናዎች ላይ ከታዩ ድክመቶች በመነሳት በአጥኚው የቀረቡ ናቸው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

ሀገር አቀፍ የፈተናዎች ድርጅት:: (1994):: *የትምህርት ተከታታይ ምዘናና ግምገማ መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳቦችና ቴክኒኮች*፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

መሠረት አለማየሁ፡፡ (2005)፡፡ “በትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው ከ1999 እስከ 2004 ዓ.ም. በተሰጡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘት እና አቀራረብ ግምገማ፡፡” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ሙሉፀሐይ ገነት፡፡ (2005)፡፡ “ከ2001 — 2004 ዓ.ም. በተሰጡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሞዴልና ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ በቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች መካከል ያለ የይዘትና የአቀራረብ ዝምድና በአማራ ክልል ሰሜን አቸፈር ወረዳ በተመረጡ ሶስት ት/ቤቶች ናሙናነት፡፡” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ማረው ዓለሙ፡፡ (2003)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*፡፡ 2ኛ እትም፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ ፕሪንተርስ፡፡

በለጠ ያዕቆብ፡፡ (1995)፡፡ “ለዘጠነኛ ክፍል የሚዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃ ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት አግባብነት እና ያጠያየቅ ብቃት ትንተና፡፡” ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ባየ ይማም፡፡ (1987)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው*፡፡ አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ.፡፡

ተስፋ አከለ። (2000)። "የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ታለጌታ ይመር። (2005)። "በሀገር መከላከያ ሠራዊት ከ2001 — 2004 ዓ.ም. ድረስ ለርቀት ትምህርት መርሐ ግብር የቀረቡ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ ፈተናዎች ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያላቸው ዝምድና።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ትምህርት ሚኒስቴር። (1993 ዓ.ም.፣ ሐምሌ)። "ቆይታ ከትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር።" *ከትምህርት ዓለም*፣ ቅፅ 2፣ ቁ.2፣ ገጽ 28-43።

_________። (1994)። *የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

_________። (1996ሀ)። የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዘጠነኛ ክፍል። ተሻሽሎ የወጣ። አዲስ አበባ፣ ያልታተመ።

_________። (1996ለ)። የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት አሥረኛ ክፍል። ተሻሽሎ የወጣ። አዲስ አበባ፣ ያልታተመ።

_________። (1997ሀ)። *አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ ዘጠነኛ ክፍል*። ተሻሽሎ የወጣ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

_________። (1997ለ)። *አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ አሥረኛ ክፍል*። ተሻሽሎ የወጣ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

__________:: (2004ሀ):: *አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ ፱ኛ ክፍል*:: ዱባይ፣ አል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት::

__________:: (2004ለ):: *አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ ፲ኛ ክፍል*:: ዱባይ፣ አል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት::

ትንሳኤ ብርሐኔ:: (1988):: "የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት::" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)::

አለም እሸቱ:: (1992):: *መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ*:: አዲስ አበባ፣ የቅድስተ ማርያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋካልቲ ህትመት::

አበበች ገብሩ:: (2004):: "ከ1998 — 2003 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ::" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)::

ወንድማገኝ አደም:: (2005):: "ከ2001 — 2004 ዓ.ም. የተሰጡ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገር አቀፍ እና ሞዴል ፈተናዎች ይዘትና አቀራረብ ንጽጽር በጋምቤላ ክልል በሁለት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መነሻነት::" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)::

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት:: (1985):: *አጠቃላይ የትምህርት ሥልጠና ረቂቅ ፖሊሲ ማብራሪያ*፡ አዲስ አበባ፣ ቼምበር ማተሚያ ቤት::

ያለው እንዳወቀ። (2004)። *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡* ሦስተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። (1990)። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ* ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ጠጅቱ በሬቻ። (1999)። "በአዲስ አበባ ከተማ በግል እና በመንግስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አገር አቀፍ ፈተና ውጤቶች ንጽጽር።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ፀጋዬ ግርማ። (1997)። "በ1995 እና በ1996 ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል መምህራን ስልጠና የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተናዎች ግምገማ በተመረጡ የአማራ ክልል መምህራን ኮሌጆች መነሻነት" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

Alderson, J.C., Clapham, C. and Wall, D. (1995). *Language Test Construction and Evaluation*. Cambridge: Cambridge University Press.

Bachman, L.F. (1990). *Fundamental Consideration in Language Testing*. Oxford: Oxford University Press.

Bachman, L.F. and Palmer, A.S. (1996). *Language Testing in Practice*. Oxford: Oxford University Press.

Braun, H. and Kanjee, A. (2006). "Using Assessment to Improve Education in Developing Nations." *Improving Education*

*Through Assessment, Innovation, and Evaluation*. (pp.1-46). Cambridge: American Academy of Arts and Sciences.

Brinton, L.J. (2000). *The Structure of Modern English*. Amsterdam: John Benjamins Publishing Company.

Brown, H.D. (2004). *Language Assessment Principles and Classroom Practices*. New York: Pearson Education, Inc.

Brown, J.D. (1996). *Testing in Language Programs*. New Jersey: Prentice Hall Regents.

Cheng, L. and Watanabe, Y. (Ed.). (2004). *Washback in Language Testing*. New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates, Inc.

Chesla, E.L. (2002). *TOEFL Exam Success From Learning Express in Only 6 Strategic Steps*. New York: Learning Express, LLC.

Fulcher, G. and Davidson, F. (2007). *Language Testing and Assessment*. New York: Routledge Taylor & Francis Group.

Harmer, J. (2001). *The Practice of English Language Teaching*. 3rd ed. London: Pearson Education Limited.

Heaton, J.B. (1988). *Writing English Language Tests*. New York: Longman Group UK Limited.

Henning, G. (1987). *A Guide to Language Testing.* Cambridge, Mass: Newbury House.

Hughes, A. (1989). *Testing for Language Teachers*. Cambridge: Cambridge University Press.

Hughes, A. (2003). *Testing for Language Teachers.* 2nd ed. Cambridge: Cambridge University Press.

Madsen, H.S. (1983). *Techniques in Testing*. Oxford: Oxford University Press.

Mulu Nega and Daniel Tefera. (2005). "Introduction To Measurement and Evaluation." Prepared for Psyc.211 Modules 1-3. Addis Ababa Univerisity.

Murthy, J.D. (2006). *Contemporary English Grammar for Scholars and Students*. New Delhi: Sanjeev Offset Printers.

Thorndike, R.L. and Hagen, E.P. (1977). *Measurement and Evaluation in Psychology and Education*. 4th ed. New Delhi: Wiley Eastern Limited.

Todd, L. (1987). *An Introduction to Linguistics*. Singapore: Longman York Press.

Weir, C.J. (2005). *Language Testing and Validation*. Basingstoke: Palgrave.

# አባሪ ሀ

## ከ2001ዓ.ም. ከሀገር አቀፍ ፈተና የተወሰዱ የሰዋስው ይዘት ጥያቄዎች

## GENERAL EDUCATION QUALITY ASSURANCE AND EXAMINATIONS AGENCY (GEQAEA)

## ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE AMHARIC EXAMINATION

## GINBOT 2001 / MAY 2009

**BOOKLET CODE: 81**

## የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

## ግንቦት 2001 ዓ.ም

**የዚህ ጥራዝ መለያ፡- 81**

**መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 22 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። በመሆኑም ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።**

1. የቋንቋን አመጣጥ በተመለከተ ከሚከተሉት አመለካከቶች መካከል ተቀባይነት ያለው የትኛው ነው?
   A. ቋንቋ ለሰው ልጅ ከፈጣሪ የተሰጠ ፀጋ ነው።
   B. የሰው ልጅ በስራ ሂደት ቋንቋን ፈጠረ።
   C. የሰው ልጅ በቋንቋ መጠቀም የጀመረው በኩረጃ ነው።
   D. የሰው ልጅ ቋንቋን ከዝንጀሮ መሰል እንስሳ ተማረ።

2. በቃላት አደራደር ስርዓቱ መልእክት ለማስተላለፍ ተመራጭ የሚሆነው አረፍተ ነገር _______________ ነው?

   A. ሰው ሳይተው እሱነቱን በጥበብ መሳሪያነት ኑሮውንና ህይወቱን ያሻሽላል፤ያሳምራል፡፡

   B. በጥበብ መሣሪያነት እሱነቱን ኑሮውንና ህይወቱን ሰው ሳይተው ያሻሽላል፤ያሳምራል፡፡

   C. ሰው እሱነቱን ሳይተው ኑሮውንና ህይወቱን በጥበብ መሣሪያነት ያሻሽላል፤ያሳምራል፡፡

   D. በጥበብ መሣሪያነት ሰው ኑሮውንና ህይወቱን ያሻሽላል፤ያሳምራል እሱነቱን ሳይተው፡፡

3. "ገበሬው ማሳውን በሚገባ አርሶ አለሰለሰው፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ በተሳቢነት የገባው ቃል የትኛው ነው?

   A. ገበሬው C. አርሶ

   B. በሚገባ D. ማሳውን

4. እንደ "ራዕይ ፣ ህዳሴ ፣ ሚሊኒየም ፣ ኮምፒዩተር ፣ ዲሞክራሲ ..." ያሉት ቃላት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ገብተው ማገልገላቸው ከቋንቋ ባህርይ አንጻር ምን ሊያስረዳን ይችላል?

   A. የቋንቋን ምሉእነት C. የቋንቋን ዘፈቀዳዊነት

   B. የቋንቋን ተዋዋሽነት D. የቋንቋን አንደበታዊነት

5. "ተባበሩባቸው" በሚለው ቃል ውስጥ የመተባበሩን ተግባር የፈፀሙት እነሱ መሆናቸውን የሚያመለክተው ቅጣይ ምእላድ የትኛው ነው?

   A. /-ኡ/ C. /-ቸ/

   B. /-ባቸው/ D. /-ኣቸው/

6. "ምንዱባን" በሚለው ቃል ውስጥ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጣይ ምእላድ የትኛው ነው?

   A. /-ኡ/ C. /-ን/

   B. /-ባን/ D. /-ኣን/

7. "በሥራ ባልደረቦቹ ድጋፍ የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ ሆነ።" በሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ማን ነው?

A. በሥራ ባልደረቦቹ C. እሱ

B. በሥራ ባልደረቦቹ ድጋፍ D. እነሱ

8. ከሚከተሉት ቃላት መካከል አንዱ /-ኣም/ን መድረሻ ላይ መቀጠል ይችላል።

A. አመል C. ቁማር

B. ነገር D. መልክ

9. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ለምስርት ቃል ምሳሌ **አይደለም** ።

A. ብልግና C. ጉልበተኛ

B. ሰውነት D. ወታደሩን

10. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ጥገኛ ምእላዶችን በውስጡ የያዘ ቃል ነው።

A. ምርቃት C. ወረቀት

B. ምራቅ D. መሃረብ

11. _________ በመነሻውና በመድረሻው ላይ ቅጣይ ምእላዶች **የሌሉት** ቃል ነው።

A. አስተባበረ C. አይበላም

B. አልመጣም D. አውራሪስ

12. "መ" ላልቶና ጠብቆ በመነበቡ ምክንያት ፣ "ይመራል" የሚለው ቃል የተለያየ ፍቺ የሚኖሮው በየትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. የዘንድሮው የገበያ ዋጋ እጅግ ይመራል።

B. የኢትዮጵያ ብሄራዊ የእግር ኳስ ቡድን አንድ ለዜሮ ይመራል።

C. መድሃኒቱ በጣም ይመራል።

D. ልጁ ማየት የተሳነውን ወጣት ይመራል።

13. "አስረገፋት" በሚለው ቃል ውስጥ መድረሻ ላይ ያለችው ቅጣይ ምእላድ /-ት/ _________ ትገልጻለች።

A. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ጾታን

B. ሰስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ጾታን

C. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ጾታን

D. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ጾታን

14. "ደኖቻችን" በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ቅጣይ ምእላዶች ከይዘት አንፃር ____________ ያመለክታሉ፡፡

A. ድርጊትንና ጉዳይን C. ብዛትንና ባለገንዘብነትን

B. አይነትንና መጠንን D. ብዛትንና ግብርን

15. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ ተራ አረፍተ ነገር ነው፡፡

A. ወንድሜ ወደ ውጪ ሃገር ዛሬ ጠዋት ሄደ፡፡

B. ለምለም ከገበያ ስትመጣ አገኘኋት፡፡

C. ለማ ትናንት ያጠበውን ልብስ ለበሰ፡፡

D. ደመቀ ወንድሙን ስሞ ተሰናበተው፡፡

16. "ግብርና <u>የትጉህ ሰው ስራ</u> ነው፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምሳሌነቱ ለየትኛው ሃረግ ነው?

A. ለቅጽላዊ C. ለስማዊ

B. ለግሳዊ D. ለመስተዋድዳዊ

17. "ኢትዮጵያ የአበባ ምርቶቿን ለአለም <u>ገበያ</u> አቀረበች፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምንድነው?

A. ስም C. ቅጽል

B. ግስ D. ተውሳከ ግስ

18. "ኢትዮጵያውያን በረጅም ርቀት ሩጫ የበላይነትን <u>እንደገና</u> አገኙ፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ______________ ነው፡፡

A. ስም C. ቅጽል

B. ተውሳከ ግስ D. መስተዋድድ

19. "ጠይም ፀጉረ ዞማ ሰው በጣም እወዳለሁ፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ____________ የስም ገላጭ ነው፡፡

A. ጠይም ፀጉረ ዞማ ሰው C. ዞማ ሰው

B. ጠይም ፀጉረ D. ጠይም ፀጉረ ዞማ

20. "ታላቅ ወንድሜ ዛሬ ከጎጃም ይመጣል፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ____________ የግስ ገላጭ ነው፡፡

A. ታላቅ ወንድሜ ዛሬ ከጎጃም C. ዛሬ ከጎጃም ይመጣል

B. ወንድሜ ዛሬ ከጎጃም D. ዛሬ ከጎጃም

21. "ታላቁ የሳይንስ ሊቅ አልበርት አንስታይን የፊዚክሱን ሳይንስ ከዳር ያደረሰ ነው፡፡" የሚለው አረፍተ ነገር ግሳዊ ሃረግ የትኛው ነው?

A. የፊዚክሱን ሳይንስ ከዳር ያደረሰ

B. ያደረሰ ሰው ነው

C. የፊዚክሱን ሳይንስ ከዳር ያደረሰ ሰው ነው

D. አልበርት አንስታይን የፊዚክሱን ሳይንስ ከዳር ያደረሰ ሰው ነው

22. ከሚከተሉት መካከል አንዱ ለውስብስብ አረፍተ ነገር ምሳሌ ነው፡፡

A. በፈተና አዳራሹ ውስጥ ያሉት ተፈታኞች በመብዛታቸው ክፍሉ ተጨናንቋል፡፡

B. በፈተና አዳራሹ ውስጥ በርካታ ተፈታኞች አሉ፡፡

C. የፈተና አዳራሹ በተፈታኞች ተጨናንቋል፡፡

D. በፈተና አዳራሹ ውስጥ ተፈታኞች በረድፍ በረድፍ ተቀምጠዋል፡፡

**መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 44 እስከ ጥያቄ 55 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡**

29. "የመጀመሪያ ልጄ መወለዱን ስሰማ እጅግ በጣም ተደሰትኩ፡፡ ምክንያቱም የበኩር ልጄ ወንድ እንዲሆን እመኝ ስለነበር ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሚኖረኝ የወንድ ልጅ ብዛት ካንድ እንዲበልጥ አልፈልግም፡፡ ስለዚህ የሁለተኛ ልጄ ጾታ ምን ቢሆን ልደሰት እንደምችል መገመት ትችላላችሁ፡፡"

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ከመጀመሪያው አረፍተ ነገር ወደ ሁለተኛው አረፍተ ነገር መሸጋገሪያ ሆኖ ያገለገለው __________ ነው፡፡

A. እጅግ በጣም ተደሰትኩ C. ምክንያቱም

B. ተደሰትኩ D. ምክንያቱም የበኩር ልጄ

***መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 69 እስከ 90 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ፡፡***

85. “ሰነፍ ተማሪ በፈተናው ሰዓት ያምጣል፡፡” በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ በፍካሬያዊ ፍቺው የገባው ቃል የትኛው ነው?

A. ሰነፍ፡ C. ያምጣል

B. ሰነፍ ተማሪ D. በፈተና ሰዓት

86. “አነሳ” የሚለው ቃል “አማ” የሚል ፍቺ የሚይዘው በየትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. እሱ የሰው ስም በከንቱ አነሳ፡፡

B. አዝማሪው የሰዎችን ስም እያነሳ ሲዘፍን ነበር፡፡

C. ልጅቷ ራስ አሉላን የመሰሉ ጀግኖችን በግጥም አነሳች፡፡

D. የፕሮፌሰሩ ንግግር ሚዛን አነሳ፡፡

90. “ብርሃን” የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍቺ የገባው በየትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. ወገኖቻችንን የእውቀት ብርሃን ልናሳያቸው ይገባል፡፡

B. በቂ ብርሃን በሌለበት ቦታ ማንበብ በዓይናችን ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡

C. እኛ ተማሪዎች በትምህርት ብርሃን ዓለምን መጎብኘት ችለናል፡፡

D. መምህራን የድንቁርናን ጨለማ በእውቀት ብርሃን ይገፉታል፡፡

# አባሪ ለ

## ከ2002 ዓ.ም. ከሀገር አቀፍ ፈተና የተወሰዱ የሰዋስው ይዘት ጥያቄዎች

## GENERAL EDUCATION QUALITY ASSURANCE AND EXAMINATIONS AGENCY (GEQAEA)

## ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE AMHARIC EXAMINATION

## GINBOT 2002/JUNE 2010

BOOKLET CODE: 81

## የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

## ግንቦት 2002 ዓ.ም

**የዚህ ጥራዝ መለያ፡- 81**

**መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 ድረስ ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጭ/ምረጥ፡፡**

1. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በሚሰጠው ፍቺ የሚለየው የትኛው ነው?

   A. ረግረግ　　C. ድጥ

   B. አረንቋ　　D. ማጥ

5. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ "እየቀዱ" የሚለውን ቃል አማሬያዊ ፍቺ ያመለክታል፡፡

   A. ሰነፍ ተማሪዎች ፈተና እየቀዱ ለማለፍ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

   B. ሴቦቹ ወሬያቸውን እየቀዱ እያሉ በፀጥታ ኃይሎች ተያዙ፡፡

C. የሰዎችን ምስጢር እየቀዱ ለሌላው ማስተላለፍ የእኩዮች ተግባር ነው፡፡

D. ጎረቤቶቻችን ውሃ ከምንጭ እየቀዱ ሲጠቀሙ ጥንቃቄ ያድርጋሉ፡፡

6. “እንጀራ” የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው አረፍተ ነገር ነው?

A. ልጅቷ እንጀራ እየጋገረች ነው፡፡

B. ወንድማችን እንጀራ ፍለጋ ከአገር አገር ይዞራል፡፡

C. ዛሬ እንጀራ የመብላት ፍላጎት የለኝም፡፡

D. እንጀራ በወጥ የተለመደ ኢትዮጵያዊ ምግብ ነው፡፡

7. “አይን” የሚለውን ቃል እማሬያዊ ፍቺ ለማሳየት የሚመረጠው __________ ነው፡፡

A. አይኗ የብረት አሎሎ ይመስላል፡፡

B. አንዳንዱ ሰው ጉቦ ሲበላ አይን የለውም፡፡

C. እመቤት የቤታችን አይን ስለሆነች እንወዳታልን፡፡

D. ሾፌሩ በመንግስት መኪናና ነዳጅ ሲጠቀም አይን የለውም፡፡

8. “አይገባም” የሚለው ቃል “ተገቢ አይደለም” የሚል ፍቺ እንዲኖረው የትኛው አረፍተ ነገር ተመራጭ ነው?

A. ልጁ ክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ አይገባም፡፡

B. መምህሩ፣ “ህፃናትን ማስፈራራት አይገባም” ብለው ተናገሩ፡፡

C. ክብደት የሌለው ነገር ይንሳፈፋል እንጂ፣ ውሃ ውስጥ አይገባም፡፡

D. እሱ በሰው ነገር ውስጥ ዝም ብሎ አይገባም፡፡

9. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በአንዱ “ይፈሳል” የሚለው ቃል “ይወርዳል” የሚል ፍቺ ይኖረዋል፡፡

A. በቀጣዩ አመት ለሚሰሩ መንገዶች ብዙ ብር ይፈሳል ተባለ፡፡

B. ሱሌማን ምን በመሰለች መኪና ይፈሳል፡፡

C. ቧንቧው ባለመዘጋቱ ውሃው ይፈሳል፡፡

D. በበአል ጊዜ የእኔ ቢጤው በየቤተ እምነቱ ዙሪያ ይፈሳል፡፡

10. "ማርታ ስለቸኮለች ቆሎውን __________ አደረገች፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ለባዶ ቦታው ተገቢነት ያለው የትኛው ነው?

A. ዋጥ ዋጥ C. ጎረስ ጎረስ
B. ቃም ቃም D. አኘክ አኘክ

**መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 29 እስከ 45 ድረስ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡**

29. የሰው ልጅ የቋንቋ ባለቤት የሆነው __________ ነው፡፡

A. በተፈጥሮ ፀጋ C. ከወላጆቹ ወርሶ
B. በስራ ሂደት D. ከእንስሳት ተውሶ

30. ከሚከተሉት አንዱ የቋንቋ ባህርይ ነው፡፡

A. ሰብአዊነት C. አይለወጤነት
B. ግላዊነት D. ዘረኝነት

31. "ዳገቱን ወጥተን <u>ደልዳላ</u> ሜዳ ላይ ስንደርስ ቤቱን አገኘነው፡፡" በሚለው የተሰመረበት ቃል ትክክለኛ ፍቺ እንዲኖረው ጠብቆ መነበብ ያለበት ድምፅ በየትኛው ሆሄ ውስጥ ይገኛል?

A. ዳ C. ደ
B. ላ D. ል

32. "አለሚቱ ደብረ ብርሃን <u>ሰንብታ</u> መጣች፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት የትኛውን ያመለክታል?

A. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታን
B. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታን፡፡
C. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ፆታን፡፡
D. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ፆታን፡፡

33. "በከብት እርባታ የሚተዳደር ገበሬ አርብቶ አደር ተብሎ ይጠራል፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ግሳዊ ሃረጉ __________ ነው፡፡

A. ገበሬ አርብቶ አደር ተብሎ ይጠራል

B. በከብት እርባታ የሚተዳደር ገበሬ

C. የሚተዳደር ገበሬ አርብቶ አደር

D. አርብቶ አደር ተብሎ ይጠራል

34. "በጣም ግዙፍ ሰውነት ያላቸው ሰዎች ሩጫ ይከብዳቸዋል፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት __________ ነው፡፡

A. የአረፍተ ነገሩ ባለቤት C. ስማዊ ሃረግ

B. ቅጽላዊ ሃረግ D. መስተዋድዳዊ ሃረግ

35. "ሰውየው ከባሌ እስከ አዲስ አበባ በእግሩ መጣ፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምንድን ነው?

A. ስማዊ ሃረግ C. መስተዋድዳዊ ሃረግ

B. ቅፅል D. ነፃ ምእላድ

36. "አቶ ከበደ ኃይለኛ ውሻ ነክሷቸው ክፉኛ ታመዋል፡፡" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምንን ያመለክታል?

A. ስም C. ተውሳከ ግስ

B. ግስ D. መስተዋድድ

37. እንግሊዝኛ ከአማርኛ የበለጠ ዕድገትና ግልጋሎት ሊኖረው የቻለበት ምክንያት ምንድን ነው?

A. የተቀደሰ ቋንቋ በመሆኑ

B. ለመናገር አመቺነት ያለው ቋንቋ በመሆኑ

C. በአለም የተወደደ ቋንቋ በመሆኑ

D. ቋንቋው በስልጣኔና በቴክኖሎጂ የዳበረ በመሆኑ

38. "ፀሃፊያን" በሚለው ቃል ውስጥ የብዜት አመልካች ሆኖ የገባው የትኛው ቅጥያ ነው?

A. -ያን C. -ኣን

B. -ያ D. -ን

39. ከሚከተሉት ውስጥ ለነፃ ምእላድ ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ቤት C. ቤታችን

B. ቤቱ D. ቤቶች

40. "በግ" ምእላድም ቃልም ነው እንዲባል ያስቻለው ምንድን ነው?

A. ከእሱ ወዳነሱ አሃዶች ሊከፈል የማይችል መሆኑ
B. ፍች ያለው አሃድ መሆኑ
C. በቃልነቱ ባንዱ የቃል ክፍል የሚመደብ መሆኑ
D. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

41. "ወፍራም አካላዊ አገነባብ ያላቸው ልጆች ከጡንቻ ይልቅ ከፍተኛ የሆነ የስብ ቲሹ ይኖራቸዋል።" በሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ከመጠን አንፃር ለመግለፅ የገባው ምን የሚለው ነው?

A. አካላዊ አገነባብ ያላቸው
B. ከፍተኛ የሆነ የስብ ቲሹ
C. ወፍራም
D. ከፍተኛ

42. "አዲስ የተወለዱ ሕፃናት አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠር አይችሉም።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሃረጉ የትኛው ነው?

A. አዲስ የተወለዱ
B. አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን
C. አዲስ የተወለዱ ሕፃናት
D. አካላዊ እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠር

43. ከሚከተሉት ስማዊ ሃረጎች መካከል መሪው ስም የተሰራበትን ነገር የሚጠቁመው __________ ነው።

A. የወሎ ጤፍ
B. የወለጋ ቅቤ
C. የጎጃም ማር
D. የስንዴ ዳቦ

44. "የአንደኛነት ደረጃዋን ያልለቀቀችው አቦዘነች የነፃ ትምህርት እድል አጋጠማት።" በሚለው አረፍተ ነገር የባለቤት ገላጩ ምንድን ነው?

A. የአንደኛነት ደረጃዋን
B. የአንደኛነት ደረጃዋን ያልለቀቀችው
C. የነፃ ትምህርት እድል
D. አቦዘነች የነፃ ትምህርት እድል አጋጠማት

45. ከሚከተሉት ውስጥ ቅፅል ብለን ለምንጠራው የቃል ክፍል የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. ክፉኛ
B. ትሁት
C. ቀረፈ
D. ህይወት

# አባሪ ሐ

## ከ2003 ዓ.ም. ከሀገር አቀፍ ፈተና የተወሰዱ የሰዋስው ይዘት ጥያቄዎች

NATIONAL AGENCY FOR EXAMINATIONS (NAE)

ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE AMHARIC EXAMINATION

GINBOT 2003/JUNE 2011

BOOKLET CODE: 83

## የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና

## ግንቦት 2003 ዓ.ም

**የዚህ ጥራዝ መለያ፡- 83**

***መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 1 እስከ 12 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡***

6. "ጎጆ" የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው አረፍተነገር ነው?

   A. የበሽታ አይነቶች በውሂብ ላይ ጎጆ ሠርተዋል፡፡

   B. ውሂብ የቀለሳት ጎጆ ከሩቅ ትታያለች፡፡

   C. የጎጆዋ ዙሪያ በእሾህ ታጥሯል፡፡

   D. ጎጆዋ እጥር ምጥን ብላ ታምራለች፡፡

8. "ቃሪያ" የሚለውን ቃል እማሬያዊ ፍቺ የሚያሳየው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. አለሙ ገና በቃሪያ እድሜው በደባል ሱሶች ተጠምዷል፡፡

B. ከቀረበው ምግብ ሁሉ በጣም የጣፈጠኝ ቃሪያው ነበር፡፡

C. አስተሳሰቡ ቃሪያ የሆነ ሰው ለራሱም ሆነ ለሀገር አይበጅም፡፡

D. ምንተስኖት ልጁን በቃሪያ ጥፊ አላሰው፡፡

10. "ትከሻ" የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው አረፍተነገር ነው?

A. ወንድሙ በትከሻው ላይ መፃህፍቱን ተሸክሟል፡፡

B. ነፃነት ዛሬም በቤተሰቦቿ ትከሻ ላይ ናት፡፡

C. ዘመኑና እድገት ትካሻ ለትከሻ ተያይዘው ይታገላሉ፡፡

D. ነጋሽ ትከሻው ላይ እባጭ ወጣበት፡፡

11. "የሴትየዋ ንግግር መርዝ ነው፤ እያደር ይቆጠቁጣል፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ፍካሬያዊ ፍቺ ያለው ቃል ___________ ነው፡፡

A. ይቆጠቁጣል C. እያደር

B. ንግግር D. መርዝ

***መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 37 እስከ 50 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ፣ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ የሆነውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ፡፡***

43. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የምክንያትና ውጤት ትስስር ያላቸውን አረፍተነገሮች ለማያያዝ ያገለግላል፡፡

A. በጥቅሉ C. ስለዚህ

B. ቢሆንም D. ወይም

45. "ማንኛውም ስፖርተኛ በተሰማራበት የስፖርት አይነት ውጤታማ ለመሆን በቂ ልምምድ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ አለበለዚያ በውድድር ላይ

ወገቤን ማለቱ አይቀርም፡፡ ጥሩ ልምምድ ያደረገ ስፖርተኛ በተሳተፈበት ውድድር ሁሉ አሸናፊ የመሆን እድሉ የሰፋ ነው፡፡"

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ከመጀመሪያው ወደ ሁለተኛው አረፍተነገር መሸጋገሪያ ሆኖ ያገለገለው የቱ ነው?

A. ይኖርበታል
B. ማለቱ አይቀርም
C. ማድረግ ይኖርበታል
D. አለበለዚያ

**መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 66 እስከ 85 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡**

66. ተውሳከ ግስ ውስጥ የሚመደበው የትኛው ቃል ነው?

A. ብእረኛ
B. ዘመነኛ
C. ምንኛ
D. ፈረሰኛ

67. "ከስራችሁ" የሚለው ቃል ውስጥ ያለችው "ስ" ጠብቃ የምትነበበው በየትኛው አረፍተነገር ነው?

A. አለቆች ከስራችሁ ያሉትን ሰራተኞች ማንነት በውል ልታውቁ ይገባል፡፡
B. ለእለት ችግራችሁ እንዲደርስላችሁ ከፈለጋችሁ ከስራችሁም ቢሆን እቃውን ሽጡ፡፡
C. ቢነገራችሁም ባለማመናችሁ ከስራችሁ የነበራችሁን አጣችሁ፡፡
D. እቃውን ከስራችሁ የምትለውጡበት ምክንያት አላሳመነኝም፡፡

68. የቋንቋን የመወራረስና የመዋዋስ ፅንሰ ሃሳብን የሚገልፀው የትኛው አባባል ነው?

A. መዋዋስ ለቋንቋዎች መበላሸት በር ይከፍታል፡፡
B. እያንዳንዱ ቋንቋ በራሱ ምሉእ ነው፡፡
C. መዋዋስ የቋንቋና የማህበራዊ ስርአት የሚጠይቀው ግዴታ ነው፡፡
D. ዘመኑ ቋንቋዎች ንፅሕናቸውን ጠብቀው የሚያድጉበት ነው፡፡

69. ሰዋስዋዊ ስህተት <u>የሌለበት</u> አረፍተነገር የትኛው ነው?

A. እኔ የእህቴን ደብተር አመጣሁ፡፡

B. እኔ የእህቴን ደብተሯን አመጣሁላት፡፡

C. እኔ ለእህቴ ደብተር አመጣሁላት፡፡

D. እኔ የእህቴን ደብተሯን አመጣሁባት፡፡

70. "ለጉንጮችሽ" በሚለው ቃል ውስጥ ፆታን ለማመልከት የገባው ጥገኛ ምእላድ ምንድን ነው?

A. -ሽ          C. -ች

B. -ችሽ          D. -ኦችሽ

71. "ጋቢው ተቀደደ፡፡" የሚለው ተራ አረፍተነገር ወደ ስማዊ ሃረግ ቢለወጥ የትኛው ትክክል ይሆናል?

A. ጋቢው ተቀደደ እንዴ          C. ጋቢው ሊቀደድ ነው

B. ጋቢው ይቀደድ          D. ቀዳዳ ጋቢ

72. ከቃላቱ መካከል በስም ውስጥ <u>የማይካተተው</u> የትኛው ነው?

A. መጻፍ          C. ንኡስ

B. መስራት          D. ቋንቋ

73. ከሃረጎቹ መካከል ቅጽላዊ ሃረግ የሆነው የትኛው ነው?

A. ቀዩ ልጅ          C. ብሔራዊ ፈተና

B. በጣም ዘገምተኛ          D. ጠመዝማዛው መንገድ

74. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ለተራ አረፍተነገር ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ወንድምየው ቁርሱን በልቶ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

B. ወንድምየው ቁልፍ ወስዶ ቁም ሳጥኑን ከፈተ፡፡

C. ወንድምየው ከእህቱ ጋር በጋራ ወደ ገበያ ሄደ፡፡

D. ወንድምየው ከመኝታው ተነስቶ አልጋ አነጠፈ፡፡

75. “በመቅደላ አምባ ብዙ ነዋሪዎች አሉ። ሰፈራቸውም እንደአይነታቸው የተለያየ ነው።” በሚለው አረፍተነገር ውስጥ በተሰመረበት ቃል ውስጥ ያለው -አቸው ተግባሩ ምንድን ነው?

A. ቁጥርን ማመልከት
C. ባለቤትን ማመልከት
B. ፆታን ማመልከት
D. ንብረትን ማመልከት

76. “አሁን ልብስ እያጠብኩ ነው።” በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ግሳዊ ሃረጉ ምን የሚለው ነው?

A. እያጠብኩ ነው
C. አሁን ልብስ እያጠብኩ ነው
B. ልብስ እያጠብኩ ነው
D. አሁን ልብስ እያጠብኩ

77. “አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አሰራቸው።” የሚለው ሃተታዊ አረፍተነገር ወደ አሉታዊ አረፍተነገር ሲለወጥ ምን ይሆናል?

A. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ እንዳያስራቸው።
B. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አይሰራቸው።
C. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አይሰር።
D. አጥፊው ተለይቶ እስኪታወቅ ሁሉንም ይዞ አላሰራቸውም።

78. በሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታ የተነገረው ምን የሚለው ቃል ነው?

A. ፈለቀቀች
C. ፈለቀቅሽ
B. ፈለቀቀ
D. ፈለቀቅህ

79. “አብዛኛው ወላጅ ለልጆቹ ተገቢውን እንክብካቤ ያደርጋል።” በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ያለው መስተዋድዳዊ ሃረግ ምን የሚለው ነው?

A. ለልጆቹ
C. እንክብካቤ ያደርጋል
B. አብዛኛው ወላጅ
D. ተገቢውን እንክብካቤ

80. “የመንደራችን ወጣቶች ስንፍናን ለመዋጋት ቃል ገቡ!” በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ___________ የስም ገላጭ ነው።

A. ስንፍናን ለመዋጋት
C. የመንደራችን
B. የመንደራችን ወጣቶች
D. ለመዋጋት

81. “ቀለሟ በጣም የሚያምር የቤት ፈትል ቀሚስ አሰርታ ለበሰች፡፡” በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የግስ ገላጩ __________ ነው፡፡

A. ቀለሟ በጣም የሚያምር

B. በጣም የሚያምር የቤት ፈትል ቀሚስ አሰርታ

C. ቀለሟ በጣም የሚያምር የቤት ፈትል ቀሚስ

D. የቤት ፈትል ቀሚስ

82. የቋንቋ መሠረቱ ምንድነው?

A. ምእላድ

C. ድምፅ

B. ቃል

D. ሃረግ

83. ስለቋንቋ ትክክል የሆነውን ሃሳብ የሚያንፀባርቀው __________ ነው፡፡

A. በነገሮችና በስያሜያቸው መካከል የባህርይ ግንኙነት አለ፡፡

B. አንድ ቋንቋ በየትኛውም አካባቢ ያሉትን ነገሮች ይገልጻል፡፡

C. ቋንቋ በዘር ስለሚወረስ አማርኛን የሚናገረው አማራ ነው፡፡

D. ቋንቋ ይወለዳል የሚለው ሃሳብ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡

84. ከቃላቱ ውስጥ መድረሻ ቅጥያ ያለው የትኛው ነው?

A. ሰብአዊ

C. እንቅልፍ

B. ፍትህ

D. ሃገር

85. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ አንዱ ነፃ ምእላድ ነው?

A. መወጣጫ

C. መዘፍዘፊያ

B. መሸጋገሪያ

D. ብርጭቆ

# አባሪ መ

## ከ2004 ዓ.ም. ከሀገር አቀፍ ፈተና የተወሰዱ የሰዋስው ይዘት ጥያቄዎች

## NATIONAL AGENCY FOR EDUCATIONAL ASSESSMENT AND EXAMINATIONS (NAEAE)

## ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE AMHARIC EXAMINATION

## GINBOT 2004/MAY 2012

BOOKLET CODE: 83

## የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና

## ግንቦት ፳፻፬/2004 ዓ.ም

**የዚህ ጥራዝ መለያ፡- 83**

***መመሪያ፡-* ከተራ ቁጥር 12 እስከ 34 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡**

12. "ወርቅነሽ <u>በጣም ወፍራም</u> ልጅ አዝላ መጣች፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት የትኛውን ሀረግ ያመለክታል?

    A. ቅጽላዊ ሀረግ.  C. ስማዊ ሀረግ

    B. ግሳዊ ሀረግ  D. መስተዋድዳዊ ሀረግ

13. "ጎረቤታችን ራሱን እስኪስት ድረስ <u>ገና</u> በጠዋት ለምን እንደሚጠጣ ይገርመኛል፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል?

A. ግስ C. ቅጽል

B. መስተዋድድ D. ተውሳከ ግስ

14. "ቆራጥና ጎበዝ የሆኑ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የመወጣት ብቃት አላቸው።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የስም ገላጩ __________ ነው።

A. ቆራጥና ጎበዝ የሆኑ C. ቆራጥና ጎበዝ የሆኑ ሰዎች

B. ቆራጥና ጎበዝ D. ጎበዝ የሆኑ ሰዎች

15. ተራ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?

A. አርቆ አሳቢ የሆኑ ሰዎች የማመዛዘን ችሎታ አላቸው።

B. ወንዝ ተሻግሮ የመጣ ጠላት ሳይገድል አይመለስም።

C. ታናሽ እህቴ በትላንቱ መርከብ ወደ ውጪ ሀገር ሄደች።

D. በሀገሬ ማር የተጣለው ጠጅ ተጠጥቶ አይጠገብም።

16. "በነጋዴዎቹና በሸማቾቹ መካከል የተፈጠረውን ፍጥጫ ማብረድ ካልተቻለ፣ የኑሮ ውድነት በጣም ሊንር ይችላል።" በተሰመረበት ቃል ውስጥ ጠብቆ የሚነበበው ድምጽ የሚገኝበት ሆሄ የትኛው ነው?

A. /ጥ/ C. /ፍ/

B. /ጭ/ D. /ጫ/

17. "ኑሮህ ለአደጋ እንዳይጋለጥ ምን አይነት ጥንቃቄዎችን ታደርጋለህ?" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የትኛውን ይገልጻል?

A. ሁለተኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ

B. አንደኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ

C. ሁለተኛ መደብ፣ብዙ ቁጥር፣ተባእታይ ጾታ

D. ሶስተኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣አንስታይ ጾታ

18. "እናቴ ብዙ ደክማ የሰራችው ቤት በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ያለው ግሳዊ ሀረግ __________ ነው።

A. በአነስተኛ ዋጋ C. በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ

B. እናቴ ብዙ ደክማ D. የሰራችው ቤት

19. "አቶ ከበደ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ሀገር ቤት ሄዱ፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ምን ዓይነት ሀረግ ነው?

A. ቅጽላዊ ሀረግ
B. ግሳዊ ሀረግ
C. ስማዊ ሀረግ
D. መስተዋድዳዊ ሀረግ

20. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ትክክል ነው፡፡

A. ንቦች በቋንቋ የሚግባቡ ማህበራዊ እንስሳ መሆናቸው ይታመናል፡፡
B. የቋንቋ ባለቤት የሆነው ብቸኛ ማህበራዊ እንስሳ ሰው ነው፡፡
C. ወፎች ማለዳ ተነስተው ዝማሬ የሚያሰሙት ቋንቋ ስላላቸው ነው፡፡
D. እንስሳት ቋንቋ ስላላቸው በራሳቸው ቋንቋ ሰላምታ ይለዋወጣሉ፡፡

21. "ሙስና ውስጥ የሚዘፈቁ ሰዎች ለሀገራቸው የማይቆረቆሩ ስግብግቦች ናቸው፡፡" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ _________ ነፃ ምእላድ ነው፡፡

A. /-ሞች/
B. ስግብግቦ
C. ስግብግብ
D. /-ኦች/

22. "ከትምህርት ቤታችን መምህራን መካከል ሶስቱ ፈረሶች እንደገዙ ሰማሁ፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ስንት ጥገኛ ምእላዶች ይዟል?

A. ሶስት
B. አንድ
C. አራት
D. ሁለት

23. በቃላት አደራደር ስርአቱ ትክክለኛነት ተገቢ መልእክት የሚያስተላልፈው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. ሴቶቹ የተቀቡት መዓዛ የሽቶ ያውዳል፡፡
B. ሴቶቹ የተቀቡት የሽቶ መዓዛ ያውዳል፡፡
C. ሴቶቹ የተቀቡት ሽቶ መዓዛው ያውዳል፡፡
D. ሴቶቹ የተቀቡት ሽቶ የመዓዛው ያውዳል፡፡

24. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል አንዱ ውስብስብ ነው፡፡

A. ታታሪ ገበሬ በርካታ የጓሮ አትክልት ለመትከል ይጥራል፡፡
B. ምርጥ ዘር የተጠቀሙ ገበሬዎች የተትረፈረፈ ምርት አገኙ፡፡
C. ቅድመ አያቶቻችን ስራ ወዳድ፣ ታታሪና ጀግና ያደንቁ ነበር፡፡

D. ጎበዝ ተማሪዎች በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያገኛሉ፡፡

25. በትክክለኛው የቃላት ምርጫ የተገነባው አረፍተነገር የትኛው ነው፡፡

A. የንግድ ምንስቴር ምኒስቴር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ፡፡

B. የንግድ ምንስቴር ምኒስትር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ፡፡

C. የንግድ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ፡፡

D. የንግድ ሚኒስቴር ምኒስትር ዴኤታ ለሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ሽልማት ሰጡ፡፡

26. "የእግር ኳስ አጫዋች ዳኞች ፍትሀዊ መሆን እንዳለባቸው ይነገራል፡፡" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ የሚገኘው መድረሻ ምእላድ ምንድነው?

A. /-ኣዊ/ C. /-ትሀዊ/

B. /-ሀዊ/ D. /-ዊ/

27. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የትኛው ቃል ቅጽላዊ ሀረግ ሊያስመሰርት ይችላል?

A. ዘመን C. ሥልጣኔ

B. ዘመናዊ D. ሠለጠነ

28. ከሚከተሉት መካከል በመሪነት የተቀመጠው ስም ከምን እንደተሰራ የሚጠቁመውን ስማዊ ሀረግ የያዘው አረፍተነገር የትኛው ነው?

A. የቆዳው ጃኬት ተላልጧል፡፡

B. የአንበሳ ጫማ በውድ ዋጋ ተሸጠ፡፡

C. የቅርጫት ኳስ ይወደዳል፡፡

D. የቦርሳው ዋጋ አይቀመስም፡፡

29. "የንግድ ፈቃድ በወቅቱ አልታደሰም፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የግሱ ገላጭ ምን የሚለው ነው?

A. የንግድ B. ፈቃድ

C. በወቅቱ D. አልታደሰም

30. ከሚከተሉት ውስጥ ለተውሳከ ግሳዊ ሀረግ የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. ክፉኛ እየሳለ C. ጠንካራው ተማሪ

B. በጣም ክፉኛ D. በጣም ጠንካራ

31. "የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ፕሮግራም ነው።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሀረጉ የትኛው ነው?

A. የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠል

B. የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ ተጠናክሮ

C. የአረንጓዴ ልማት

D. የአረንጓዴ ልማት ዘመቻ

32. ከሚከተሉት ውስጥ ለነጻ ምእላድ የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. ተንኮለኛ C. ስምምነት

B. ሰማእት D. ስምምነቶች

33. ከሚከተሉት መካከል በተለየ የአጠማመር ስልት የተመሠረተው የትኛው ጥምር ቃል ነው?

A. ትምህርትቤት C. ዳቦቤት

B. ሻይቤት D. ቤተመንግሥት

34. "___________ አብዛኛውን ጊዜ ስለሰው የሚገልጽ፣ የሚመራመር፣ የሙያ መስክ ነው።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ለባዶ ቦታው ተገቢ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ጋዜጣዊ C. ጋዜጠኞች

B. ጋዜጣ D. ጋዜጠኛነት

**መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 35 እስከ 47 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ።**

35. "ከበደ ጮቅ ነው፤ ሳይታወቅበት ባላጋራዎቹን እንዴት ማሽነፍ እንደሚችል አሳምሮ ያውቃል።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ፍካሬያዊ ፍቺ ያለው ቃል ___________ ነው።

A. ጮቅ
B. ማሽነፍ
C. አሳምሮ
D. ባላጋራዎቹን

39. "ሳሳ" የሚለው ቃል "ከሳ" የሚል ፍች የሚኖረው በየትኛው አረፍተነገር ውስጥ ነው?

A. አባትየው ለልጁ ሳሳ።
B. በርኖሱ ሳሳ።
C. እንጀራው ሳሳ ይላል።
D. ተድላ ሰውነቱ ሳሳ።

40. "አሰራጨ" የሚለው ቃል "አዛመተ" የሚል ፍች የሚኖረው በየትኛው አረፍተነገር ውስጥ ነው?

A. ንጽህናው ያልተጠበቀ ውሃ ለበሽታው መሰራጨት አንዱ ምክንያት ነበር።
B. መመሪያው ከላይ እስከ ታች እየተሰራጨ ነው።
C. ዜናው በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች ተሰራጭቷል።
D. የጋዜጣ በወቅቱ አለመሰራጨት የመረጃ ውሱንነትን ያስከትላል።

41. "ነከረ" የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው አረፍተነገር ነው?

A. አንድም ቀን በሳል ሀሳብ አቅርቦ አያውቅም፤ የተነከረ ነው።
B. ገመዱን ውሃ ውስጥ ነከረው።
C. እየነከሩ ያወጡት መሆኑ በአነጋገሩ ያስታውቃል።
D. ሰሎሞን ከተነከረ ያልተጠመዘዘ ነው።

42. "ደረቅ" የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍቺው የገባው በየትኛው አረፍተነገር ውስጥ ነው?

A. ደረቅ በመሆኑ ሰዎቹ ሊያሳምኑት አልሞከሩም።
B. ደረቅ እንጨት በቀላሉ ይሰበራል።
C. ደረቅ ኬክ ከባክቴሪያ ነጻ ነው ተብሎ ይገመታል።
D. የቁርበቱ ደረቅነት በቀላሉ ለመጫን ጠቅሟል።

47. “ሬዲዮው <u>የጀርመን</u> ስራት ነው፡፡ <u>በጀርመን</u> ሬዲዮ ስለ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ሰፊ ገለጻ ተደረገ፡፡” በሚሉት አረፍተነገሮች የተሰመረባቸው ቃላት ከገቡበት ሁኔታ አንፃር በቅደም ተከተል ምንን ያመለክታሉ?

A. የመጀመሪያው ሬዲዮው የተፈበረከበትን ሀገር፣ ሁለተኛው የሬዲዮ ጣቢያውን

B. የመጀመሪያው የሬዲዮ ጣቢያውን፣ ሁለተኛው የተፈበረከበትን ሀገር

C. የመጀመሪያው የሬዲዮ ጣቢያውን፣ ሁለተኛው ሬዲዮው ንብረትነቱ የጀርመኖች መሆኑን

D. የመጀመሪያው ሬዲዮው የተፈበረከበትን ሀገር፣ ሁለተኛው ሬዲዮው ንብረትነቱ የጀርመኖች መሆኑን

# አባሪ ሠ

## ከ2005 ዓ.ም. ከሀገር አቀፍ ፈተና የተወሰዱ የሰዋስው ይዘት ጥያቄዎች

## NATIONAL EDUCATIONAL ASSESSMENT AND EXAMINATIONS AGENCY(NEAEA)

## ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE AMHARIC LANGUAGE EXAMINATION

## GINBOT 2005/MAY 2013

## BOOKLET CODE: 81

## የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

## ግንቦት ፳፻፭ ዓ.ም.

**የዚህ ጥራዝ መለያ፡- 81**

***መመሪያ፡-* ከተራ ቁጥር 1 እስከ 20 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ሰዋስውን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል የሆነውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጭ/ምረጥ፡፡**

1. አንባቢያን በሚለው ቃል ውስጥ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክተው ቅጥያ ምን የሚለው ነው?

   A. -ኣን C. -ያን

   B. -ቢያን D. -ን

2. "ፈረሙባቸው" በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ጥገኛ ምዕላዶች የትኞቹ ናቸው?

   A. -ባ-ቸው C. ኡ-ባ-ቸው

   B. -ባ-ቸ-ው D. ኡ-በ-ኣቸው

3. ከሚከተሉት ውስጥ ለግሳዊ ሀረግ የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. አንደበተ ርቱዕና ተናግሮ የማያስቀይመው ጎረቤታችን

B. መሸለምን የዘወትር ልማዷ ያደረገችው ብሩክታይት

C. ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ተዘጋጅታለች

D. የዘመኑ ኮከብ ተጫዋች የነበረው ሙሉጌታ ከበደ

4. ከግስ ላይ ለተመሰረተ ውልድ ስም የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. ገራገርነት

B. ግራጫማ

C. ነቀፌታ

D. ዳገታማ

5. "የልጁን ማንነት ለማወቅ መስቀልኛ ጥያቄ ጠየቁት፡፡" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ ያለው "ት" ተግባር ምንድን ነው?

A. ባለቤትን ማመልከት

B. ድርጊትን ማመልከት

C. ተሳቢን ማመልከት

D. አድራጊን ማመልከት

6. በአንድ አረፍተነገር ውስጥ የአረፍተነገሩ ባለቤት የሚገኝበት የሀረግ አይነት ምን ይባላል?

A. ስማዊ ሀረግ

B. ግሳዊ ሀረግ

C. ቅጽላዊ ሀረግ

D. መስተዋድዳዊ ሀረግ

7. "በጣም ጎበዝ ተማሪ" በሚለው ሀረግ ውስጥ የተሰመረበት ምን አይነት ገላጭ ነው?

A. የስም ገላጭ

B. የግስ ገላጭ

C. የስምና የግስ ገላጭ

D. የባለቤትና የግስ ገላጭ

8. "ገና" በሚለው ቃል ለሚመሰረት ተውሳከግሳዊ ሀረግ የትኛው ትክክል ነው?

A. ገና እየመጣ ነው

B. በጣም ገና

C. ገና ይወፍራል

D. እጅግ ገና ነው

9. ቀጥሎ ከቀረቡት አረፍተነገሮች መካከል ውስብስብ አረፍተነገር የቱ ነው?

A. ፈተና ስለወደቀች ትምህርቷን አቋረጠች፡፡

B. ስልጣኔ የሚለውን ቃል ሰዎች በቀላሉ አይረዱትም፡፡

C. ኢትዮጵያ የተለያዩ የልማት መርሃግብሮችን ነድፋለች፡፡

D. ወተት እርጎ፣አይብ እና ቅቤ ይወጣዋል፡፡

10. ለተራ አረፍተነገር የትኛው ምሳሌ ይሆናል?

A. እህተ በጣም ነቃ ያለችና አስተዋይ ተማሪ ነች፡፡

B. መንበረ እጅግ ጨዋ በመሆኗ ሁሉም ያከብራታል፡፡

C. ዳዊት መጠየቅና መከራከር በጣም ይወዳል፡፡

D. መሀመድ ጥናት ከማፍቀሩም በላይ ትሁት ነው፡፡

11. አንገታም የሚለው ቃል ሁለት ፍቺ ሊሰጥ የሚችለው ምን ሲሆን ነው?

A. "ን" ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ነው፡፡

B. "ገ" ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ነው፡፡

C. "ታ" ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ነው፡፡

D. "ን" ጠብቆ ሲነበብ እና "ገ" ላልቶ ሲነበብ ነው፡፡

12. የጥሬ ስጋ ማባያን አንዳንዶች "አዋዜ" ይሉታል፤ሌሎች ደግሞ "ዳጣ" ወይም "ቆጭቆጫ" ይሉታል፡፡ ይህ አሰያየም ከቋንቋ መሰረታዊ ባህርያት መካከል ይበልጥ የቱን ያሳያል?

A. የቋንቋን ስርዓታዊነት

B. የቋንቋን ዘፈቀዳዊነት

C. የቋንቋን ተዋዋሽነት

D. የቋንቋን ረቂቅነት

13. ትእዛዛዊ አረፍተነገር የቱ ነው?

A. ሰፈርተኛው ሁሉ ወገቡን አስሮ ለልማት ተነሳሳ፡፡

B. ካልዘሩ ማጨድ ስለሌለ በርትቶ መስራት ጠቃሚ ነው፡፡

C. ጨዋታችሁን አቁሙና ቤተመጻህፍት ገብታችሁ አንብቡ፡፡

D. ድህነት ቀንደኛ ጠላታቸው መሆኑን አውቀው ለስራ ተነቃቁ፡፡

14. ውሻ በሚለው ስም ላይ ___________ የሚል ቅጥያ ሲጨመር የውሻው ጾታ ይታወቃል፡፡

A. -ኢቱ

B. -ኦች

C. -ኤ

D. -ኣችን

15. ከሚከተሉት ስሞች መካከል "-ኦች" የሚለውን ቅጥያ በመውሰድ የሚበዛው ቃል የትኛው ነው?

A. አሸዋ C. ወተት

B. ሴት D. ዝናብ

16. ባለ አንድ ምእላድ የሆነው ቃል __________ ነው፡፡

A. ሆዳም C. ደብተሬ

B. ድርሰት D. ድመቷ

17. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አሉታዊ አረፍተነገር የትኛው ነው?

A. ሰውየው በጣም ሃይለኛ ሰው ነው፡፡

B. ሴትየዋ ጠንካራ መኪና ገዛች፡፡

C. አትሌቱ ወደ ለንደን አልሄደም፡፡

D. በመጥፎ ሥነምግባሩ ይቀጣ፡፡

18. "-ኧኛ" የሚለውን ቅጥያ በመውሰድ አዲስ ቃል ሊመሰረትበት የሚችለው ቃል የቱ ነው?

A. ሱዳን C. ወንድ

B. በር D. አናጺ

19. "<u>በጣም ትጉህ</u> ሰዎች ካሰቡበት ቦታ ለመድረስ የሚከለክላቸው የለም፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ከየትኛው የሀረግ አይነት ውስጥ ይመደባል?

A. ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ C. ቅጽላዊ ሀረግ

B. ስማዊ ሀረግ D. ግሳዊ ሀረግ

20. "ዳለቻ" የሚለውን ቃል የአማርኛ ቋንቋ ከኦሮምኛ ቋንቋ የወሰደው ነው ብንል፣ ክስተቱ ምንን ይጠቁማል?

A. ቋንቋ ምሉእ መሆኑን

B. የቋንቋ አንዱ ባህርይ ውሰት መሆኑን

C. ቋንቋ ዘፈቀዳዊ መሆኑን

D. የቋንቋ አንዱ ባህርይ ስርዓታዊነት መሆኑን

**መመሪያ፡- ከተራ ቁጥር 29 እስከ 36 ድረስ ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል የሆነውን መልስ ምረጭ/ምረጥ፡፡**

29. "ንፉግ" በሚለው ቃል ላይ "ነት" የሚል ቅጥያ ምዕላድ ሲጨመር የሚገኘው ቃል ፍች ምን ይሆናል?

A. የማይሰጥ
B. አለመስጠት
C. ገብጋባነት
D. መሰሰት

30. "ቴክኖሎጂን በተመለከተ <u>ባይተዋር</u> ስለሆነ ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልገዋል፡፡" የተሰመረበትን ቃል በፍቺ ሊተካው የሚችለው __________ ነው፡፡

A. እንግዳ
B. መጤ
C. ፈሪ
D. አስተዋይ

35. በግርጌያቸው ከተሰመረባቸው ቃላት መካከል በእማሬያዊ ፍቺው የገባው የትኛው ነው?

A. ሰናይት ያገባችው ባል <u>መልአክ</u> ነው፡፡
B. ትላንት በጎርፍ ተራቁቶ የነበረው <u>ተራራ</u> ዛሬ በደን ተሸፍኗል፡፡
C. እሷ እንደሆን <u>መሬት</u> ናት፤ ያሏትን ሁሉ እሺ ነው የምትለው፡፡
D. ልጃችን አድጎ ይኸው ስንጣላ <u>ሽማግሌ</u> ሆኖ ያስታርቀናል፡፡

36. "ብዙ ዘመን አብረው ቢኖሩም፣ በልጆቻቸው መካከል በተፈጠረው ነገር አሁን <u>ደመኛ</u> ሆነዋል፡፡" የተሰመረበትን ቃል በፍቺ የሚቃረነው ቃል የትኛው ነው?

A. ባላጋራ
B. ወዳጅ
C. አማች
D. አበልጅ

# አባሪ ረ

## ከ2006 ዓ.ም. ከሀገር አቀፍ ፈተና የተወሰዱ የሰዋስው ይዘት ጥያቄዎች

## NATIONAL EDUCATIONAL ASSESSMENT AND EXAMINATIONS AGENCY (NEAEA)

## ETHIOPIAN GENERAL SECONDARY EDUCATION CERTIFICATE AMHARIC EXAMINATION

## GINBOT 2006/MAY 2014

**BOOKLET CODE: 012**

## የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

## ግንቦት ፳፻፮ ዓ.ም.

**የፈተና ጥራዝ መለያ�:- 012**

***መመሪያ ፬:- ከተራ ቁጥር 34 እስከ 41 ድረስ ቃላትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።***

34. "የአንድን ተውኔት ጭብጥ ቢያንስ በደንብ <u>በተንሰላሰለ</u> ነጠላ አረፍተነገር ወይም ቢበዛ ደግሞ በድርብ አረፍተነገር ብቻ መግለጽ ይቻላል።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ከግርጌው ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳዩ ምን ሊሆን ይችላል?

    A. በተጠላለፈ
    B. በተቆላለፈ
    C. በተቀጣጠለ
    D. በተደራጀ

35. "ዘልቋል" የሚለው ቃል "ተዳርሷል" የሚል ፍች እንዲኖረው የሚያደርገው የትኛው አረፍተነገር ነው?

A. ምስማሩ ወደ ውስጥ ዘልቋል።

B. ወሬው አገር ቤት ድረስ ዘልቋል።

C. ልጁ በትምህርቱ ዘልቋል።

D. እንግዳው ወደ ውስጥ ዘልቋል።

36. "ይሰጣሉ" የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍቺው **ያልገባው** በየትኛው አረፍተነገር ነው?

A. ከዋክብት እንደ ፀሀይ ሁሉ ብርሃን ይሰጣሉ።

B. የቀበሌያችን ነዋሪዎች ለተቸገሩ ሰዎች በየአመቱ እርዳታ ይሰጣሉ።

C. ዓላማ ያላቸው ሰዎች ለመልካም ተግባር ህይወታቸውን ይሰጣሉ።

D. ልጆቹ በወሬ መካከል የሚሆነውንም የማይሆነውንም ይሰጣሉ።

41. "የሰርጉ ደጋሾች ከተጠሩት እንግዶች ይልቅ ቋሚዎችን ለማብላት ቅድሚያ ሰጡ።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው?

A. አስተናጋጆች

B. በህይወት ያሉ

C. ቆመው የሚውሉ

D. የማይለወጡ

***መመሪያ ፮፡- ከተራ ቁጥር 58 እስከ 78 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ሰዋስውን የሚመለከቱ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጪ/ምረጥ።***

58. _____________ በቃላት ላይ የሚቀጠሉት ቅጥያዎች ተግባር ነው።

A. በቃሉ ላይ ሰዋስዋዊ ለውጥ እንዲኖር ማድረግ

B. በቃሉ ላይ መሰረታዊ ለውጥ እንዲኖር ማድረግ

C. የቃሉ አነባበብ በመጠኑ እንዲለወጥ ማድረግ

D. የቃሉን ፍቺ ሙሉ በሙሉ መለወጥ

59. "-ኣችሁ" የተሰኘው ቅጥያ ባለገንዘብን ለማመልከት የገባው በየትኛው ቃል ውስጥ ነው?

A. መቅረታችሁ C. ቤታችሁ

B. ተፈተናችሁ D. ገደላችሁ

60. ከሚከተሉት ውስጥ ተራ አረፍተነገር የሆነው የትኛው ነው?

A. ኦዲት ተደርጎ የቀረበው የማህበራችን ሂሳብ ለውይይት ቀረበ፡፡

B. የመጠጥ ሱሰኛ የሆነ ሰው ኃላፊነትን ለመሸከም ብቁ አይደለም፡፡

C. ቀናነትና በጎ አስተሳሰብ የንቃትና የብርታት መንፈስ መሰረት ናቸው፡፡

D. የእግር ኳስ ውድድሩ እንደተጀመረ የመጀመሪዋ ግብ ተቆጠረች፡፡

61. ከቅፅል ላይ ለተመሰረተ ውልድ ስም የትኛውን በማስረጃነት መውሰድ ይቻላል?

A. ልጅነት C. ሰውነት

B. እውንነት D. ሰላማዊነት

62. ከሚከተሉት ውስጥ ነፃ ምእላድ የሆነው የትኛው ነው?

A. ሀብታም C. ትርንጎ

B. አይነኬ D. መከረኛ

63. ______________ የቋንቋ መሰረታዊ ባህርይ ነው፡፡

A. ዘላለማዊነት C. አይለመዴነት

B. ተዋዋሽነት D. አይለወጤነት

64. "እክስቴ የጠላውን አተላ ደፋችው፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ በተሰመረበት ቃል ውስጥ ያለው "-ን" ተግባሩ ምንድን ነው?

A. ባለቤትን ማመልከት C. ግስን ማመልከት

B. ተሳቢን ማመልከት D. ገላጭን ማመልከት

65. ከሚከተሉት ውስጥ ለአንድ ቋንቋ ስርጭትና እድገት እገዛ **የማያደርገው** የትኛው ነው?

A. የመገናኛ ብዙሃን ስርጭት

B. የተናጋሪው ህዝብ ብዛት

C. ከውሰት ነፃ የሆነ መድበለ ቃላት

D. የትምህርት መስፋፋት

66. ከሚከተሉት ውስጥ ሀተታዊ አረፍተነገር የሆነው የትኛው ነው?

A. በዛሬው እግር ኳስ ጨዋታ አጥቂው እንዲህ የፈዘዘው ለምን ይመስልሀል?

B. በዛሬው ጨዋታ የተመለከትነው የእግር ኳስ ጥበብ ይደነቃል እንዴ?

C. በዛሬው የእግር ኳስ ጨዋታ ግብ ጠባቂ ለመሆን በደንብ ተዘጋጅ!

D. በዛሬው የእግር ኳስ ጨዋታ ተጫዋቾቹ እንደጠበቅሁት አልተጫወቱም፡፡

67. "ፀሀይ የሀገር ባህል ስትለብስ ውብ ሆና <u>ትታያለች</u>፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል፣ አረፍተነገሩ ለየትኛው የተነገረ መሆኑን ያመለክታል?

A. ሁለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አንስታይ ፆታ

B. ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አንስታይ ፆታ

C. ሁለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባእታይ ፆታ

D. ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባእታይ ፆታ

68. "በአካባቢያችሁ ስለሚገኝ ሐይቅ ወይም ግድብ ወይም ወንዝ ማህበራዊ አገልግሎት በጽሁፍ አስረዱ፡፡" የሚለው ለ______________ የአረፍተነገር ስልት በምሳሌነት ይጠቀሳል፡፡

A. ለመጠይቃዊ የአረፍተነገር ስልት

B. ለትዕዛዛዊ የአረፍተነገር ስልት

C. ለሀተታዊ የአረፍተነገር ስልት

D. ለአሉታዊ የአረፍተነገር ስልት

69. "ገበያተኛ መስለው የሚዘርፉ አታላይ ሰዎች ከገበያ ውስጥ በፖሊስ እየተመነጠሩ ታሰሩ፡፡" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ያለው ቅፅል ______________ ነው፡፡

A. ገበያተኛ

B. በፖሊስ

C. እየተመነጠሩ

D. አታላይ

70. "<u>መጽሃፉ</u> በድጋሚ ታትሞ ለገበያ ቀረበ።" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ ያለው መድረሻ ቅጥያ ተግባር ______________ ማመልከት ነው።

A. እምርነትን C. ቁጥርን

B. አድራጊነትን D. ፆታን

71. "ወገኔ ከመጻህፍት መደርደሪያ ላይ ብዙ ጊዜ የሚያነሳቸው መጻህፍት <u>ስለማይገቡት</u>፣ አንብቦ ሳይጨርስ 'ምን አስጨነቀኝ?' እያለ ወደ ነበሩበት ቦታ ይመልሳቸዋል።" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ ጠብቆና ላልቶ በመነበብ አረፍተነገሩ ሁለት መልእክት እንዲኖረው የሚያደርገው ሆሄ ______________ ነው።

A. ማ C. ት

B. ስ D. ገ

72. "ከበደ ከፍቶ የተወውን በር ዘግቶ እንዲሄድ የሚገልጽ ትእዛዝ ደረሰው።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ______________ ስማዊ ሀረግ ነው።

A. ከፍቶ የተወውን በር

B. የተወውን በር ዘግቶ

C. ከበደ ከፍቶ

D. በር ዘግቶ

73. "ፈጣኑ አበበ ከወንድሙ ጋር ተግቶ አጠና።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጉ የትኛው ነው?

A. ከወንድሙ ጋር

B. ፈጣኑ አበበ ከወንድሙ ጋር

C. ከወንድሙ ጋር ተግቶ

D. ከወንድሙ ጋር ተግቶ አጠና

74. "የተመረዘ ምግብ የሚባለው ሰዎችን ወይም እንስሳትን ለአደጋ የሚዳርግ ነገር የተቀላቀለበት ምግብ ነው።" በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ______________ የስም ገላጭ ነው።

A. የሚባለው C. ምግብ

B. የተመረዘ D. እንስሳትን

75. "በመንኮራኩር ወደ ጠፈር ሄደ።" የሚለው ሀረግ ምሳሌነቱ ለየትኛው ነው?

A. ለግሳዊ ሀረግ

B. ለስማዊ ሀረግ

C. ለተውሳከግሳዊ ሀረግ

D. ለመስተዋድዳዊ ሀረግ

76. ከሚከተሉት ውስጥ ውስብስብ አረፍተነገር የሆነው የትኛው ነው?

A. ከሶስት ሳምንት በኋላ ደብዳቤ በፖስታ ቤት መጣልኝ።

B. የፈተና ውጤቴንና የምማርበትን ትምህርት ቤት አውቂያለሁ።

C. የጠበቃው ምክር በፍርድ ቤት ተሟግቼ እንዳሸንፍ ረድቶኛል።

D. እኔ፣ ወንድሜና ታናሽ እህቴ ምክርህን ስራ ላይ አውለናል።

77. "በአዲስ አበባ በርካታ ነዋሪዎች አሉ፤ ሰፈራቸውም እንደአይነታቸው የተለያየ ነው።" በሚለው አረፍተነገር በተሰመረበት ቃል ውስጥ ያለው "-ኣቸው" ተግባሩ ምንድን ነው?

A. ቁጥርን ማመልከት

B. ፆታን ማመልከት

C. ተሳቢን ማመልከት

D. ባለንዘብን ማመልከት

78. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ የእርባታ ቅጥያ ያለው የትኛው ቃል ነው?

A. ሰራተኛ C. ተቀማጭ

B. መንገዳችን D. ስብራት

# አባሪ ሰ

## ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን

| ተ.ቁ | ይዘት | 9ኛ ክፍል | | 10ኛ ክፍል | | በየፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1997 | 2004 | 1997 | 2004 | 2001 | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 |
| 1 | የቋንቋ መሰረተ ሀሳቦች | 1 | 2 | 4 | 5 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 2 |
| 2 | ስነ-ድምጽ | | | | | | | | | | |
| 2.1. | የድምጽ መጥበቅና መላላት | 2 | 5 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 2.2. | የሚረዝሙና የሚያጥሩ ድምጾች | - | - | - | 1 | - | - | - | - | - | - |
| 3 | ስነ-ምዕላድ | | | | | | | | | | |
| 3.1. | ምእላድ (ነጻ እና ጥገኛ | 3 | 9 | 2 | 4 | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 2 |
| 3.2. | የጥገኛ ምእላድ ተግባር | 3 | 3 | - | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 5 |
| 3.3. | የቃልና የምእላድ አንድነት | - | 1 | - | - | - | 1 | - | - | - | - |
| 3.4 | የቃል ክፍሎች | 2 | 9 | - | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | - | 1 |
| 3.4.1. | የቃል ምስረታ | 8 | 2 | 4 | 6 | 1 | 1 | - | 1 | 4 | 2 |
| 4 | ስነ-አገባብ | | | | | | | | | | |
| 4.1.1. | ስነ-ሐረግ | | | | | | | | | | |
| 4.1.2. | የሀረግ ዓይነትን መለየትና መመስረት | - | 5 | 5 | 7 | 2 | 4 | 4 | 7 | 4 | 3 |
| 4.1.1. | የስምና የግስ ገላጭ | 1 | - | - | - | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 |
| 4.2. | አረፍተ ነገር | | | | | | | | | | |
| 4.2.1. | የአ.ነ. ክፍሎች | 1 | 4 | 1 | - | 2 | - | - | - | - | - |
| 4.2.2. | ተራ እና ውስብስብ አ.ነ. | 1 | 1 | 3 | 7 | 2 | - | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 4.2.3. | የአ.ነ. ስልት | - | - | - | 5 | - | - | 1 | - | 2 | 2 |
| 4.2.4. | ሰዋስዋዊ ስህተት | 3 | 1 | 3 | - | - | - | 1 | - | - | - |
| 4.2.5. | ተገብሯዊ አ.ነ. መመስረት | - | - | 1 | - | - | - | - | - | - | - |
| 4.2.6. | ቃላትን በአገባብ ቅደም ተከተል በማደራጀት አ.ነ. ማስተካከል | 1 | - | - | - | 1 | - | - | 1 | - | - |
| 4.3. | አያያዥ/መሸጋገሪያ ቃላት | - | 7 | 1 | 3 | 1 | - | 2 | - | - | - |
| 5 | ስነ-ፍች | | | | | | | | | | |
| 5.1. | እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ | 1 | 6 | - | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 1 |
| 5.2. | የቃላት ተቃራኒ ፍቺ | 2 | 2 | - | 4 | - | - | - | - | 1 | - |
| 5.3. | የቃላትና ሐረጋት ቀጥተኛ/መዝገበ ቃላዊና አገባባዊ ፍቺ | 17 | 13 | 22 | 13 | 1 | 3 | - | 3 | 1 | 3 |

# ማረጋገጫ

ይህ “ከ2001—2006 ዓ.ም. በሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ትንተና” በሚል ርዕስ የተሰራው ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ ሥራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ሲሳይ ቴሌ

ፊርማ

ቀን፡- መጋቢት 2007 ዓ.ም.